# የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት
# የንግድ ችሎቶች ሥርዓተ-ችሎት

# Federal Democratic Republic of Ethiopia
# Federal First Instance Court Commercial Bench Proceedings Code



ሚያዝያ 2011 ዓ.ም
April, 2019

# የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የንግድ ችሎቶች ሥርዓተ-ችሎት

# Federal First Instance Court Commercial Bench Proceedings Code

ሚያዝያ 2011 ዓ.ም

April, 2019

# የክብርት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ መልዕክት

## Her Excellency Meaza Ashenafi, President of the Federal Supreme Court



አገራችን ኢትዮጵያ ተቋማትን የማጠናከር፣ የመገንባትና የሚመሩበትን ሥርዓት የማበጀት ጉዳይን እንደ አንድ ስትራቴጂክ ጭብጥ በመያዝ በየዘርፉ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት እየተጋች መሆኑ ይታወቃል፡፡

በፌዴራል ፍርድ ቤቶችም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሪነት የፍርድ ቤቶችን መሰረታዊ አሰራር ለመቀየርና ለማዘመን ዘርፈ-ብዙ ስራዎች እየተካሄዱ ይገኛል፡ ፡ ይህም ሂደት ዳኝነትንና እና የዳኝነት ስርዓቱን ለማጠናከር፣ የህግ የበላይነትን ለማረጋጥ፣ የዳኝነት ስርዓቱም ከማናቸውም ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖ እና ጣልቃ-ገብነት ነጻ ለማድረግ፣ እንዲሁም ቀደም ሲል የተጓደለውን የተገልጋዮች እርካታን ለማሳደግ የሚያስችል ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በዚህም አሁን በሥራ ላይ ያሉ መሰረታዊና እና የሥነ-ሥርዓት ህጎች ትርጉም ባለው፣ ተገማችና ግልፅነትን በተላበሰ ስርአት ተግባራዊ የማድረግ አስፈላጊነትን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተጨባጭ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው፡፡ የዳኞችን የእለት ተእለት ሥራዎች በማቅለል የፍርድ ቤቶችን ተልዕኮ በአግባቡ ለማሳካት የሚያግዙ እና የፍርድ ቤት ጉዳዮች አስተዳደርን የሚመለከቱ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎች ለማውጣት ጥናቶች እየተደረጊ ይገኛል፡፡ የጥናቶቹ ዋና ትኩረትም ፍርድ ቤቶች ለጉዳዮች የተለየ ትኩረት በመስጠት ውጤታማ ሥራን በአጭር ቀጠሮ እና በተፋጠነ ሁኔታ ለማከናወን የሚችሉበትን አሰራር በመዘርጋት ቀደም ሲል ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶችን መሙላት ነው፡፡

የዚህ ጥናት ሂደትና ዝግጅት ምእራፍ አንዱ አካልም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ከዚህ ወር ጀምሮ በይፋ በስራ ላይ የዋለውና በጥብቅ የስራ ዲሲፕሊን የሚተገበረው "የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የንግድ ችሎቶች ሥርዓተ-ችሎት" (Commercial Bench Proceedings Code) ነው፡፡ ይህ ስርአተ ችሎት ለአሁኑ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብቻ የተዘጋጀ ሆኖ በማውጫው ላይ በዝርዝር በተመለከቱ በተለያዩ የንግድ ጉዳዮች ፍሰት አመራር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ይህ የሥርዓተ-ችሎት መመሪያ እንደጉዳዮቹ ውስብስብነት እና ቅለት በየትኛውም የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤቶች የንግድ ችሎት የሚቀርቡ አቤቱታዎች እጅግ በተቀላጠፈና ተገማች በሆነ ስርአት ውሳኔ ወይም መፍትሄ የሚያገኙበትን መንገድ የሚመራ ደንብ ነው፡፡

በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሚሰሩ ዳኞች ሥርዓተ-ችሎቱ ቀደም ሲል ሰኔ 1997 ዓ.ም የተዘጋጀውን የዳኞች መርሀ-ችሎት በማሻሻልና በማስፋት የተዘጋጀና የፀደቀ መሆኑን ተረድተው ይዘቱን እንዲተገብሩ ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ፡፡

በዚህ አጋጣሚ ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የንግድ ችሎቶች ሥርዓተ-ችሎት እውን እንዲሆን ሙያዊ እገዛ ላደረጉልን አካላት ሁሉ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

**መዓዛ አሸናፊ**

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት**

**ሚያዝያ 2011 ዓ.ም**

# ማውጫ


መግቢያ 1

**ክፍል አንድ** 5

**በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎቶች የሚታዩ ጉዳዮች አይነት** 5

1.1 **ከንግድ ማህበራት ባለ አክሲዮንነት መብት ጋር የተያያዙ የመብት ጥያቄዎች /ክሶች፣ አቤቱታዎች** 5

1.1.1 የንግድ ማህበራት መፍረስን የተመለከቱ ክርክሮች 5

1.1.2 የማህበራት መፍረስ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች /Dispute During Disolution process/ 6

1.1.3 የንግድ ማህበራት ሂሳብ መጣራት እና ከሂሳብ አጣሪ መሾም ጋር የተያያዙ ክርክሮች 6

1.1.4 በሂሳብ ማጣራት ሂደት የሚቀርቡ ክርክሮች /Dispute during Liquidation/ 6

1.1.5 የሂሳብ ማጣራትን ተከትሎ ከትርፍ ደርሻ ይከፈለኝ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ክርክሮች 7

1.1.6 ከስራ አስኪያጆች መሻር እና ከንግድ ማህበራት አስተዳዳሪዎች ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮች 7

1.1.7 ከተጠባባቂ ስራ አስኪያጅ መሾም ጋር የተያያዙ ክርክሮች 8

1.1.8 ከቃለ ጉባኤዎች መሠረዝ እና ከቃለ ጉባኤ አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ክርክሮች 8

1.1.9 በንግድ ማህበራት ላይ የመክሠር ፍርድ እንዲሰጥ 8

1.1.10 የመጠባበቂያ ስምምነት ሥነ- ስርዓት እንዲከፈት 9

1.1.11 በመክሠር ስነ- ስርዓት ሂደት ወቅት የሚቀርቡ ክርክሮች 9

1.1.12 የንግድ ማህበር ባለ አክሲዮኖች ከአባልነት በፈቃዳቸው እና ተገደው ሲወጡ የሚቀርቡ ክርክሮች 10

1.1.13 ከጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮች 10

1.1.14 የንግድ ማህበር ትርፍ ድርሻ ለመካፈል፣ ሠነዶችን የመመልከት እና የመመርመር፣ የባለ አክሲዮንነት ሠርተፊኬት እንዲሰጥ እና ሌሎች የአክሲዮን ማህበር አባልነት መብቶች እንዲከበሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎች 11

1.1.15 በንግድ ማህበራት የባለ አክሲዮንነት መብት ላይ የሚፈጠር ሁከት፣ ህገወጥ ተግባር ወይም የመብት ጥሰት ለማስቆም የሚቀርቡ ክርክሮች 11

1.2. **ከሚተላለፉ የገንዘብ ሠነዶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች** 11

1.2.1. የተስፋ ወረቀቶች /ሠነዶች/ 12

1.2.2. ቼክን የተመለከቱ ክርክሮች 12

1.3. **ከግልግል ዳኞች ጉባኤ መቋቋም ጋር የሚቀርቡ አቤቱታዎች** 12

1.3.1. የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንዲቋቋም የሚቀርቡ አቤቱታዎች 13

1.3.2. በጊዜአዊነት ለሚቋቋሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዎች የማህተም አገልግሎት የሚቀርብ ማመልከቻ 13

1.3.3. በጊዜአዊነት ለሚቋቋሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዎች ተጨማሪ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚቀርቡ አቤቱታዎች 13

1.4. **በንግድ ህጉ ላይ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እና ሌሎች ከንግድ ህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ህጎች መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች** **13**

1.5. **ግምታቸው እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) የሆኑ የውል ግንኙነቶችን መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄዎች** **14**

**ክፍል ሁለት** **15**

**በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎቶች የስነ-ስርአት ህግ አተገባበር እና የጉዳዮች ፍሰት የጊዜ ስታንዳርድ** **15**

**2.1. ክስ ከመሰማቱ በፊት ያሉ ሂደቶች (pre-trial stages)** 15

2.1.1. የክስ ማመልከቻን ስለመመርመር 15

2.1.2. ለተከሳሽ መጥሪያ መላክ 16

2.1.3. ከቅድመ ክስ መስማት በፊት ጉዳዮችን በአማራጭ በፍርድ ቤት-መር አስማሚ ስለመቋጨት 18

2.1.4. የመከላከያ መልስን ስለመመርመር 19

2.1.5. የፅሑፍ ማስረጃ ስለሚቀርብበት ጊዜና ሁኔታ 19

2.1.6. የፅሑፍ ክርክር የማቀባበል ሥራን ማጠናቀቅ 21

**2.2. ክስን ስለመስማት (Trial)** 21

2.2.1 ስለተከራካሪ ወገኖች አለመቅረብ 21

2.1.2 ስለ ተከራካሪ ወገኖች መቅረብ 22

2.2.3 የሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት ወይም ክስ ውስጥ መግባት 23

2.2.4 ተከራካሪዎቹን ስለመመርመር 23

2.2.5 በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር ላይ የሚቀርቡ መቃወሚያዎች 25

2.2.6 የክርክሩን ጭብጥ መያዝ 26

**2.3. ክርክሩን ስለመስማት እና ምስክሮችን ስለመመርመር** 28

2.3.1 ስለ ምስክሮች 28

2.3.2 ለምስክሮች መጥሪያ መላክ 29

2.3.3 የምስክሮች ተሟልተው አለመቅረብ 30

**2.4. የተከራካሪዎቹ ሙግት መጀመርና ምስክሮችን መመርመር** 32

2.4.1. ስለ ክሱ መከፈትና ሙግትን የመጀመር መብት 32

2.4.2. የማስረጃ አቀራረብ 33

2.4.3. የፍ/ቤቱ ሥልጣን 35

2.4.4. የምስክር ቃልን ለመስጠት ፈቃደኛ ስላለመሆንና ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል 35

2.4.5. ፍርድ 36

**2.5. ልዩ ሥነ-ሥርዓት** 38

2.5.1. በአጭር ሁኔታ ስለሚወሰኑ ክርክሮች (summary Procedures) 38

2.5.2. የተፈጠነ ሥነ ሥርዓት (Accelerated Procedure) 39

**2.6. የንግድ ህጉን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ሂደት መቋጫ የጊዜ ስታንድርዶች ወሰንና ተጠባቂ ውጤት ማጠቃለያ (በመቶኛ)** 40

2.6.1. የንግድ ማህበራትን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች 40

2.6.2. ቼክ፣ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች 40

2.6.3. በአጭር ሥነ-ሥርዓት መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮች 41

**2.7. ለጊዜው ስለሚሰጡ ማገጃዎችና ሌሎች ትዕዛዞች (Provisional Remedies)** 41

2.7.1. ከፍርድ በፊት ንብረትን ማስከበር (ቁ 151-153) 41

2.7.2. ለጊዜው የሚሰጥ የማገድ ትዕዛዝ (ቁ 154-159) 42

**2.8. ስለ ፍርድ አፈፃፀም** 42

2.8.1. ፍርድ እንዲፈፀም ስለሚቀርብ ማመልከቻ 42

2.8.2. ፍርድ እንዲፈፀም የሚገደድበት ሁኔታ 43

2.8.3. የፍርድ ባለዕዳውን ስለመመርመር 44

**2.9. የፍርድ አፈፃፀም ሥርዓት** 46

2.9.1. ንብረትን ስለማስከበር 46

2.9.2. በተከበረ ወይም በተያዘ ንብረት ላይ ሦስተኛ ወገኖች የሚያቀርቡት መቃወሚያ 47

2.9.3. ለፍርድ አፈፃፀም ንብረትን የመሸጥ ሥ/ሥርዓት 48

**2.10. ልዩ ልዩ ጉዳዮች (Miscellaneous Issues)** 50

2.10.1. አቤቱታን ስለማሻሻል 50

2.10.2. ስለ ጊዜ አወሳሰንና ስለ ቀጠሮ 50

2.10.3. በኪሳራ ስለሚከፈል ገንዘብ የሚሰጥ ዋስትና 51

2.10.4. ስለወጪና ኪሳራ -

**2.11. ፍርዱን ወይም ትዕዛዙን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ የሚፈፅማቸው ማረሚያዎች ወይም ማስተካከያዎች (Review by Court of Rendition)** 51

2.11.1. ከሥነ–ሥርዓት ውጪ የተፈፀሙ ጉዳዮች 51

2.11.2. ጉዳዩን እንደገና ማየት 51

2.11.3. ስለ መቃወም (Opposition) 52

2.11.4. ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት 53

**ክፍል ሶስት** **53**

**በንግድ ችሎቶች የቀጠሮ ፖሊሲ** **53**

**3.1. የጉዳዮች ሂደት እልባት የሚያገኝበትን ጊዜ ስለመወሰን** 53

3.1.1 በንግድ ችሎቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እልባት ሊያገኙ ስለሚገባቸው ጉዳዮች 54

3.1.2 በንግድ ችሎቶች ቀጠሮ የሚሰጥበት ሁኔታ 55

3.1.3. በንግድ ችሎቶች ተለዋጭ ቀጠሮ ሲሰጥ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ሁኔታዎች 55

3.1.4. የንግድ ችሎት ዳኞች የጉዳዮችን ሂደት ስለሚቆጣጠሩበት ስርዓት 56

**3.2. የባለ ድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት** 56

3.2.1 የፍ/ቤቱ አስተዳደር ተግባር እና ኃላፊነት 56

3.2.2 የችሎቱ ዳኞች ተግባር እና ኃላፊነት 56

3.2.3. የችሎቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተግባር እና ኃላፊነት 57

3.2.4 በተከራካሪ ወገኖች ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት 57

**ክፍል አራት** **59**

**4. በፌደራል መጀመሪያ ፍ/ቤት የንግድ ችሎቶች ተፈፃሚ የሚሆኑ ዋና ዋና የህግ ምንጮች** 59

**1.1 የተለያዩ የአገር ውስጥ ህጎች** **59**

**1.2 በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም የተሰጠባቸው የንግድ ጉዳዮችን የተመለከቱ ውሣኔዎች** 61



# መግቢያ

በአገር አቀፍ ደረጃ በፌዴራል ፍ/ቤቶች እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶችን ለማሻሻል በመከናወን ላይ ከሚገኙ ተግባራት አንዱ ችሎቶችን በጉዳያቸው አይነት በማደራጀት ጉዳዮችን በአፋጣኝ እና ጥራት ባለው መንገድ እልባት ለመስጠት የሚስችል አሰራር መዘርጋት ሲሆን ይህንኑ ለማሳካት በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ጨምሮ የንግድ ጉዳዮችን ብቻ የሚያስተናግዱ ችሎቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ የንግድ ጉዳዮችን ብቻ የሚያስተናግዱ ልዩ ችሎቶች እንዲቋቋሙ ከማድረግ ባለፈ ችሎቶቹና የችሎቶቹ ዳኞች የሚመሩበትን ልዩ ሥርዓተ ችሎት ማዘጋጀት በዘርፉ የታለመውን ውጤት ለማምጣት እንደሚያስችል በኢትዮጵያ የፍርድ ቤቶች መዋቅር ከፍተኛው የስልጣን አካል በሆነው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስተዳደር ታምኖበት ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 16(1) ስር የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ ይህ ስርዓተ-ችሎት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እውቅና እና ፈቃድ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎቶች ሊዘጋጅ ችሏል፡፡

ይህን የንግድ ችሎቶች ሥርዓተ-ችሎት (Commercial Proceedings Code) ማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋና ዓላማ በችሎቶቹ የዕለት ተዕለት ተግባር ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ዳኞች በቀላሉና ሊፈቱ የሚችሉበትን መሪ ማጣቀሻ ለማዘጋጀት፤ ተከራካሪ ወገኖች እና የህግ ባለሙያዎችም በንግድ ችሎቶች የሚታዩ ጉዳዮችን እና ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ህግጋት በቀላሉ መለየት የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ

ለመፍጠር፣ የንግድ ጉዳዮችን የተመለከቱ ክርክሮች መደበኛውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ተከትሎ ወጪ ቆጣቢ፣ ፈጣን እና ጥራት ባለው መንገድ በልዩ ሁኔታ የሚታዩበትን እድል ለማመቻቸት እንዲሁም በንግድ ችሎቶች ወጥነት ያለው የህግ አተረጓጎም፣ የችሎት ሥነ ሥርዓት አተገባበር እና ቀጠሮ አሰጣጥ እንዲኖር ለማስቻል በማሰብ ነው።

ይህ ሥርዓተ-ችሎት አራት ዋና ዋና ክፍሎችን የያዘ ሆኖ የመጀመሪያው ክፍል በንግድ ችሎቶች የሚታዩ ጉዳዮችን ዓይነት በዝርዝር የያዘ ሲሆን በችሎቶቹ የሚታዩ ጉዳዮች ህጋዊ መሠረታቸው ምን እንደሆነ፣ የመብት ጥያቄዎቹ በማን እና በምን ሁኔታ ሊቀርቡ እንደሚገባ በአጭሩ ተብራርቷል። ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች የገንዘብ ግምታቸውን መሠረት በማድረግ የተሰጣቸው የዳኝነት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ችሎቶች ከንግድ ተቋማት እና ከንግዱ ማህበረሰብ የእለት ተለት የንግድ እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ነገር ግን በውጤታቸው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አንድምታ ያላቸው ክርክሮች የሚታይባቸው ችሎቶች በመሆናቸው ይህን የችሎቶቹን ልዩ ባሕሪይ ታሳቢ በማድረግ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎችን በዚሁ ክፍል ላይ ለመዳሰስ ተሞክሯል።

የንግድ ጉዳዮችን የተመለከቱ ክርክሮች እንደማንኛውም ፍትሐብሔራዊ ጉዳይ ለጉዳዮች እልባት በመስጠት ሂደት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህጉን የሚተገብሩ ሲሆን የንግድ ችሎቶች ከባሕሪያቸው አኳያ ጉዳዮችን ለማየት የሚከተሉት ልዩ ስነ- ስርዓት በስርዓተ ችሎቱ ክፍል ሁለት ላይ በዝርዝር ተመልክቷል። ይህ የሥርዓተ-ችሎቱ ክፍል በአመዛኙ በፍ/ቤቶች ማሻሻያ ፕሮጀክት እና በፍትህ አካላት ስልጠና ማዕከል ትብብር በ1997 ዓ.ም ከተዘጋጀው "የፍትሐብሔር ክርክሮች ሥርዓተ ችሎት" ላይ የተወሰደ ሲሆን በንግድ ችሎቶች ከሚታዩ ጉዳዮች ልዩ ባህሪይ አኳያ የተጨመሩ ነጥቦችን እና በችሎቶቹ የጉዳዮችን ሂደት ለመቋጨት የሚያስፈልገውን የጊዜ ስታንዳርድ አካቷል።

የሥርዓተ ችሎቱ ሶስተኛ ክፍል በንግድ ችሎቶች የሚተገበሩ የቀጠሮ ፖሊሲዎችን የሚመለከት ሲሆን በቀጠሮ አሰጣጥ ረገድ የችሎቱ ዳኞች ምን የተለየ ስርዓት መከተል እንደሚገባቸው እንዲሁም የቀጠሮ ፖሊሲ አተገባበር ላይ የባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት ምን ሊሆን እንደሚገባው ተብራርቷል። ይህ ክፍል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል ካዘጋጀው ረቂቅ "የፌደራል ፍ/ቤቶች የፍትሐብሔር እና መሠል ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ትግበራ መመሪያ" ላይ ለንግድ ችሎቶች አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች በመውሰድ እና ሌሎች ከችሎቶቹ ልዩ ባህሪይ አኳያ በቀጠሮ አሰጣጥ ሂደት ሊተገበሩ የሚገባቸውን ነጥቦች በማካተት የተዘጋጀ ነው።

የስርዓተ-ችሎቱ መጨረሻ ክፍል የንግድ ጉዳዮችን የተመለከቱ ዋና ዋና ህግ ምንጮችን እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በንግድ ጉዳዮች ላይ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸውን አብዬት ውሣኔዎች በአባሪ መልክ የያዘ ሲሆን የንግድ ጉዳዮችን የተመለከቱ ህግጋትን በቀላሉ ለማግኘት እንደሚያግዝ ይታመናል፡፡

የዚህ ሥርዓተ-ችሎት ዋና መሠረቶች በዋነኝነት የንግድ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መሠረታዊ ህጎች፤ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ፤ በንግድ ችሎቶች ለሚታዩ ጉዳዮች የተሰጠውን ልዩ ትኩረት ተከትሎ የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲሁም በችሎቶቹ የዳበሩ የአሰራር ተሞክሮዎች ሲሆኑ በንግድ ችሎቶች ከሚታዩ ጉዳዮች ልዩ ባሕሪይ አኳያ በመሰረታዊ ህጎቹም ሆነ በስነ-ስርዓት ህጉ አተገባበር ላይ ማብራሪያ የሚሹ ጉዳዮችን በመጠኑ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ በሕጉ የተሸፈኑ ሆነው ነገር ግን በአተርጓጎምና በአተገባበር ረገድ ልዩነት የሚታይባቸውን የተወሰኑ ስነ-ስርዓታዊ ሂደቶችን በተመለከተ በተቻለ መጠን ልዩነቶቹ የሚጠቡበትን እና ሕጎቹ ወጥነት ባለው መልኩ የሚተገበሩበትን አቅጣጫ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡





# ክፍል አንድ

## በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎቶች የሚታዩ ጉዳዮች ዓይነት

### 1.1 ከንግድ ማህበራት ባለ አክሲዮንነት መብት ጋር የተያያዙ የመብት ጥያቄዎች

#### 1.1.1 የንግድ ማህበራት መፍረስን ተመለከቱ ክርክሮች

የንግድ ማህበራት በፍ/ቤት ውሣኔ አማካኝነት እንዲፈርሱ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ እና ማህበራቱ እንዲፈርሱ የሚወሰነውም ከማህበርተኞች አንዱ ወይም የተወሠኑ ማህበርተኞች ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሠው የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ጥያቄ /ክስ/ ሲያቀርብ ስለመሆኑ በንግድ ህግ ቁጥር 218/1/2/፣ 258/1/፣ 278/1/ረ/፣ 303፣ 495/1/ሠ/3/፣ 542/1/፣ 543/2/ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄዎች በንግድ ችሎቶች ከሚታዩ እና ውሳኔ ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች መካከል ናቸው፡፡

### 1.1.2 የንግድ ማህበራት መፍረስ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች /Dispute During Disolution process/

አንድ በህግ አግባብ የተቋቋመ የንግድ ማህበር በተለይም ኃላፊነታቸው የተወሠነ የንግድ ማህበሮች /Limited liability company/ ማለትም አክሲዮን ማህበር /Share company/ እና የተወሠነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር /Private Limited company/ እንዲሁም ሌሎች የንግድ ማህበራት እንዲፈርሱ ውሳኔ መሰጠቱን ተከትሎ የመፍረስ ሂደቱ ሲከናወን፤ የመፍረስ ሂደቱን የማጠናቀቅ ስራው ከሚያስከትለው ኃላፊነት አኳያ፤ ለሶስተኛ ወገኖች ሊደረግላቸው ከሚገባው ጥበቃ አንፃር እና ከባለ አክሲዮኖች መብት እና ጥቅም አንፃር ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ በመሆኑ የማህበር መፍረስ ሂደቱን በማከናወን ሂደት የሚስተዋሉ ችግሮች ካሉ እንዲስተካከሉ፤ ሂደቱ ላይ እክል የሚፈጥር አካል ካለ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ እና ሌሎች በመፍረስ ሂደቱ ዙሪያ ጠቃሚ የሆኑ ተጨማሪ ትዕዛዞች እንዲሰጡ ለፍ/ቤት አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል።

### 1.1.3. የንግድ ማህበራት ሂሳብ መጣራት እና ከሂሳብ አጣሪ መሾም ጋር የተያያዙ ክርክሮች

አንድ የንንግድ ማህበር ባለ አክሲዮን የሆነ ሰው በህግ የተሰጡት የተለያዩ መብቶች ያሉ ሲሆን ማህበርተኛው በህግ ከተሰጡት መብቶች አንዱ የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ ገቢውን እና ወጪውን የማወቅ መብት ነው። ማህበርተኛው በዚህ መብቱ መጠቀም ይችል ዘንድ ደግሞ በየአመቱ የማህበሩ ሂሣብ እየተመረመረ የሒሣብ ሪፖርቱ እንዲቀርብ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ ከን/ህ/ቁ 345፣ 381፣ 389፣ 538 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል። ማህበርተኛው በማህበሩ ውስጥ ያለው ይህ መብት ካልተከበረለት መብቱ ይከበርለት ዘንድ ሂሳብ አጣሪ ካለ ባለሙያው ሂሳብ እዲያጣራ ወይም ሂሳብ አጣሪ እንዲሾምና የሂሳብ መጣራቱ ውጤት የሚያስገኘለትን መብት እንዲከበርለት ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

### 1.1.4 በሂሳብ መጣራት ሂደት የሚቀርቡ ክርክሮች /Dispute during Liquidation/

አንድ በህግ አግባብ የተቋቋመ የንግድ ማህበር ማለትም ኃላፊነታቸው የተወሠነ የንግድ ማህበሮች እና ሌሎች የንግድ ማህበራት ሂሳባቸው እንዲጣራ ወይም ማህበራቱ እንዲፈርሱ ውሳኔ መሰጠቱን ተከትሎ ሂሳብና ንብረት ሲጣራ የሂሳብ ማጣራት ስራው በህጉ፣ በሂሳብ አሰራር ድንብ እና በአግባቡ የተጣራ ስለመሆኑ የማህበሩ ሂሳብ መጣራት ከሚያስከትለው የኃላፊነት ወሠን አኳያ፤ ለሶስተኛ ወገኖች ሊደረግላቸው ከሚገባው ጥበቃ አንፃር እና ሂሳብና ንብረት መጣራቱን ተከትሎ ለባለ አክሲዮኖች የሚደርስ ድርሻ ካለ ሂሳቡ ሲጣራ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ በመሆኑ በባለሙያ ተሰርቶ በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ላይ

ተከራካሪ ወገኖች አስተያየት እንዲሰጡና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሂሳብ ባለሙያው ማብራሪያ እንዲሰጥ ከተደረገ በኋላ የኦዲት ሪፖርቱ ሊፀድቅ፤ ሊሻሻል አልያም እንደገና እንዲሰራ ሊታዘዝ ይችላል።

### 1.1.5 የሂሳብ ማጣራትን ተከትሎ ከትርፍ ደርሻ ክፍፍል ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ክርክሮች

የንግድ ማህበር ሒሣብ በሂሳብ ባለሙያ ከተጣራና ትርፍና ኪሣራው ተለይቶ ታውቆ፤ ሪፖርቱ በፍ/ቤት ከፀደቀ በኋላ የማህበር አባል (ባለአክሲዮን) የሆነ ሰው ከትርፍ ሊደርሰው የሚገባውን የድርሻ ክፍያ በመለየት ክፍያ እንዲፈፀምለት መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 82503 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን ከትርፍ ድርሻ ክፍፍል ውጪ በሆኑ የኦዲት ሪፖርትን ውጤት መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ደግሞ ሪፖርቱን መነሻ በማድረግ ተገቢው ዳኝነት ተከፍሎ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት ይችላል።

### 1.1.6 ከስራ አስኪያጅ መሻር እና ከንግድ ማህበራት አስተዳዳሪዎች ተጠያቂነት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮች

አንድ በህግ አግባብ የተቋቋመ የንግድ ማህበር በተለይም ኃላፊነታቸው የተወሠነ የንግድ ማህበር ስራ አስኪያጅ ሆኖ የተመረጠ ሠው በፍ/ቤት ውሣኔ አማካኝነት ከስራ አስኪያጅነት እንዲሻር ሲወሠን የሚችል ስለመሆኑ በን/ህ/ቁ 527/2/ /5/ ስር የተመለከተ ሲሆን በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ ባለአክሲዮን የሆነ ሠው ባለአክሲዮን በሆነበት ማህበር ውስጥ በህግ ከተረጋገጡለት የተለያዩ መብቶች ውስጥ አንዱ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የተሾመው ሠው ከየስራ አስኪያጅነት ስልጣኑ እንዲሻር ለፍ/ቤት ጥያቄ /ክስ/ ማቅረብ ስለመሆኑ በን/ህ/ቁ 525/5/ ስር ተመልክቷል።

በሌላ በኩል የአንድ አክሲዮን ማህበር የቦርድ አባላት በህግ፤ በማህበሩ መመመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው የማህበሩን ሃብትና ገንዘብ ካባከኑ፤ አስተዳዳሪዎቹ በፈፀሙት ያልተገባ ተግባር ምክንያት በማህበሩ፤ በባለ አክሲዮኖች፤ በገንዘብ ጠያቂዎች እና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት እና ኪሣራ ያደረሱ ከሆነ፤ ጉዳዩም ለጠቅላላ ጉባኤ ደርሶ ጠቅላላ ጉባኤ በቦርድ አባላቱ ላይ ክስ እንዲቀርብ ከወሰነ እንዲሁም በቦርድ አባላቱ ጥፋት ወይም የማጭበርበር ተግባር ምክንያት በባለ አክሲዮን ወይም በሶስተኛ ወገን ላይ በቀጥታ የደረሰ ጉዳት ከደረሰ አክሲዮን ማህበሩም ሆነ ሌሎች ጉዳት የደረሰባቸው አካላት በቦርድ አባላቱ ላይ ክስ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ በን/ህ/ቁ 364፤ 365፤ 366 እና 367 ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል።

### 1.1.7 ከተጠባባቂ ስራ አስኪያጅ መሾም ጋር የተያዙ ክርክሮች

የንግድ ማህበራት በአጠቃላይ፤ በተለይም የተወሠነ ኃላፊነት ያላቸው የንግድ ማህበራት /Limited Liability Company/ የተቋቋሙበትን ዓላማ ማሳካት ያስችላቸው ዘንድ የንግድ ማህበሩ በአስተዳዳሪ ሊኖራቸው እንደሚገባ በን/ህ/ቁ 347፣ 528፣ ስር በአስገዳጅነት የተመለከተ ሲሆን የማህራቱም ስራ አስኪያጆች በተለያዩ ምክንያቶች የስራ አስኪያጅነት ተግባራቸውን ማከናወን የማይችሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ፤ አባላቱ ስራ አስኪያጅ ለመሾም የማይችሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ፤ የንግድ ማህበሩን ህልውና በማስቀጠል በማህበሩ፤ በአባላት እና በሶስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል ሲባል ጊዜአዊ ስራ አስኪያጅ መሾም ካስፈለገ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 308 መሠረት ተጠባባቂ ስራ አስኪያጅ እንዲሾም አቤቱታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል።

### 1.1.8 ከቃለ ጉባኤዎች መሠረዝ እና ከቃለ ጉባኤ አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ክርክሮች

አንድ የንግድ ማህበር የተቋቋመበትን ዓላማ ማሳካት ያስችለው ዘንድ ጉባኤዎችን በማድረግ፣ በጉባኤዎች ላይ አጀንዳዎችን ይዞ በመምከር ውሣኔዎችን ማሳለፍ የሚችል ሲሆን የንግድ ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ የሚያስተላልፈው ውሳኔ ሁሉንም አባላት የሚያስገድድ እንደመሆኑ መጠን አባላት በስብሰባው በመሳተፍ በሚተላለፈው ውሳኔ ላይ ድምፅ የመስጠት እና የመቃወም መብት አላቸው። ሆኖም ግን የባለ አክሲዮኖችን መብት እና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ህግን፤ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና መመስረቻ ጽሑፍን መሠረት ያላደረገ ቃለ ጉባኤ ከተደረገ በጉዳዩ ጥቅም ያለው ሰው ቃለ ጉባኤውን በመቃወም ክስ ሲያቀርብ በፍ/ቤት የጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔ እንዲሠረዝ ሊወሰን እንደሚችል በን/ህ/ቁ 416 /2/ /3/ ስር ተመልክቷል።

የንግድ ማህበር ባለ አክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባኤ በተላለፉ ውሳኔዎች ላይ የተጠበቁላቸው መብቶች ሳይከበሩ ቢቀሩ ወይም ባለ አክሲዮነኖች ጠቅላላ ጉባኤው ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ሳይፈፅሙ ቢቀሩ ባለ አክሲዮኖቹ በቃለ ጉባኤው ላይ በተላለፈው ውሳኔ መሠረት ይፈፀም ዘንድ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ክስ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን አክሲዮን ማህበሩም በውሣኔው ግዴታውን ያልተወጣ አባል ላይ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰደው ሌላ ህጋዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለ አክሲዮኑ ተገዶ እንዲፈፅም ክስ ሊያቀርብ ይችላል ይችላል።

### 1.1.9 በንግድ ማህበራት ላይ የመክሠር ፍርድ እንዲሰጥ

በህግ አግባብ የተቋቋመ የንግድ ማህበር ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ማሳካት ካልቻለ ማለትም ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ የገባውን ግዴታ መፈፀም ካልቻለ

ወይም በገባው ግዴታ መሠረት የተቀበለውን እና ያለበትን እዳ መመለስ ወይም መክፈል ካልቻለ ወይም እዳውን መክፈል ካቋረጠ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በማህበሩ ላይ የመክሰር ፍርድ እንዲሰጥ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት የማስታወቅ ግዴታ እንዳለበት፤ ከስራ አስኪያጁም በተጨማሪ ከነጋዴው ላይ ገንዘብ የሚጠይቅ ሠው በፍ/ቤት የመክሰር ውሣኔ እንዲሰጥ ክስ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ በን/ህ/ ቁጥር 972 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡

### 1.1.10 የመጠባበቂያ ስምምነት ሥነ- ስርዓት እንዲከፈት

በህግ አግባብ የተቋቋመ የንግድ ማህበር ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ የገባውን ግዴታ መፈፀም ካልቻለ ወይም በገባው ግዴታ መሠረት የተቀበለውን እና ያለበትን እዳ መመለስ ወይም መክፈል ካልቻለ ወይም እዳውን መክፈል ካቋረጠ ኩባንያው እዳውን በመክፈል ጤናማ የብድር አከፋፈል እና የማህበሩ ስራ የተሻለ የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር የኩባንያው ስራ አስኪያጅ ለንግድ ድርጅቱ የመጠበቂያ ስምምነት ስነ-ስርዓት እንዲጀመር ስልጣን ላለው ፍ/ቤት የማስታወቅ ግዴታ እንዳለበት ከን/ህ/ቁ 972 ድንጋጌ የተመለከተ ሲሆን ይህን ዓይነት ማመልከቻ በማናቸውም እዳውን መክፈል ባቋረጠ ነጋዴ ሊቀርብ የሚችል ስለመሆኑ እና የመጠባበቂያ ስምምነት ስነ ስርዓት እንዲከፈት ለፍ/ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ምን ዓይነት ሁኔታዎች መሟላት እንደሚገባቸው በን/ህ/ቁ በን/ህ/ቁ 1019፤ 1020፤ 1021/3/(ለ) እና 973 ስር ተመልክቷል፡፡

### 1.1.11 በመክሠር ስነ- ስርዓት ሂደት ወቅት የሚቀርቡ ክርክሮች /Bankruptcy Proceedings/

በአንድ ነጋዴ /የንግድ ማህበር/ ላይ የመክሰር ፍርድ ከተሠጠ በኋለ የተለያዩ ተግባራት የሚፈፀሙ እና መፈፀም እንዳለባቸው ከን/ህ/ቁ 977 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ከነዚህ ተግባራት መካከል ዋናዎቹ ማህበር የኪሣራ ሰርዓቱን የሚመረምር መርማሪ ዳኛ /commissioner/ እና ንብረት ጠባቂ /trustee/ መሾም፤ የገንዘብ ጠያቂዎች ኮሚቴ ማቋቋም እና የከሠረው ኩባንያ እዳ መክፈል ያቋረጠበትን ቀን መወሰን ይገኙበታል፡፡ የመክሰር ስነ ስርዓትቱን የሚያስፅሙት አካላት በፍ/ቤት ከተሾሙ /ከተመረጡ/ በኋላ ምን ምን ተግባር መፈፀም እንደሚገባቸው በን/ህ/ቁ 989 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን በመክሰር ሂደቱ በመርማሪ ዳኛ በሚሰጡ የሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች፤ የመክሰር ፍርድ በሰጠው ችሎት በቀጥታ በሚታዩ ጉዳዮች እና የመክሠር ስነ ስርዓት ሂደቱን ለማከናወን በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ የሚቀርቡ ማናቸውም አቤቱታዎች በንግድ ችሎቶች አቤቱታ ሲቀርብባቸው እንደየ አግባብነታቸው የሚስተናገዱ ይሆናሉ፡፡

### 1.1.12 የንግድ ማህበር ባለ አክሲዮኖች በፈቃዳቸው እና ተገደው ከማህበር አባልነት አባልነት ሲወጡ የሚቀርቡ ክርክሮች

የንግድ ማህበር አባላት በህግ፣ በማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በጊዜው እና በአግባቡ መፈፀም ሲኖርባቸው ካልፈፀሙ በዚህ ምክንያትም በማህበሩ ስራ ስራ ላይ ጉዳት ከደረሰ ወይም ሌላኛው ማህበርተኛ በማህበሩ ውስጥ ያለውን መብት መጠቀም ካልቻለ፤ በዚህ ምክንያት በሌሎች የማህበሩ አባላት ጉዳት እንዳይደርስ እና የማህበሩ መደበኛ ስራ እንዳይስተጓጎል በመፍትሔነት ከተቀመጡ አማራጮች አንዱ ግዴታውን ያልተወጣው ወይም በመብቱ መጠቀም ያልፈለገው አባል ከማህበሩ እንዲወጣ ማድረግ ሲሆን የንግድ ማህበራት ባለ አክሲዮኖች እንደየ ማህበራቱ ዓይነት እና የባለ አክሲዮኖች ቁጥር እንዲሁም ከንግድ ማህበራቱ መተዳደሪያ ደንብ አኳያ ድርሻቸው ተሰጥቷቸው ከማህበር አባልነት ለመውጣት መጠየቅ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ የሽርክና ማህበራትን በተመለከተ በቂ ምክንያት ሲኖር ከማህበሩ አባላት መካከል አንዱ ከአባልነት እንዲወጣ በፍ/ቤት ሊወሰን እንደሚችል በን/ህ/ቁ 261 ስር የተመለከተ ሲሆን አክሲዮን ማህበር እና ሽርክና ማህበርን አስመልክቶ ማህበሩ እንዲፈርስ ጥያቄ የሚያቀርብ ሽሪክ ወይም አባል ሲኖር እንዲፈርስ የጠየቀው አባል ድርሻው ተሰጥቶት ከማህበር አባልነት እንዲወጣ በማድረግ የማህበሩን ህልውና ማስቀጠል የሚቻል ስለመሆኑ ከን/ህ/ቁ 261፤ 258፤ 259፤ እና 511 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል።

### 1.1.13 ከጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮች

በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ ባለአክሲዮን የሆነ ሠው በዚህ ባለአክሲዮን በሆነበት ማህበር ውስጥ በህግ የተረጋጠለት የተለያዩ መብቶች ያሉት ሲሆን ማህበርተኛው በህግ ከተረጋገጡለት መብቶች አንዱ በስብሰባ የመካፈል መብት ነው። ይህን በን/ህ/ቁ 406፣ 447፣ 537 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። የንግድ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የመጥራት ግዴታ ያለበት በሆነ ጊዜ ማህበርተኛው የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ ማወቅ ይችል ዘንድ ደግሞ የማህበሩ አስተዳዳሪዎች የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት የሚጠበቅባቸው ሲሆን አስተዳዳሪዎች በተሰጣቸው ስልጣን እና ኃላፊነት መሠረት ይህን ግዴታቸውን ካልተወጡ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ለመጠየቅ ህጉ የሚጠይቀውን አነስተኛ ድምፅ የሚያሟላ ማህበርተኛ በህግ የተሠጠው መብቱ ተግባራዊ ይሆንለት ዘንድ የማህበሩ ጉባኤ እንዲጠራ መጠየቅ ይችላል።

### 1.1.14 የንግድ ማህበራትን የትርፍ ድርሻ ለመካፈል፣ ሠነዶችን የመመልከት እና የመመርመር፣ የባለ አክሲዮንነት ሠርተፊኬት እንዲሰጥ እና ሌሎች የአክሲዮን ማህበር አባልነት መብቶች እንዲከበሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ ባለአክሲዮን የሆነ ሠው በዚህ ባለአክሲዮን በሆነበት ማህበር ውስጥ በህግ የተረጋጠለት የተለያዩ መብቶች ያሉት ማህበርተኛው በህግ ከተረጋገጡለት መብቶች አንዱ ስለማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ የማወቅ፣ ትርፍ ካለም የመካፈል እና በንግድ ማህበሩ ለሌሎች ባለ አክሲዮኖች የተከበሩ መብቶች ሁሉ ለእርሱም እንዲከበሩለት የመጠየቅ መብት ነው። የማህበሩን እንቅስቃሴ ማወቅ የሚያስችሉ ሰነዶችን ለመመልከት እና ግልባጭ ለማግኘት ያልቻለ ባለ አክሲዮን ወይም ማናቸውም የማህበር አባልነት መብቱን የተነፈገ አባል ሰነዶችን ለመመከት፣ የትርፍ ድርሻ እንዲከፈለው አልያም ማናቸውም ሌላ መብቱ እንዲከበርለት በፍ/ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል።

### 1.1.15 በንግድ ማህበራት የባለ አክሲዮንነት መብት ላይ የሚፈጠር ሁከት ወይም ህገወጥ ተግባር ለማስቆም የሚቀርቡ ክርክሮች

በአንድ የንግድ ማህበር ባለ አክሲዮን የሆነ ሰው በህግ፣ በመተዳደሪያ ደንብ እና በመመስረቻ ጽሑፍ በተረጋገጡለት መብቶች እንዳይጠቀም ክልከላ ከተደረገበት ወይም ሌላ ማናቸውም የባለ አክሲዮንነት መብቱን መጠቀም እንዳይችል የሚያደርግ ሁከት ነክ ተግባር ቢፈፀምበት ይህ ባለ አክሲዮን ክልከላው እንዲቆመም፣ የሁከት ድርጊቱ እንዲወገድ ወይም መብቱ መብቱ እንዲከበርለት ለፍ/ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል።

## 1.2 ከሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች

በህግ እንደሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ከሚቆጠሩት መካከል የንግድ ወረቀቶች ዋነኞቹ ሲሆኑ ከነዚህ የንግድ ወረቀቶች መካከል ደግሞ ቼኮች በተለይም መደበኛው ቼክ እና የተስፋ ወረቀቶች ከሌሎች ሰነዶች በተለየ ሁኔታ በአገራችን የእለት ከእለት የሰዎች የንግድ እንቅስቃሴ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ከመሆናቸው አንጻር ሁለቱን የንግድ ወረቀት አይነቶች አስመልክቶ በፍ/ቤቶች የመብት ጥያቄዎች በስፋት ይስተዋላሉ። ከዚህም በመነሣት ሁለቱን የንግድ ወረቀቶች የተመለከቱ የመብት ጥያቄዎች በፍ/ቤት የሚቀርቡበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች ባሉት ክፍሎች ተመልክቷል።

### 1.2.1 የተስፋ ወረቀቶች /ሠነዶች/

የቃል ኪዳን ሠነድ /Promissory note/ በንግድ ህጉ እንደ ንግድ ወረቀት ይቆጠራሉ ተብለው በን/ህ/ቁ 732/2/ ስር ከተዘረዘሩት የንግድ ወረቀቶች / Commercial instruments/ ውስጥ አንዱ ሲሆን የተስፋ ሠነድ አውጪ ሠነዱን ፈርሞ ሲያወጣ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በሠነዱ ላይ እከፍላለሁ ብሎ ቃል የገባበትን ገንዘብ የመክፈያው ጊዜ ሲደርስ ለሠነዱ አምጪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት። የተስፋ ሠነድ አውጪው በገባው ግዴታ መሠረት ገንዘቡን በተጠቀሰው ጊዜ ሳይከፍል ከቀረ የሠነዱ አምጪ ገንዘቡ እንዲከፈለው መጠየቅ የሚችል ስለሆኑ ከን/ህ/ቁ 780፣ 825/1//ለ//ሐ/ 826 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል።

### 1.2.2 ቼክን የተመለከቱ ክርክሮች

ከንግድ ወረቀቶች መካከል ገንዘብን ተክቶ በተግባር ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኙት ቼኮች ሲሆኑ በህጉ ላይ ከተመከቱ የቼክ ዓይነቶችም መደበኛው ቼክ በዋነኝነት ይጠቀሳል። ቼክ እንደቀረበ የሚከፈልበት የንግድ ወረቀት ስለመሆኑ በን/ህ/ቁ 854 ስር የተመለከተ ሲሆን የቼኩ አምጪ /Drawee/ ቼኩን ለክፍያ ለከፋዩ ባንክ /Payee/ አቅርቦ ቼኩ ሳይከፈልበት ከተመለሰ የቼኩ አውጪ / Drawer/ ስለ ቼኩ አከፋፈል ዋስ በመሆኑ እና ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ የቼኩ አውጪ እንዲከፍለው መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በን/ህ/ቁ 840 ፣ 868 ፣ 881 /1/ ስር የተመለከተ ሲሆን ይህንኑ መነሻ በማድረግ ቼክ አምጪው ገንዘቡ እንዲከፈለው በአውጪው ላይ በፍ/ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል።

## 3. ከግልግል ዳኞች ጉባኤ መቋቋም ጋር የሚቀርቡ አቤቱታዎች

### 3.1 የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንዲቋቋም የሚቀርቡ አቤቱታዎች

ተዋዋይ ወገኖች ባደረጉት ውል ላይ ውሉን ተከትሎ በመካከላቸው ወደፊት አለመግባባት ቢፈጠር ይህ አለመግባባት በአማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ ታይቶ መፈታት እንዳለበት በመስማማት ካስቀመጡ በኋላ አለመግባባት ቢፈጠር፤ ይህ አለመግባባት መታየት እና መፈታት ያለበት በውሉ ላይ በተቀመጠው አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ መሆን ይገባዋል። በዚህም መሠረት በውሉ ላይ የተቀመጠው አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ በግልግል ዳኝነት ታይቶ መወሠን እንዳለበት ከተቀመጠ አንደኛው ተዋዋይ ወገን ውሉን መሠረት በማድረግ አለመግባባቱን ተመልክቶ የሚፈታው የግልግል ዳኞች ጉባኤ እንዲሠየም ለፍ/ቤቱ ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል።

### 3.2 በጊዜአዊነት ለሚቋቋሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዎች የማህተም አገልግሎት ለማግኘት

ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠረውን አለመግባባት እንዲፈታ በመረጡት አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ የተቋቋመ ጉባኤ ግዜኢዊ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ /Adhoc- Arbtration Panel/ በሚሆንበት ጊዜ ጉባኤው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በክርክር ሂደት ለውሳኔው ግብዓት የሚሆኑ ማስረጃዎችን በማሰባሰብም ሆነ እንደ ዳኝነት አካል ሌሎች አስገዳጅነት ያላቸውን ትዕዛዛት በሚሰጥበት ወቅት የሚሰጣቸው ትዕዛዞች ላይ የፍ/ቤት ካልታገዘ ለአፈፃፀም መሆኑ አያከራክርም። ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ ጉባኤ ተቋቁሞ የሚሰጠውን ውሳኔ ተቀብሎ እንደማንኛውም በፍ/ቤት እንደተሰጠ ውሳኔዎች እንደሚያስፈፅመው ሁሉ ከዋናው ጉዳይ ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ትዕዛዞች በመስጠት ወይም ጉባኤው በሚሰጣቸው ትዕዛዞች ላይ ማህተም እንዲያርፍበት በማድረግ ግልግል ተቋማት ውሳኔዎች ብቻ ሳይሆን ትዕዛዞችም ተፈፃሚነት ተቋማዊ ድጋፍ ቢደረግ የስነ ስርዓት ህጉን ዓላማ ከማሳካት አኳያ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ስለሚታመን የማህተም አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል አቤቱታ ሲያቀርቡ በዚህ ችሎት ይስተናገዳሉ።

### 3.3 በጊዜአዊነት ለሚቋቋሙ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዎች ተጨማሪ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች

ከላይ በተራ ቁጥር 3.2 ላይ በተገለፀው መልኩ ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠረውን አለመግባባት እንዲፈታ የመረጡት አማራጭ የሙግት መፍቻ ግዜኢዊ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ /Adhoc- Arbitration Panel/ ሲሆን ጉባኤው ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በክርክር ሂደት ተከራካሪ ወገኖች የፍ/ቤት እገዛ የሚያስፈልግበት ጉዳይ ሲኖር የትዕዛዝ ማስጠት ፋይል በማስከፈት ተጨማሪ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

### 4. በንግድ ህጉ ላይ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እና ሌሎች ከንግድ ህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ህጎች መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች

ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተመለከቱት የመብት ጥያቄዎች የንግድ ህጉ ላይ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረጉ ሲሆኑ ከላይ የተዘረዘሩት የመብት ጥያቄዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የንግድ ህጉን፣ የንግድ ህጉን መሠረት አድርገው የወጡ ህጎችን እና ከንግድ ህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ህግጋት መሠረት ያደረጉ የመብት ጠያቄዎችም እንደየ አግባብነታቸው በንግድ ችሎቶች ይታያሉ። ለአብነት ያህልም የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008፣ የንግድ ምልክት ምዝገባ እና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 ን

መነሻ በማድረግ የንግድ ምልክት ጥበቃ መብት ጥሰትና ደንበኞችን በሃሰተኛ ምርት የማደናገር ተግባር ሲፈጸም መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስ፤ የንግድ ስራ ፍቃድ አላግባብ ሲታገድ እና በህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት በተቋቋሙ የህብረት ስራ ማህበር አባላት የሆኑ ሰዎች የማህበር አባልነት መብታቸውን ለማስከበር በፍ/ቤት የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችን መጥቀስ ይቻላል።

5. **ግምታቸው እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) የሆኑ የውል ግንኙነቶችን መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄዎች የንግድ ህጉን እና ተያያዥ ህግጋትን መሠረት አድርገው በንግድ ችሎቶች ከሚታዩ ጉዳዮች እና ከሚቀርቡ መብት ጥያቄዎች ባሻገር ከንግድ ህጉ ውጪ ያሉ የሆኑ የእለት ከለት የንግድ እንቀስቃሴዎች መሠረት ያደረጉ የውል ግንኙነትን መሠረት ያደረጉ እንደ የሽያጭ ውል የገንዘብ ብድር ውል እና የተለያዩ የገንዘብ ክፍያ መተማመኛ ሠነዶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በንግድ ችሎቶች ይታያሉ።**



# ክፍል ሁለት

## በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድ ችሎቶች የስነ-ስርአት ህግ አተገባበርና የጉዳዮች ፍሰት የጊዜ ስታንዳርድ

### 2.1. ክስ ከመሰማቱ በፊት ያሉ ሂደቶች (pre-trial stages)

#### 2.1.1. የክስ ማመልከቻን ስለመመርመር

ሀ. ክስ የሚጀመረው የክሱን ምክንያት የሚገልፅ አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ነው (ቁ.213(1))።

ለ. የክስ ማመልከቻ መጀመሪያ የሚቀርበው ለሬጅስትራር ሲሆን ማመልከቻው በሶፍት ኮፒም ጭምር መቅረብ አለበት። ሬጅስትራሩ የክስ ማመልከቻው የፍ/ሥ/ሥርዓት ሕግ አንቀፅ 80-93 እና 222-228 በሚያዘው መሠረት ፎርሙን አሟልቶ መቅረቡን ከመረመረ በኂላ በአንቀፅ 229 መሠረት ውድቅ ሊያደርገው ወይም በአንቀፅ 230 መሠረት ሊቀበለው ይችላል።

ሐ. ሬጅስትራሩ የክስ ማመልከቻውን ከተቀበለ በቁጥር 214 መሠረት ማመልከቻውን በፍትሐብሔር ክስ መመዝገቢያ ደብተር ውስጥ ይመዘግባል።

መ. ሬጅስትራሩ/ሯ/ የክስ አቤቱታው በትክክል የቀረበ መሆኑን ተቀብሎ ለችሎቱ

ሲያስተላልፍ ፍርድ ቤቱም በቁጥር 231 መሠረት የክስ ማመልከቻውን ይመረምራል፡፡

ሠ. በቁጥር 231 (1) (ሀ) እና (ለ) እንዲሁም (2) ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ክሱን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን በተመለከተ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 (ከነማሻሻያዎቹ) መሠረት ይታያል፡፡

ረ. በቁጥር 229 ወይም በ231 መሠረት የክስ ማመልከቻው ወድቅ መሆን የሚያስከትለው ውጤት በቁጥር 232 መሠረት ይታያል፡፡ እ

ሰ. ፍርድ ቤቱ በቁጥር 231 መሠረት ክሱን ውድቅ ካላደረገውና ከተቀበለው የክስ ማመልከቻውን (ከማንኛውም አስረጅና የጽሑፍ ግልባጭ ጋር አያይዞ) ከመጥሪያ ጋር ለተከሳሹ እንዲደርስውና የመከላከያ መልሱን ፅፎ እንዲያቀርብ ያዛል (ቁ.233)

የክስ ማመልከቻን ለመመርመር የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ

- ✓ ክስ ለመመርመር የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ጊዜ፡- አንድ ቀን
- ✓ ክስ ለመመርመር የሚስፈልገው ከፍተኛ ጊዜ፡- አምስት ቀናት

### 2.1.2. ለተከሳሽ መጥሪያ መላክ

ሀ. መጥሪያ ለተከሳሹ የሚላከው ከቁ.94 እስከ 110 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ሲሆን የችሎቱ ዳኛ መጥሪያ አድራሹ ተገቢውን ትጋት ማድረጉን መቆጣጠር አለበት፡፡

ለ. የክሱ አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ በቀረበ ጊዜ ወዲያው ተከሳሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ያመነ እንደሆነ መጥሪያ መላክ አስፈላጊ አይደለም (ቁ.94 (1)) ፡፡

ሐ. መጥሪያው ላይ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ላይ ይጠቀሙኛል ሲል የዘረዘራቸውን ሰነዶች ሁሉ ይዞ እንዲቀርብ መገለፅ አለበት (94(2))፡፡

መ. ተከሳሾች ብዙ በሆኑ ጊዜ የአሰጣጡ ሥርዓት በሌላ አኳኃን እንዲፈፀም ከልተወሰነ በቀር መጥሪያው ለያንዳንዳቸው እንዲደርስ መታዘዝ አለበት (ቁ 95 (2))፡፡

ሠ. የመጥሪያ አሰጣጥን በተመለከተ ሕጉ አማራጮችን በየደረጃቸው አስቀምጧል፡፡ ፍርድ ቤቱ እነዚህን አማራጮች መጠቀም ያለበት ሕጉ ባስቀመጠው መሠረት የመጀመሪያና የተከታይ ደረጃዎችን በመከተል ብቻ

መሆን አለበት፡፡ (ለምሳሌ የመጀመሪያውን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ እየተቻለ ሦስተኛውን አማራጭ ማዘዝ የለበትም፡፡)

ረ. ከአማራጮቹ የመጀመሪያው የሆነውና በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ ተግባራዊ መሆን ያለበት መጥሪያውን ለተከሳሹ ራሱ መስጠት ነው (95(3)) ፡፡

ሰ. በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ ከቁጥር 96-101 ያሉትን አማራጮች በመጠቀም መጥሪያው እንደሁኔታው ለተከሳሹ ነገረ ፈጅ፣ ለወኪሉ፣ ለእንደራሴው ወይም ሕጉ በሚያዘው መሠረት መጥሪያ ለመቀበል ሥልጣን ላለው ሰው እንዲሰጥ ለማዘዝ ይችላል፡፡

ሸ መጥሪያ የተቀበለ ማንኛውም ሰው መጥራያው የደረሰው መሆኑን ለማረጋገጥ በዋናው መጥሪያ ላይ መፈረም አለበት፡፡

ቀ. መጥሪያ የተላከለት ሰው ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆኑ ወይም ደረሰኝ ለመስጠት እምቢተኝነቱ በመኃላ ቃል የተረጋገጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መጥሪያው እንደደረሰው ቆጥሮ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ለማዘዝ ይችላል (ቁ.103) ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከታየው ግን በቁጥር 105 መሠረት ምትክ መጥሪያ እንዲሰጥ ማድረግ ይችላል፡፡

በ. ተከሳሹ ወይም ስለሱ መጥሪያ መቀበል የሚገባቸው ሰዎች ተፈልገው ካልተገኙ ወይም ተከሳሹ ወኪል ከሌለው ወይም ተከሳሹ መጥሪያው በደንበኛው ሥነ ሥርዓት እንዳይደርሰው መሰናክል ካደረገ በቁጥር 105 መሠረት ምትክ መጥሪያ ይሰጣል፡፡

ተ. ለዋናው መጥሪያ ተጨማሪ የሚሆን ወይም እራሱ ዋናው መጥሪያ ሊሆን የሚችል መጥሪያ በአደራ ፖስታ መላክ ይቻላል (ቁ.106)፡፡

ቸ. በሌላ ፍርድ ቤት ሥልጣን ክልል ውስጥ ለሚኖር ተከሳሽ የሚሰጥ መጥሪያ፣ ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚኖር ተከሳሽ የሚላክ መጥሪያና ለመንግሥት ወይም ለኩባንያ ሠራተኞች የሚሰጥ መጥሪያ ከቁ.106-109 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል፡፡

መጥሪያ ለማድረስ የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ

- ✓ መጥሪያ ለማድረስ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ጊዜ፡- አስር ቀናት
- ✓ መጥሪያ ለማድረስ የሚስፈልገው ከፍተኛ ጊዜ፡- ሰላሳ ቀናት

## 2.1.3. ከቅመ ክስ መስማት በፊት ጉዳዮችን በአማራጭ በፍርድ ቤት-መር አስማሚ ስለመቋጨት

ሀ/ በንግድ ችሎቶች ክስ ተመሥርቶ ለችሎት ሲቀርብ የችሎቱ ዳኞች ቅድመ ክስ ምርመራ ከማድረጉ በፊት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በስምምነት መጨረስ የሚፈልጉ መሆኑን መጠየቅ አለባቸው፡፡

ለ/ የችሎቱ ዳኞች ከላይ በቁጥር 1 ስር በተጠቀሰው መሠረት ተከራካሪ ወገኖች የመስማማት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን መጠየቅ፤ እና ጉዳያቸውን በስምምነት እንዲጨርሱ ከማግባባት እና ከመምከር ኃላፊነት ባለፈ በስረ-ነገር ስልጣን፤ ስነ-ስርአታዊ ጉዳዮች፤ መደበኛ ክስ ስለሚወስደው ጊዜና ወጪ፤ እንዲሁም በባለጉዳዮቹ የሚነሱ ዋና ዋና የክርክር ነጥቦችን በማጥበብ ዙሪያ መለስተኛ የሃሳብ ልውውጥ እንዲደረግ መገፋፋትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው፡፡

ሐ/ የተከራካሪ ወገኖች የመስማማት ፍላጎት ካሳዩ የችሎቱ ዳኞች ጉዳዩን ወዲያውኑ ለፍ/ቤቱ አስማሚ ባለሙያ መምራት አለባቸው፡፡

መ/ ተከራካሪ ወገኖች ከፍ/ቤት ውጪ በራሳቸው መስማማት ከፈለጉም ችሎቱ ግራቀኙ ተስማምተው የሚቀርቡበትን ቀነ-ቀጠሮ በመስጠት የስምምነቱን ተግባራዊነት መከታተል ይኖርበታል፡፡

መ/ ጉዳዩ ወደ አስማሚ ባለሙያ ከተመራበት ቀን ወይም ስምምነት ውጤት ለመጠባበቅ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እልባት ማግኘት አለበት፡፡

ሠ/ ከላይ በቁጥር 5 ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደየ አስፈላጊነቱ የችሎቱ ዳኞች ከአንድ ወር ያልበለጠ ጉዳዩ እልባት የሚያገኝነትን ጊዜ መስጠት ይችላሉ፡፡

ረ/ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በስምምነት መቋጨት ካልቻሉ ጉዳዩ ወደ መደበኛ የዳኝነት ተመልሶ እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ጉዳዮችን በአማራጭ በፍርድ ቤት-መር አስማሚ ለመቋጨት የጊዜ ስታንዳርድ

- ✓ ጉዳዮችን በአማራጭ በፍርድ ቤት-መር አስማሚ ስለመቋጨት የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ጊዜ፡- አስር ቀናት
- ✓ ጉዳዮችን በአማራጭ በፍርድ ቤት-መር አስማሚ ስለመቋጨት የሚያስፈልገው ከፍተኛ ጊዜ፡- አንድ ወር

### 2.1.4. የመከላከያ መልስን ስለመመርመር

ሀ. በመጥሪያው መሠረት ተከሳሹ ፍርድ ቤቱ በቀጠረው ቀን የመከላከያ መልሱን ይዞ ከቀረበ ፍርድ ቤቱ በአንቀፅ 238 መሠረት መልሱን ይመረምራል። ስለ ክስ አቤቱታ የተደነገገው ቁጥር 229 የመከላከያ መልስን ለመርመመርም በተመሳሳይነት ተፈፃሚ ይሆናል።

ለ. የመከላከያ መልሱ ተቀባይነት ካገኘና መከላከያው የከሳሽ ከሳሽነት ክስ ወይም የማቻቻል ጥያቄ ካለው ፍርድ ቤቱ በቁጥር 231 በተደነገገው መሠረት ጥያቄውን መርምሮ መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል (ቁ.238(2))። ጥያቄው ተቀባይነት ከገኘና ከሳሹ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ መልሱን እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ያዛል። ከሳሹ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መልሱን ባያቀርብ ወይም መልሱ ውድቅ ቢደረግ ዋናውን ክስ በተመለከተ የክስ መስማቱ ሂደት ( trial ) ይቀጥላል (ቁ. 239) ።

ሐ. የመከላከያ መልሱ ተቀባይነት ባያገኝም ክሱን የመስማት ሂደት (trial) ይቀጥላል። (ቁ.238 /3/)። ስለዚህ ተከሳሹ መልሱን ይዞ እንዲመጣ በተቀጠረበት ቀን እራሱም ባይመጣ ወይም መልሱን ይዞ ባይመጣም የክሱ መሰማት ሂደት ይቀጥላል።

መከላከያ መልስ ለመመርመር የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ

✓ መከላከያ መልስን ለመመርመር የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ጊዜ፡- አንድ ቀን

✓ መከላከያ መልስን ለመመርመር የሚስፍልገው ከፍተኛ ጊዜ፡- አምስት ቀናት

### 2.1.5. የፅሑፍ ማስረጃ ስለሚቀርብበት ጊዜና ሁኔታ

ሀ. የፅሑፍ ማስረጃዎች በሙሉ ክርክሩን መስማትና ምስክሮችን መመርመር ከመጀመሩ በፊት ተጠቃለው መግባት አለባቸው።

ለ. በመጀመሪያ ደረጃ ከሳሹ ከክስ ማመልከቻው ጋር ተከሳሹ ደግሞ ከመከላከያ መልሱ ጋር ይጠቅመናል የሚሉትንና በእጃቸው የሚገኙትን ወይም ሊያቀርቡ የሚችሉትን የጽሑፍ ማስረጃ በሙሉ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው (ቁ. 223(1)) (ለ) እና 234 (1)።

ሐ. በሁለተኛ ደረጃ ተከራካሪ ወገኖች ለማቅረብ የሚችሉትንና ይጠቅማናል የሚሉትን ወይም ፍርድ ቤቱ እንዲቀርብ የጠየቀውንና አስቀድመው ፍርድ

ቤት ያላቀረቡትን የፅሑፍ ማስረጃ ሁሉ በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ማቅረብ አለባቸው (ቁ. 137 (1)) ::

መ. ማንኛውም አቤት ባይ ሰነዶችን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ ቀጠሮው በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ካላቀረበ በቀር ማስረጃዬ ከፍርድ ቤቱ መዝገብ ጋር ይያያዝልኝ ወይም ለማቅረብ ይፈቀድልኝ በማለት ለማመልከት አይችልም (137(3)::

ሠ. መቅረብ የሚገባቸው ማስረጃዎች ከተከራካሪዎች ወገኖች ባንዳኛው ጉድለት ወይም በቂ ባልሆነ ምክንያት ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል (ቁ. 256(1))::

ረ. ከላይ በ "መ" እና "ሠ" ሥር የተጠቀሱት አጠቃላይ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከአቤቱታ ጋር ወይም በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ የፅሁፍ ማስረጃ በሌላ ጊዜ ሊቀርብ የሚችልበት ልዩ ሁኔታዎች (exceptions) አሉ:: እነዚህም:-

- ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በተከራካሪዎች ወገኖች አመልካችነት በሌላ ፍ/ቤት ዘንድ የሚገኝ መዝገብ ወይም የጽሑፍ ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (ቁ.148 (11))::
- ማስረጃዎቹ ሳይቀርቡ የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ ስለ ክርክሩ አወሳሰንና ማስረጃ ያለመቅረቡ ስላስከተለው ኪሳራ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ በመስጠት ነገሩ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ይወስናል (ቁ. 256 (1):: (ማስረጃው እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል::)
- አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ከመያዙ በፊት በተከራካሪዎች ያልቀረበን የፅሑፍ ማስረጃ በትዕዛዝ አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁ. 149 (1)::
- ክርክሩ በሚሰማበት በማናቸውም ግዜ ፍርድ ቤቱ በተከራካሪዎቹ ያልቀረበ ነገር ግን ለክርክሩ ጠቃሚ የሆነ የፅሑፍ ማስረጃ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል (ቁ.164)::
- ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ ወይም ምስክሩ ነገሩን ለማስታወስ እንዲችል የሚቀርብ የጽሑፍ ማስረጃ በመጀመሪያ በይቀርብም ክርክሩ በሚስማበት ጊዜ መቅረብ ይችላል (137 (4))::

### 2.1.6 የፅሑፍ ክርክር የማቀባበል ሥራን ማጠናቀቅ

ሀ. ፅሑፍ የማቀባበል ሥራ የሚጠናቀቀው ከሳሹ ባቀረበው የክስ አቤቱታና የፅሑፍ ማስረጃ ላይ ተከሳሹ የመከላከያ መልሱንና የፅሑፍ ማስረጃውን ሲያቀርብ ነው፡፡

ለ. ተከሳሹ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ላይ ከሳሹ የመልስ መልስ እንዲሰጥ ሊፈቀድለት አይገባም፡፡

ሐ. ፅሑፍ የማቀባበሉ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ በቁ. 241 እና በተከታዮቹ መሠረት ተከራካሪዎቹን መመርመርና የክርክሩን ጭብጥ የመያዝ ሂደት ይቀጥላል፡፡

የጽሑፍ ማስረጃን አጠቃሎ ለመቀበል እና የጽሑፍ ክርክርን ለማቀባበል የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ

✓ ማስረጃ እና ክርክርን ለማቀባበል የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ጊዜ፡- አስራ አምስት ቀናት

✓ ማስረጃ እና ክርክርን ለማቀባበል የሚያስፈልገው ከፍተኛ ጊዜ፡- አንድ ወር ከ10 ቀናት

## 2.2. ክስን ስለመስማት (Trial)

### 2.2.1 ስለተከራካሪ ወገኖች አለመቅረብ

ሀ. ክርክሩን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ግራቀኙ ወገኖች ካልቀረቡ ዳኛው ቀረቡለትን ሌሎች መዝገቦች ካስተናገደ በኋላ የክስ መዝገቡ ይዘጋል (69(2))፡፡

ለ. በቁ.69 (2) መሠረት የክስ መዝገብ ከተዘጋ ከሳሹ በቁ.71 መሰረት ተገቢውን ዳኝነት (በድጋሚ) እና ኪሳራ ከፍሎ መዝገቡን ለማስከፈት ይችላል፡፡ ከሳሹ የቀረው በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ድጋሚ ዳኝነት ወይንም ኪሳራ ላይከፍል ይችላል፡፡

ሐ. ከሳሽ ቀርቦ ተከሳሽ ካልቀረበ በቁ.70 መሠረት እንደ ሁኔታው ተከሳሹ በሌለበት እንዲቀጥል ወይም ሁለተኛ መጥሪያ እንዲላክ ማዘዝ ወይም ክርክሩን ለሌላ ቀጠሮ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

መ. መጥሪያው ለተከሳሹ (ሾቹ) ያልደረሰው በከሳሽ ጥፋት ከሆነ ባልደረሳቸው ተከሳሾች ላይ የክስ መዝገቡ ይዘጋል (70(መ))፡፡

ሠ. በቁ.70 (መ) መሠረት የክስ መዝገቡ ከተዘጋ ከሳሹ የቁ.71ን ሁኔታዎች በማሟላት መዝገቡ እንዲከፈትለት ለመጠየቅ ይችላል:: ቁጥር 74 ለይግባኝ መዝገብ እንጂ ለቀጥታ ክስ ተፈፃሚ አይሆንም:: (በ70 (መ) ለተዘጋ መዝገብ)::

ረ. በቁ.70 (ሀ) መሠረት ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ከታዘዘ በኃላ በሚቀጥለው ቀጠሮ ቀርቦ በመጀመሪያ ቀጠሮ ያልቀረበው በቂ በሆነ እክል መሆኑን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ እንዲከራከር ሊፈቀድለት ይችላል (ቁ. 72) ::

ሰ. ተከሳሽ ቀርቦ ከሳሽ ሳይቀርብ ከቀረ ችሎቱ ምክንያታዊ ለሚሆን ጊዜ ከታገሰ በኂላ

- ተከሳሹ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በታመነው መጠን ውሳኔ መስጠት ይችላል (ቁ.73)::
- ሆኖም ግን ተከሳሽ ስለመነ ብቻ ለከሳሹ የሚወሰን ሳይሆን ተከሳሹ ቢያምንም ከሳሽ ያቀረበው ክስ ሕጋዊ መሆኑንና ከሳሹ የጠየቀው ዳኝነት በሕግ የሚገባው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማጣራት አለበት::
- ተከሳሹ ከካደ መዝገቡ ይዘጋል::
- ሆኖም ግን ችሎቱ ከሳሽ ዘግይቶ የሚቀርብ ከሆነ ሲጠባበቅ የቀረበው ወገን አላግባብ እንዳይጉላላ ፍቃዱን መጠየቅ ይሻላል::
- ከሳሹ በቁጥር 74 በተደነገገው መሠረት የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈትለት መጠየቅ ይችላል:: ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኘው ከሳሹ በመጀመሪያው ቀጠሮ የቀረው በቂ በሆነ ችግር መሆኑን ካስረዳ ነው:: ፍረድ ቤቱ ጥያቄውን ከተቀበለ ስለኪሣራውና ስለማናቸውም ወጪ አከፋፈል ተስማሚ መስሎ የታየውን ውሳኔ ከሰጠ በኃላ የተዘጋው መዝገብ እንደገና ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀጠሮ ይወስናል:: ትዕዛዙ የሚሰጥው የከሳሹ ማመልከቻ ለመልስ ሰጪው ከደረሰው በኃላ ነው:: (በቁጥር 73 መሠረት ለተዘጋ መዝገብ ቁጥር 69 ተፈፃሚ አይሆንም)::

### 2.2.2 ስለ ተከራካሪ ወገኖች መቅረብ

ሀ/ ባለጉዳዩ እራሱ የመቅረብ ግዴታ አይደለም:: ስለዚህ ባለጉዳዩ እራሱ መቅረብ ካልፈለገ ወይም ካልቻለ እንደሁኔታው ከቁጥር 57-64 በተደነገገው መሰረት ነገረ ፈጁ ፣ወኪሉ ወይንም ጠበቃው ቀርቦ መከራከር ይችላል::

እነዚህም በሕግ ወይም በውል የተሰጣቸው የውክልና ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ባለ ጉዳዩ በጠበቃ የሚወከል ከሆነ ጠበቃው ከውክልና ማስረጃው በተጨማሪ የጥብቅና አገልግሎት ውል ካለ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ ሆኖም ግን ውስን በሆኑና አስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች ባለጉዳዩ እራሱ እንዲቀርብ ማዘዝ ይቻላል (ቁጥር 65፣ 68ና 241(3))፡፡

ሐ/ ባለጉዳዩ እራሱ እንዲቀርብ ታዞ በቂ ባልሆነ ምክንያት የቀረ እነደሆነ ወኪሉ ቢቀርብም ስለክሳሽ ወይም ተከሳሽ ያለማቅረብ የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ (ቁጥር 77) ፡፡

መ/ ክርክሩን ለመስማት በተቀጠረው ቀን ባለጉዳዮች እራሳቸው ከቀረቡ ማንነታቸው ከተረጋገጠ ወኪሎቻቸው ከቀረቡ ደግሞ ሕጋዊ ውክልና እንዳላቸው ከተረጋገጠ በኂላ የክስ መሰማት ሂደት ይቀጥላል (ቁጥር 69(1)እና 241(1)) ፡፡

### 2.2.3 የሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት ወይም ክስ ውስጥ መግባት

ሐ. ሦስተኛ ወገኖች በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማመልከቻ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ከተቀበለ ከፍርድ ውሳኔ በፊት በክርክሩ ጣልቃ መግባት ይችላሉ (ቁጥር 41) ፡፡

ለ. በተከሳሹ ጠያቂነት ጉዳዩ በእዳነት የሚመለከተው ሌላ ሦስተኛ ወገን በክሱ ውስጥ እንዲገባ ፍርድ ቤት ማዘዝ ይችላል (ቁጥር 43) ፡፡

ሐ. አንድ ተከሳሽ በክሱ ውስጥ ያለ ሌላ ተከሳሽ ድርሻውን መክፈል ይገባዋል ብሎ ሲያመለከትም ቁጥር 43 በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል (ቁጥር 43(4)) ፡፡

መ. በአንቀፅ 43 መሰረት በክሱ ውስጥ እንዲገባ የታዘዘ ሦስተኛ ወገን መጥሪያው ከደረሰው በኂላ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ኃላፊ የማይሆንበትን ምክንያት ሳይከራከር የቀረ እነደሆነ ዋናው ተከሳሽ የተፈረደበትን ክስ እንደተቀበለ ተቆጥሮ ከሳሹ ባመለከተው መጠን በኃላፊነት የሚጠየቅበትን ድርሻውን እንዲከፍል ይገደዳል (ቁጥር 76)፡፡

### 2.2.4 ተከራካሪዎቹን ስለመመርመር

ሀ/ ባለጉዳዮቹ ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ስለክርክሩ መነሻ እና ከክርክሩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከባለጉዳዮቹ በመሰለው ዘዴ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ይመረምራቸዋል (ቁጥር 241)፡፡

ለ/ ከሳሹ ቀርቦ ተከሳሹ ቢቀርም ይህ ምርመራ በከሳሹ ላይ ብቻ መካሄድ አለበት፡፡

ሐ. በዚህ ደረጃ ባለጉዳዮችን በመሰለው የሚመረምረው ፍርድ ቤቱ ነው እንጂ ባለጉዳዮቹ ሙግት አይጀምሩም (ቁጥር 241(2)) ፡፡ የባለጉዳዮች የቃል ሙግት የሚጀምረው በአንቀፅ 258 ነው፡፡ ሆኖም ክሱ በሚከፈትበት ጊዜም ቢሆን ከተከራካሪዎቹ ማንኛውም ወገን እንዲብራራለት የሚፈልገውን ጉዳይ ፍርድ ቤቱ እንዲጠይቅለት ለማመልከት ይችላል (241(2))፡፡

መ/ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ወይንም በምርመራው ወቅት በሚሰጠው ቃል የተከሰሰበትን ነገር ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ያመነ እንደሆነ በታመነው መጠን ለከሳሹ ይፈረዳል (ቁጥር 242)፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ስላመነ ብቻ ለከሳሹ የሚወሰን ሳይሆን ተከሳሹ ቢያምንም ከሳሽ ያቀረበው ክስ ህጋዊ መሆኑንና ከሳሹ ያቀረበው ዳኝነት በሕግ የሚገባው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማጣራት አለበት፡፡

ሠ/ ክርክሩ በሚቀጥልበት ሂደት ውስጥ ተከሳሹ ያመነው ጉዳይ ካለም ቁጥር 242 ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ በቁጥር 241 የተደነገገው ምርመራም በክርክሩ ሂደት ሁሉ ሊቀጥል ይችላል (ቁጥር 243)፡፡

ረ/ ፍርድ ቤቱ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ሐሰተኛ ቃል የሰጠን ተከራካሪ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 446 መሰረት ፍርድ ቤቱ ወዲያው በያዘው መዝገብ ላይ ሊቀጣ ይችላል፡፡ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ ካልሆነም በተመሳሳይ ሁኔታ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 442 መሠረት መቅጣት ይችላል (ቁጥር 481)፡፡

ሸ/ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት ባለጉዳዮን መምከርና በቁጥር 480 መሠረት አስፈላጊ የሆነውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በመጨረሻ ምርጫ መሆን አለበት፡፡

ቀ/ ተከራካሪ ወገኖቹ ወይም አንዱ ችሎቱ የሚካሄድበትን ቋንቋ የማያውቁ ከሆነ ፍርድ ቤቱ አስተርጓሚ መመደብ አለበት፡፡ አስተርጓሚው የመተርጐም ስራውን ከመጀመሩ በፊት የመሐላ ወይም የማገጋገጫ ቃሉን መስጠት አለበት፡፡ የመኃላ ቃሉም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት "በዚህ ፍርድ ቤት የቀረበውን ክርክር በእውነትና የችሎታዬን ያህል ልተረጉም እምላለሁ" የሚል መሆን አለበት፡፡ አስተርጓሚው እምላለሁ ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ እምላለሁ በማለት ፋንታ አረጋግጣለሁ ማለት ይችላል፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ

እንዲምል ማስገደድ ተገቢ አይደለም።

በ/ ክሱ የሚሰማው በግልፅ ችሎት መሆን አለበት። ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ህይወት፣ የሕዝብን ሞራልና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ጉዳዩን በዝግ ችሎት ማየት ይቻላል።

## 2.2.5በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር ላይ የሚቀርቡ መቃወሚያዎች

ሀ/ ማስረጃ ተቀብሎ ከመመረመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ላቀረበው መቃወሚያ ውሳኔ መስጠት አለበት (ቁጥር 244(1))።

ለ/ መቃወሚያዎቹ ከአንድ በላይ ከሆኑ ሁሉም አንድ ላይ መቅረብ አለባቸው። ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስናክሉ ካልሆኑ በቀር መጀመሪያ ያልቀረቡ መቃወሚያዎች በኃላ መቅረብ አይችሉም። (ቁጥር 244(3))

ሐ/ መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ከመከላከያ መልስ ጋር ነው እንጂ መጀመሪያ መቃወሚያ ብቻ ቀርቦ ሙሉ መልስ በኃላ የሚቀርብበትን አሠራር ፍርድ ቤቱ መፍቀድ የለበትም። ስለዚህ ሙሉ መልስ ተሟልቶ ሳይቀርብ መቃወሚያው ብቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቁጥር 338 መሠረት የመከላከያ መልሱን ሲመረምር እንዲህ አይነቱን ያልተሟላ መልስ አለመቀበል ወይም ተሰተካክሎ እንዲቀርብ ማዘዝ አለበት።

መ/ ክሱ ትክክለኛውን ፎርም አልተከተለም የሚል ክርክር እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መቅረብ አይችልም (ቁጥር 24(4))።

ሠ/ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን መቃወሚያ እንዲሁም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በቁጥር 245 መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል።

ረ/ የቀረበው መቃወሚያ ክሱ የተነሳበት ጉዳይ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ ወይም አስቀድም በፍርድ የተወሰነ መሆኑን፣ ወይም በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈጸመ መሆኑን፣ ወይም ለዕርቅ የተቀጠረ መሆኑን የሚገልፅ ከሆነና ይህም በማስረጃ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ክሱን ዘግቶ ባለጉዳዮቹን ያሰናብታል (ቁጥር 245(2))።

ሰ/ ከላይ በቁጥር 7 ስር ከተገለፀው ውጪ ያለ መቃወሚያ ሲቀርብና በማስረጃ ሲረጋገጥ ግን ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሰጣል።

ሸ/ ከላይ በቁ. 8 ሥር በተጠቀሰው ሁኔታ መዝገቡ ሲዘጋ ካሳሽ ክሱን አሻሻሎ

በዚያው ወይም በሌላ ፍርድ ቤት ክሱን እንደገና ለማቅረብ ይችላል:: ከላይ በቁጥር 7 ሥር በተጠቀሰው ሁኔታ ክሱ ሲዘጋ ግን ከሳሹ በዚያው ጉዳይ ሌላ ክስ ለማቅረብ አይችልም (ቁጥር 245 (3))::

ቀ/ መዝገቡ የተዘጋው ፍርድ ቤቱ ሥልጣን በማጣቱ ከሆነ ከሳሹ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ላይ በደንቡ መሠረት ከሚከፈለው ሂሣብ የቀረው ይመለስለታል (ቁጥር 245(4))::

### 2.2.6 የክርክሩን ጭብጥ መያዝ

ሀ/ በቁጥር 241 መሠረት ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎቹን በአግባቡ በቃል ከመረመረ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተነስቶ እንደሆነም በመቃወሚያው ላይ አስፈላጊው ብይን ከተሰጠ በኋላ (በቀረበው መቃወሚያ መሰረት ክሱ ወይም መዝገቡ ካልተዘጋ በቀር) ባለ ጉዳዮቹ የሚከራከሩበት ወይም የተለያዩበት ጭብጥ ይመሰረታል::

ለ/ ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ወገን ያመነውን ወይም አለ ብሎ የሚከራከረውንና ከክርክሩ ጋር አግባብነት ያለውን የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ጉዳይ ሌላኛው ወገን ሲክድ ነው (ቁጥር 247(1)::

ሐ/ የሚመሠረተው ጭብጥ እንደነገሩ ሁኔታ

- የሕግ ብቻ፣
- የፍሬ ነገር በቻ ወይም
- የፍሬ ነገር እና የህግ ሊሆን ይችላል::

መ/ በአንድ ክስ ላይ ከአንድ በላይ የሆነ የፍሬ ነገር ወይም የህግ ወይም የሁለቱንም

ጭብጦችን መያዝ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል (ቁጥር 247(3)(4)) ::

ሠ/ የሕግና የፍሬ ነገር ጭብጦች አንድ ላይ ከተያዙ መጀመሪያ የሕግ ጉዳይ ላይ በተያዘው ጭብጥ ላይ ውሳኔ መሰጠት አለበት:: ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍርድ ቤቱ በሕግ ረገድ የተያዙትን ጭብጦች እስኪወስን ድረስ በፍሬ ነገር የተያዘውን ጭብጥ በቀጠሮ ሊያቆየው ይችላል (ቁጥር 247 (4)) ::

ረ/ የተያዘው ጭበጥ የሕግ ጉዳይ ብቻ ከሆነ (የፍሬ ነገር ክርክር ወይም ጭብጥ ከሌለ) ወዲያው አስፈላጊው ውሳኔ መሰጠት አለበት::

ሠ/ ጭብጥ የሚመሰረተው የግራቀኙ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት መሆን አለበት::

ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ከመመስረቱ በፊት ምስክሮችንና የፅሁፍ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁጥር 249)፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ መጀመሪያ ተይዘው የነበሩትን ጭብጦች ለማሻሻል፣ ለመቀየር ወይም ተሳስቶ ተቀብሎ የነበረውን ጭብጥ ለመሰረዝ ይችላል (ቁ. 251) ፡፡

ሸ/ በመሰረቱ ጭብጥ የሚይዘው ፍርድ ቤቱ ነው፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ሲይዝ ጭብጡ ምን እንደሆነ ለባለጉዳዮቹ መግለፅና ሐሳባቸውን የመስማት ኃላፊነት አለበት፡፡

ቀ/ በሌላ በኩልም ተከራካሪ ወገኖች እራሳቸው ጭብጡ ላይ በመስማማት ፍርድ ቤቱ ጭብጡን እንዲይዝላቸው ለማመልከት ይችላሉ (ቁጥር 251)፡፡ ፍርድ ቤቱም በቁጥር 253 መሠረት ጥያቄውን መርምሮ ጭብጡን በመቀበል በዚያው መሠረት ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡

በ/ ክሱ በሚሰማበት ቀን ተከሳሹ የመከላከያ መልሱን ሳያቀርብ ከቀረ ፍርድ ቤቱ የነገሩን ጭብጥ ለመያዝ አይገደድም (ቁጥር 246(2)) ፡፡ ሆኖም ግን ከሳሹ ካቀረበው ክስ አና የጽሑፍ ማስረጃ እንዲሁም በቁጥር 241 መሠረት በተደረገው የቃል ምርመራ ከተገኘው መረጃ በመነሳት አሰፈላጊ መስሎ ከታየው ፍረድ ቤት መፍትሔ የሚሻውን ጭብጥ ለመያዝ ይችላል፡፡

ተ/ የክርክሩ ጭበጥ የሚያዘው (ቁጥር 248)፤

ሀ. በክሱና በመከላከያው መልስ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች፣

ለ. ተከራካሪዎቹ ያቀረቡትን የፅሑፍ ማስረጃ፣

ሐ. በቁጥር 241 መሠረት በተደረገው ምርመራ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ (እንደሁኔታው ሦስቱንም ወይም ከሦስቱ ሁለቱን ወይም አንዱን መሠረት በማድረግ) ነው፡፡

ቸ/ ከላይ በቁጥር “11” ከተዘረዘሩት ውጪ ሌላ ማስረጃ መቅረቡ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ለመመሥረት አስፈላጊ የሆኑ ምስክሮችንና የፅሑፍ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁጥር 249) ፡፡

ኀ/ ክስ በቀረበበት ሀብት ግምት ላይ ክርክር ከተነሳ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ ከመመሥረቱ በፊት የሀብቱን ግምት የሚያስታውቁ ምትክ ዳኞችን መሾም አለበት (ቁጥር 250) ፡፡

ነ/ ተከራካሪዎቹን የሚያከራክራቸው ነጥብ አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሳይሆን ወዲያው ተገቢውን ፍርድ መስጠት አለበት (ቁጥር 254)፡፡

ኘ/ ተከራካሪዎቹን የሚለያያቸው ነጥብ መኖሩ ከታወቀ ግን ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ከመሠረተ በኃላ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በመጀመሪያ ክርክር ላይ ያቀረቡት ማስረጃና (በተጨማሪም በቁጥር 249 መሠረት በፍረድ ቤት ትዕዛዝ የቀረበው ማስረጃ) ክርክር በቻ ፍትሐዊ ፍርድ ለመስጠት በቂ ከሆነ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል (ቁጥር 255) ፡፡

አ/ በመጀመሪያ ክርክር የቀረበው ክርክርና ማስረጃ ብቻ (በ223፣ በ237 ና 256(1) መሠረት በተከራካሪዎቹ የቀረበ ወይም በቁጥር 249 እና 145 መሠረት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የቀረበ ማስረጃ) ጭብጡ ላይ ውሳኔ ለመስጠትና አስፈላጊውን ፍርድ ለመስጠት በቂ ሆኖ ካልተገኘ በቁጥር 257 እና በተከታዮቹ መሠረት ምስክሮችን መመርመር ይቀጥላል፡፡

## 2.3 ክርክሩን ስለመስማት እና ምስክሮችን ስለመመርመር

### 2.3.1 ስለ ምስክሮች

ሀ/ ተከራካሪዎቹ ያቀረቡት የፅሑፍ ወይም የቃል ክርክርና ከአቤቱታዎቻቸው ጋር ወይም በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያቀረቡት የፅሑፍ ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ ጭብጡን ከመመስረቱ በፊት አስቀርቦ የመረመራቸው የሰውና የፅሑፍ ማስርጃዎች በክርክሩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት በቂ ካልሆኑ ፍ/ ቤቱ በቁ. 223 መሠረት ተከራካሪዎቹ የዘረዘሯቸው ምስክሮች ቀረበው እንዲሰሙ ያዛል፡፡

ለ/ ሁለቱም ወገኖች የምስክሮች ዝርዝር አቅርበው ከሆነ የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ቀን እንዲቀርቡ መታዘዝ አለበት፡፡

ሐ/ መቅረብ ያለባቸው ተከራካሪዎቹ በአቤቱታቸው ላይ የገለጿቸው ምስክሮች ሁሉ ሳይሆን በፅሑፍ ማስርጃ ያልተረጋገጡና በቁ. 241 መሠረት በተደረገው ምርመራ ተከራካሪዎቹ ያልተማመኑባቸውን የፍሬ ነገር ጭብጥ ለማስረዳት የሚችሉ ምስክሮች ብቻ ናቸው፡፡

መ/ አንደኛው ወገን የሌላውን ወገን ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ የመመርመር መብት ስላለው በመሠረቱ ምስክሮች በተቻለ መጠን በአካል ፍ/ቤት ቀርበው ቃላቸውን መስጠት አለባቸው (ቁ. 261(3)) ፡፡

ሠ/ ከላይ በቁ.4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በውስን ሁኔታዎች ፍ/ቤቱ

ተገቢ መስሎ ሲታየው የፍርድ ቤት እንደራሴ ሆኖ በመወከል ማንኛውንም ማስረጃ የሚሰበሰብ ወይም ምስክር የሚመረምር ምትክ ዳኛ መሰየም ይችላል (ቁ. 122-135)። እንዲሁም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) አስፈላጊውን ምርመራ አድርጎ የምርመራውን ውጤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ ለማዘዝ ይችላል (ቁ. 136)።

ረ/ በተጨማሪም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች ምስክሩ ፍ/ቤት ሳይቀርብ የመሐላ ቃል እንዲሰጥና ቃሉ በችሎት በንባብ እንዲሰማ ማድረግ ይችላል (ቁ. 203-206)።

**2.3.2 ለምስክሮች መጥሪያ መላክ**

ሀ/ ከላይ በ(ለ) (5) እና (6) ሥር ከተመለከተው ውጪ ምስክር በአካል ፍ/ቤት ቀርቦ መመስከር አለበት።

ለ/ የመቅረባቸው አስፈላጊነት የታመነባቸው የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ላይ እንዲቀርቡ መጥሪያ ሊደርሳቸው ይገባል። የመጥሪያው አላላክ ከቁ.111 እስከ 121 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል።

ሐ/ አመልካቹ ራሱ (መጥሪያ ሳይጠይቅ) ምስክሮቹን ለማቅረብ ይችላል (ቁ. 111)።

መ/ መጥሪያ የሚጠይቀው ወገን መጥሪያውን ከመቀበሉ በፊት ፍ/ቤቱ በወሰነው ልክ ለምስክሮች ማጓጓዣና ሌላ የቀን ወጪ ወይም አበል የሚሆን ገንዘብ እንዲያስቀምጥ ይገደዳል። ይህን ግዴታ ካልፈፀመ የመጥሪያ ትዕዛዝ ሊሰጠው አይገባም (ቁ. 212 እና 213)።

ሠ/ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ ወይም የፅሑፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ለሚጠራ ሰው በሚፃፈው የመጥሪያ ትዕዛዝ ላይ የተጠራበትን ምክንያት፣ የሚቀርብበትን ቀንና ሰዓት፣ ሥፍራው፣ የተጠራው ለምስክርነት ወይም የፅሑፍ ማስርጃ ለማቅረብ ወይም ስለ ሁለቱም ጉዳይ መሆኑ ተለይቶ መገለፅ አለበት (114)።

ረ/ የምስክርነት ቃል ለመስጠት ሳይሆን የፅሑፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብቻ የታዘዘ ሰው ማስረጃው ለፍ/ቤቱ እንዲደርስ ካደረገ ራሱ ለመቅረብ አይገደድም (ቁ. 115)።

ሠ/ ስለተከሳሽ መጥሪያ የተደነገጉት ድንጋጌዎች (ከቁ. 103-105 ከተደነገገው በቀር) ለምስክር በሚሰጥ መጥሪያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ (ቁ. 116)።

ሰ/ መጥሪያው ሲላክ ተጠሪው በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ለመድረስ እንዲችል ለመጓጓዣና አስፈላጊውን መሰናዳት ለማድረግ በቂ ሆኖ በሚገመት ጊዜ ውስጥ ሊደርሰው እንዲችል መደረግ አለበት፡፡

ሸ/ መጥሪያው የተላከለት ሰው መጥሪያው ስላልደረሰው ሳይቀርብ የቀረ ወይም የፅሑፍ ማስረጃውን ሳያቀርብ ከቀረና ምስክሩ ወይም የፅሑፍ ማስረጃው መቅረቡ ጠቃሚ ከሆነ ባለ ጉዳዩ ተገቢውን ኪሣራ ከፍሎ ሌላ መጥሪያ እንዲደርሰው ይታዘዝለታል (118(2) (ሀ))፡፡

ቀ/ የተጠራው ሰው መጥሪያው ደርሶት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት ከሆነ ወይም እንዳይደርሰው ሆነ ብሎ ከተሰወረ ተጠሪው ተገዶ ወይም ታስሮ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ያዛል (ቁ. 118 (2) (ለ))፡፡ በተጨማሪም በወ/መ/ሕ/ቁ 442 መሠረት በወንጀል ሊቀጣው ይችላል (ቁ. 118 (3) እና 481)፡፡

በ/ ክርክሩን ለመስማት በተቀጠረው ቀን የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ላይ ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡

### 2.3.3 የምስክሮች ተሟልተው አለመቅረብ

ሀ/ ከሁለቱም ወገን ምንም ምስክር ካልቀረበ ወይም ምስክሮች በከፊል ብቻ ከቀረቡ (መጥሪያውን እንዲያደርስ የታዘዘው ቁ. 95 (1) በሚያዘው መሠረት መጥሪያ ሰጪ ሳይሆን ባለጉዳዮቹ ራሳቸው እንዲያደርሱ በታዘዙ ጊዜና ክርክሩን የመጀመርና ማስረጃ በቅድሚያ የማሰማት መብት የከሳሹ በሆነበት ሁኔታ

✓ የሁለቱም ወገን ምስክሮች ካልቀረቡ፤

- በሁለቱም ባለጉዳዮች ጥፋት ከሆነ መዝገቡ ላይ ባለው ማስረጃ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት ወይም ክሱን መዝጋት እንጂ ምስክሮቹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መሰጠት የለበትም (ቁ. 196 እና 199)፡፡
- የከሳሽ የቀሩት በከሳሹ ጥፋት ሆኖ የተከሳሹ የቀሩት ግን በጥፋቱ ሳይሆን ከዓቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የከሳሹን ምስክር ለመስማት ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም፡፡ ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት ወይም የከሳሹ ምስክሮች ባይሰሙም በተከሳሽ ምስክር መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ካሉ የተከሳሽ ምስክሮችን ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት፡፡
- የከሳሹ ያልቀረቡት ከዐቅም በላይ በሆነ ችግር ሆኖ የተከሳሹ የቀሩት በተከሳሹ ጥፋት ከሆነ የከሳሹን ምስክሮች ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ትዕዛዝ

ወይም ውሳኔ መስጠት። የተከሳሹ ምስክሮች እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም።

✓ የከሳሽ ምስክር ምንም ሳይቀርቡ የተከሳሽ የተወሰነ ወይም በሙሉ ቢቀርቡ፤

- የከሳሽ ምስክር ያልቀረቡት ከዓቅሙ በላይ በሆነ ችግር ከሆነ ምስክሮቹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠትና እንዲሁም የተከሳሹን ምስክሮች መመለስና በሚቀጥለው ቀን ቀጠሮ እንዲቀርቡ ማዘዝ። በተከሳሹና በምስክሮቹ ላይ ለደረሰው መጉላላት በቂ ኪሣራ መወሰን።
- በከሳሹ ጥፋት ከሆነ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም። ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት። የከሳሹ ምስክር ባይሰሙም በተከሳሽ ምስክር መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ካሉ የተከሳሽ ምስክሮችን ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት።

✓ የከሳሽ የተወሰኑ ብቻ ቀርበው የተከሳሽ በሙሉ ወይም በከፊል ቢቀርቡ

- ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የቀረቡትን የከሳሽ ምስክር መስማት። ያልቀረቡት መቅረባቸው የግድ አስፈላጊ ከሆነ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠት። የተከሳሽ ምስክሮች እንዲመለሱና በሚቀጥለው ቀነ-ቀጠሮ እንዲቀርቡ ማዘዝ። በተከሳሽና በከሣሹ ምስክሮች ላይ ለደረሰው መጉላላት ተገቢውን ኪሣራ መወሰን።
- በከሳሹ ጥፋት ከሆነ የቀረቡትን ምስክሮች ብቻ መስማት። የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም። የተሰሙት የከሳሽ ምስክሮች ብቻ እንደክሱ ካላስረዱ ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት። የተሰሙት ብቻ ክሱን በማስረዳታቸው ወይም ባያስረዱም አንዳንድ ነጥቦችን ለማጣራት የተከሳሽ ምስክር መስማት አስፈላጊ ከሆነ መስማት።

✓ የከሳሽ በሙሉ ቀርበው የተከሳሽ ምንም ካልቀረቡ፡-

- በተከሳሽ ጥፋት ከሆነ የከሳሽ ብቻ ተሰምተው አስፈላጊው ውሳኔ ይሰጣል። የተከሳሹን ምስክር ለመስማት ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም።
- በተከሳሹ ጥፋት ሳይሆን ከዓቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የከሳሹን ሰምቶ የተከሳሹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠት። በከሳሹ ላይ ለደረሰው መጉላላት ተገቢውን ኪሣራ ተከሳሽ እንዲከፍል ማዘዝ።

✓ የከሳሽ በሙሉ ቀርበው የተከሳሽ በከፊል ብቻ ቢቀርቡ፡-

- በተከሳሹ ጥፋት ከሆነ የከሳሽ ከተሰሙ በኃላ እንደ ክሱ ካስረዱ የቀረቡትን

የተከሳሽ ምስክር ብቻ መስማት:: የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀን ቀጠሮ አይሰጥም::

- ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ወይም ምክንያት ከሆነ የከሳሽ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ እንደ ክሱ አስረድተው ከሆነ የቀረቡትን የተከሳሽ ምስክሮች መስማት:: የቀሩት የተከሳሽ ምስክሮች መቅረብ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆናቸው ከታመነበት የቀረቡትን ሰምቶ የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀን ቀጠሮ መስጠት:: ቀጠሮ ከተሰጠ በከሳሹ ላይ ለደረሰው መጉላላት ተከሳሽ በቂ የሆነ ኪሣራ እንዲከፍል ማዘዝ::

ለ/ ከላይ በቁ. 1 የተመለከተው ሁኔታ ፍ/ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ የግድ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ያልቀረበው ምስክር እንደተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ከማዘዝ አያግደውም::

ሐ/ ምስክሩ የቀረው በባለጉዳዮች ጥፋት ሳይሆን መጥሪያ በትክክል ከደረሰው በኃላ በእምቢተኝነት የቀረ እንደሆነ በቁ. 118 (2) (ለ) የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል::

መ/ ምስክሮች ተሟልተው ከቀረቡ ወይም በከፊል ቢቀርቡም የቀረቡት እንዲሰሙ ፍ/ቤት የወሰነ እንደሆነ ምስክሮችን መመርመር ይቀጥላል::

ሠ/ የቀረቡትን ምስክሮች በአንድ ቀን ሰምቶ መጨረስ ካልቻለ ፍ/ቤቱ ምስክሮቹን ሁሉ ሰምቶ እስኪጨርስ ድረስ በየዕለቱ አዳሪ የሚሆን ቀጠሮ እየሰጠ ሥራውን ማከናወን አለበት እንጂ ረጅም ቀጠሮ መስጠት የለበትም (ቁ. 197 (3))::

## 2.4. የተከራካሪዎቹ ሙግት መጀመርና ምስክሮችን መመርመር

### 2.4.1. ስለ ክሱ መከፈትና ሙግትን የመጀመር መብት

ሀ/ ክስን መክፈትና ሙግትን የመጀመር መብት የከሳሽ ነው:: ነገር ግን ተከሳሹ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ሕግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሹ ይሆናል (258(1)) ::

ለ/ ክሱን የሚጀምረው ወገን የመክፈቻ ቃሉን ከሰጠና ምስክሮቹ የሚመሰክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ካስረዳ በኃላ የሚደግፈውን ማስርጃ አቅርቦ ያሰማል (259(1))::

ሐ/ ክሱን የሚጀምረው ወገን ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኃላ ሌላኛው

ወገን የራሱን የመካላከያ መክፈቻ ቃል ካሰማና የመከላከያ ምስክሮቹ የሚመሰክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ካስረዳ በኋላ የመከላከያ ምስክሩን አቅርቦ ያሰማል (ቁ. 259(2))።

**2.4.2. የማስረጃ አቀራረብ**

ሐ/ ምስክር የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የመኃላ ቃል ወይም የሚሰጠው ቃል እውነተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃል መስጠት አለበት (261(1))።

ለ/ የሚሰጠው የመኃላ ቃል በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት "በዚህ ፍርድ ቤት ፊት የምሰጠው ቃል እውነት፣በሙሉ እውነት፣ እውነት እንጂ ሌላ ምንም እንደማይሆን እምላለሁ።" የሚል መሆን አለበት። ምስክሩ "እምላለሁ" ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ "እምላለሁ" በማለት ፋንታ "አረጋግጣለሁ" ማለቱ በቂ ነው። ምስክሩ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ አስፈላጊ አይደለም።

ሐ/ ስለራሱ ጉዳይ የምስክርነት ቃል መስጠት የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን መመስከር ይችላል። የሚመሰክረውም እውነት እንደሚናገር ከማለ ወይም ካረጋገጠ በኃላ መሆን አለበት።

መ/ ምስክሩን ያቀረበው ወገን ለራሱ ምስክሮች ዋና ጥያቄ (examination-in-chief) በማቅረብ ይመረምራቸዋል። በዋና ጥያቄ ወቅት መሪ ጥያቄ አይፈቀድም። ሆኖም ፍ/ቤቱን በማስፈቀድ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል (ቁ. 263 (1) (2))።

ሠ/ በዋና ጥያቄ ጊዜ የሚቀርበው ጥያቄ ጭብጡን የሚመለከትና ምስክሩ በቀጥታ ወይም በሌላ መንገድ በሚያውቀው ወይም ሊያውቀው በሚችለው ነገር ላይ ብቻ ነው (263(1)) ።

ረ/ ምስክሩን ያቀረበው ወገን ዋና ጥያቄ አቅርቦ ከጨረሰ በኃላ ተቃራኒው ወገን መስቀልኛ ጥያቄ በማቅረብ ምስክሩን ይመረምረዋል። በመስቀልኛ የሚቀርበው ጥያቄ ምስክሩ በዋና ጥያቄ የሰጠው የምስክርነት ቃል የተሳሳተበትን፣ ሀሰት ነው የሚባልበትን ወይም አጠራጣሪ መስሎ የተገመተበትን ነጥብ ፍ/ቤቱ እንዲረዳ ለማድረግ የሚቀርብ ነው። ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት በዋና ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም። ሆኖም

በመስቀለኛ ጥያቄ  ወቅት ምስክሩን መምራት ይቻላል (ቁ. 263 (3))፡፡

ሸ/ የመስቀልኛ ጥያቄ ካለቀ በኃላ የመጀመሪያው ጠያቂ የማጣሪያ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ በማጣሪያ ጥያቄ ወቅት በመስቀልኛ ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡ ጥያቄው የሚጠየቀው ምስክሩ በመስቀልኛ ጥያቄ ወቅት የሰጠውን ቃል ለማብራራት ብቻ ነው (ቁ. 263 (4))፡፡

ቀ/ ምስክርን የመመርመር ሥራ በዋናነት የባለጉዳዮቹ ቢሆንም ስለ ጉዳዩ መብራራትና ስለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ መስሎ የታየው እንደሆነ ፍ/ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ምስክሩን ለመጠየቅ ይችላል (ቁ. 261(4)) ፡፡

በ/ በጥያቄ አቀራረብ ላይ መቃወሚያ ሲነሳ ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን ሳይቀበል ለጥያቄው መልስ እንዲሰጥበት ያዘዘ እንደሆነ መቃወሚያው የቀረበበትን ጥያቄ፣ የተሰጠውን መልስ፣ የተቃወመውን ሰው ስም፣ መቃወሚያው ውድቅ የሆነበት ውሳኔ በመዝገቡ ላይ ማስፈር አለበት (ቁ. 270)፡፡

ተ/ አንድ ባለጉዳይ ያቀረበው ምስክር መልሶ በባለጉዳዩ ላይ ቢመሰክር ባለጉዳዩ ይህ ቃል እንዳይመዘገብ ምስክሩም ቃሉን መስጠት እንዲያቆም ፍ/ቤቱን መጠየቅ አይችልም፡፡ ጥያቄው ቢቀርብም ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ሳይቀበል የምስክሩን ቃል መመዝገብ አለበት፡፡ ባለጉዳዩ ጥያቄውን ቢያቆምም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሩን መመርመር መቀጠል ይችላል፡፡

ቸ/ የምስክሩ ቃል የተሰጠው በችሎቱ ቋንቋ ሳይሆን በሌላ ቋንቋ ከሆነ አስተርጓሚ ይመደባል፡፡ አስተርጓሚውም የመተርጐም ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የመኃላ ቃል ወይም በትክክል እንደሚተረጉም የሚያረጋግጥ ቃሉን መስጠት አለበት፡፡ የመኃላ ቃሉም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት "በዚህ ፍ/ቤት የሚሰጠኝን ማስርጃ በእውነትና የችሎታዬን ያህል ልተረጉም እምላለሁ፡፡" የሚል መሆን አለበት፡፡ አስተርጓሚው "እምላለሁ" ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ "እምላለሁ" በማለት ፋንታ "አረጋግጣለሁ" ማለት ይችላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ ተገቢ አይደለም፡፡

ኀ/ የተሰጠው የምስክርነት ቃል በቁ. 269 የተደነገገውን ፎርምና ይዘት ተከትሎ መመዝገብ ለለበት፡፡

**2.4.3. የፍ/ቤቱ ሥልጣን**

ሀ/ ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማት በዋናነት የባለጉዳዮቹ ቢሆንም ለክርክሩ ጠቃሚ መስሎ ከታየው ተከራካሪዎቹ ካቀረቡት ምስክር በቀር ተጨማሪ ምስክር ጠርቶ መስማት ይችላል (ቁ. 264)። ሆኖም ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ምስክር መስማት ያለበት ለፍትህ አሰጣጥ የግድ አስፈላጊ ሲሆንና በውስን ሁኔታዎች ብቻ እንዲሁም ÑKM}˜’~” uTA›" SMŸ< መሆን አለበት።

ለ/ ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝበት ጊዜ ቀድሞ መስክረው የነበሩትን ምስክሮች ፍ/ቤቱ እንደገና አስጠርቶ ማናቸውንም ተገቢ መስሎ የታየውን ጥያቄ ሊጠይቃቸው ይችላል (ቁ. 266)።

ሐ/ በቁ. 265 የተገለፀው ሁኔታ ሲያጋጥም ፍ/ቤቱ የምስክሩን ቃል ባስቸኳይ መቀበል ይችላል።

መ/ ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ፍ/ቤቱ ክርክር የተነሳበትን ማናቸውንም ንብረት ወይም ማናቸውንም ነገር ሥፍራው ድረስ ሄዶ በማየት ለመመርመር ይችላል(ቁ. 272)።

**2.4.4. የምስክር ቃልን ለመስጠት ፈቃደኛ ስላለመሆንና ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል**

ሀ/ ማንኛውም በፍ/ቤት ችሎት የቀረበ ተከራካሪ ወገን ወይም ሌላ ሰው የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ወይም በእጁ የሚገኘውን ወይም በሥልጣኑ ሥር የሚገኘውን የፅሑፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ ሲያዘው በቂ ባልሆነ ወይም በሕግ በማይደገፍ ምክንያት ትዕዛዙን ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ወዲያውኑ ይፈርድበታል። ወይም ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ትዕዛዝ ይሰጣል።

ለ/ በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ በቁ. 480 በተጠቀሰው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል።

ሐ/ በተጨማሪም እምቢተኛውን በወ/መ/ሕ/ቁ. 442 መሠረት ወዲያው መቅጣት ይችላል (ቁ. 481)። ሆኖም ይህን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ምስክሩ ቃሉን ለመስጠት ያልፈለገበትን ምክንያት (ለምሣሌ ጥያቄውን ቢመልስ የወንጀል ክስ ሊያስከትልብኝ ይችላል ብሎ በመፍራት እንደሆነ) ማጣራትና ምስክሩ ቃሉን መስጠቱ አስፈላጊ መሆኑን፣ ቃሉን መስጠቱም ግዴታው መሆኑን፣ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለ ግን የወንጀል ቅጣት ሊወሰንበት እንደሚችል ማስርዳትና አስፈላጊውን ምክር ሁሉ መስጠት አለበት። ፍ/

ቤቱ አስፈላጊውን ማጣሪያ ካደረገና ተገቢውን ምክር ከሰጠ በኋላ ምስክሩ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለና ሌላ አማራጭ የሌለ መስሎ ከታየው የወንጀል ቅጣቱን መወሰን ይችላል፡፡

መ/ ምስክሩ ሐሳቡን ቀይሮ የምስክርነት ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኝነቱን ከገለፀና ቃሉን ከሰጠ ፍ/ቤቱ የወሰነበትን ቅጣት ሊያቀልለት ወይም ቅጣቱን ሙሉ በሙሉ አንስቶለት በተግሳፅ ብቻ ሊያልፈው ይችላል፡፡

ሠ/ ምስከሩ ግልፅ የሆነ የሐሰተኛ ምስክርነት ቃል ከሰጠ ቃሉን ያስተካክል እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተገቢውን ጥረት ካደረገና አስፈላጊውን ምክር ከሰጠው እንዲሁም በሐሰት መመስክር ወዲያው በወንጀል እንደሚያስቀጣው ካስረዳው በኃላ ምስክሩ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለ በወ/መ/ሕ/ቁ.447 መሠረት ምስከሩን ወዲያው መቅጣት ይችላል (ቁ. 481)፡፡

ረ/ ከላይ በፊደል (መ እና ሠ) በተገለፀው መሠረት ቅጣት የተወሰነበት ምስክር በራሱ ፈቃድ ቃሉን ወዲያው ካነሳው ወይም ካስተካከለ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ሲያቀልለት ወይም ቅጣቱን ሙሉ በሙሉ በማስቀረት በተግሳፅ ብቻ ሊያልፈው ይችላል (ወ/መ/ሕ/ቁ. 448)፡፡

ሰ/ የሐሰት ቃል የሰጠው ተከራካሪ ወገን ከሆነ በወ/መ/ሕ/ቁ. 446 መሠረት ወዲያው ቅጣት ሊበይንበት ይችላል፡፡ በዚህም ጊዜ ከላይ በፊደል (መ እና ረ) እና (መ እና ረ) የተመለከቱት ሁኔታዎች እና ጥንቃቄዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡

ሙግትን ሰምቶ እና ምስክሮችን መርምሮ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ

- ✓ ሙግትን ሰምቶ እና ምስክሮችን መርምሮ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ጊዜ፡- አስራ አምስት ቀናት
- ✓ ሙግትን ሰምቶ እና ምስክሮችን መርምሮ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው ከፍተኛ ጊዜ፡- አንድ ወር

### 2.4.5. ፍርድ

የማስረጃ መሰማት ሥርዓት ተጣርቶ ካለቀ በኋላ ተከራካሪ ወገኖች የመዝጊያ (የማጠቃለያ) ቃላቸውን ይሰጣሉ፡፡ ሙግቱን የጀመረው ወገን መጀመሪያ ስለ ክርክሩ አጠቃላይ የመዝጊያ ቃሉን ይሰጣል፡፡ ከዚያ ሌላኛው ወገን ስለ ክርክሩ ያለውን አስተያየት በመዝጊያ ቃል ያቀርባል፡፡ በመጨረሻም ክርክሩን የጀመረው ወገን ለክርክሩ ያለውን ጠቅላላ የመዝጊያ ሐሳብ ያቀርባል (ቁ. 259 እና 273)፡፡

ሀ/ የማስረጃ መስማት ሥርዓቱ ተጣሪቶ ካለቀና ከላይ የተጠቀሰው የመዝጊያ ቃል ከተሰጠ በኂላ ፍ/ቤቱ የፍርድ ውሳኔ ይሰጣል (ቁ. 273)::

ለ/ ለፍርድ ውሳኔው መሠረት ሊሆኑ የሚችሉት ማስረጃዎች፤

- የምስክሮች ቃል (ባለጉዳዮቹ አቅራቢነት ወይም በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ቀርበው ቃላቸውን የሰጡ፣ በምትክ ዳኛ የተሰበሰቡ የምስክሮች ቃል ወይም ከፍ/ቤቱ ውጪ በመኃላ የተሰጡ የምስክሮች ቃል)፣
- በኤክስፐርቶች የተሰጡ ማረጋገጫዎች፣
- በባለጉዳዮቹ ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ የቀረቡ የፅሐፍ ማስረጃዎችና ሰነዶች፣
- በምትክ ዳኛ የተሰበሰቡ ሌሎች ማስረጃዎች፣
- ባለጉዳዮቹ በፅሑፍ ወይም ፍርድ ቤቱ በሚመረምራቸው ጊዜ የሚሰጧቸው የእምነት ቃላት፣
- ፍ/ቤቱ በቁ. 272 መሠረት ባደረገው ምርመራ የተገኙ መረጃዎች፣
- የታወቁ ጉዳዮች (judicial notice)፣
- በሕግ የተወሰደ የህሊና ግምት (legal presumption)፣
- ያንድን ነገር አፈጣጠርና ሂደት ማሳያ (demonstration)፣
- ፍ/ቤቱ በዓይነት እንዲመለከታቸው የሚቀርቡለት ነገሮች (exhibits) ሊያጠቃልል ይችላል::

ሐ/ የእነዚህን ማስረጃዎች ተቀባይነት (admissibility) እና እውነተኛነት (credibility) ፍ/ቤቱ ይወስናል::

መ/ ባለጉዳዮቹ ወይም ወኪሎቻቸው የመክፈቻና የመዝጊያ ንግግር ሲያደርጉ ወይም ምስክሮችን በሚመረምሩበት ጊዜ የሚናገሯቸው ቃላት እንደማስረጃ መወሰድ የለባቸውም::

ሠ/ ከላይ በክፍል (ሥ) (3) ከተጠቀሰው ውጪ ዳኛው ከችሎት ውጭ ያያቸው ወይም የሰማቸው ነገሮች ወይም ያገኛቸው ማስረጃዎች ለውሳኔው መሠረት መሆን የለባቸውም::

ረ/ የቀረበው ክርክር ከተሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ ነገሩ እንዳለቀ ወዲያውኑ ወይም በአጭር ቀነ ቀጠሮ በሚወሰነው ጊዜ በግልፅ ችሎት ፍርድ መስጠት አለበት (ቁ. 180)::

ሰ/ የፍርድ አሰጣጥ፣ የውሳኔው አፃፃፍና ፎርም በቁ. 181 እና 183 በተደነገገው መሠረት መሆን አለበት።

ሸ/ በአንድ የፍርድ ሐተታ ላይ የተያዘው ጭብጥ፣ጭብጡ እንዴት እንደተወሰነና የተወሰነበት ምክንያት መገለፅ አለበት። በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ፍርድ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዋነኛ ጉዳይ ባጭር የሚገልፅ መሆን አለበት (ቁ. 182(1))።

ቀ/ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልፅ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ ለመስጠት አይችልም(ቁ. 182(2))።

በ/ በክርክሩ ላይ ከቀረቡት ብዙ ጭብጦች አንዱ ጭብጥ ብቻ ቢወሰን ሌሎቹንም ጭብጦች የሚያጠቃልል ከሆነ ክርክሩ ባንዱ ጭብጥ ብቻ ሊወሰን ይችላል። ካልሆነ ግን እያንዳንዱ ጭብጥ ለየብቻው ውሳኔ ማግኘት አለበት(ቁ. 182(4))።

**ፍርድ ለመስጠት የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ**

- ✓ ጉዳዩን መርምሮ ፍርድ ለመስጠት እና ለተከራካሪ ወገኖች የውሳኔ ግልባጭ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ ጊዜ፦ 20 ቀናት
- ✓ ጉዳዩን መርምሮ ፍርድ ለመስጠት እና ለተከራካሪ ወገኖች የውሳኔ ግልባጭ የሚያስፈልገው ከፍተኛ ጊዜ፦ አንድ ወር ከ10 ቀናት

## 2.5. ልዩ ሥነ-ሥርዓት

### 2.5.1. በአጭር ሁኔታ ስለሚወሰኑ ክርክሮች (summary Procedures)

ሀ/ ከቁ. 284 እስከ 292 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል።

ለ/ በዚህ ሥርዓት መሠረት ክስ ሊቀርብ የሚችለው በቁ. 284 ሥር በተዘረዘሩ ጉዳዮች ብቻ ነው።

ሐ/ ማመልከቻው በመኃላ ቃል ተደግፎ መቅረብ አለበት (284(ሐ))። የመኃላ ቃሉ ተከሳሹ ለነገሩ ምንም ዓይነት መከላከያ እንደሌለው ከሳሽ የሚያምን መሆኑን መግለፅ አለበት።

- መ/ ፍ/ቤቱ ማመልከቻውን ከተቀበለ በኃላ ለተከሳሹ መጥሪያ እንዲደርሰው ያዛል (ቁ. 285(1)) ።

ሠ/ ተከሳሹ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ፍ/ቤቱን ጠይቆ ካላስፈቀደ በቀር

መከላከያ ሊያቀርብ አይችልም (ቁ. 285(1))፡፡

ረ/ ተከሳሹ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ለፍ/ቤቱ ካላመለከተ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል(ቁ. 285(2))፡፡

ሠ/ ለመከላከል ፈቃድ እንዲሰጥ የሚቀርበው ማመልከቻ በቁ. 286 መሠረት በመኃላ ቃል ተደግፎ መቅረብ አለበት፡፡

ሸ/ ተከሳሹ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካጣ ወዲያው ለከሳሹ ይፈረዳል (ቁ. 287)፡፡

ቀ/ ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ግን ተከሳሹ መከላከያ እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል፡፡ ክርክሩም የሚመራው ፍ/ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ወይም እንደመደበኛው ክስ በቀጥታ ሊሆን ይችላል(ቁ. 290 እና 291)፡፡

በ/ ፍርድ ከተሰጠ በኃላ ለተከሳሹ የተላከው መጥሪያ በአግባቡ ያልደረሰው ከሆነ ፍ/ቤቱ ፍርዱ ከመፈፀም እንዲቆይ በማድረግ ተከሳሹ ቀርቦ እንዲከላከልና ስለ ጉዳዩም አፈፃፀም ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል(ቁ.292)፡፡

### 2.5.2. የተፋጠነ ሥነ ሥርዓት (Accelerated Procedure)

ሀ/ ከቁ. 300 እስከ 314 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል፡፡

ለ/ በመሠረቱ ይህ ሥርዓት የሚፈቀደው በቁ. 305 እና 307-314 በተዘረዘሩት ጉዳዮች ነው (ቁ. 300(11))፡፡

ሐ/ ሆኖም ግን ጉዳዩ በዚህ ሥርዓት መታየት የለበትም ብሎ ፍ/ቤቱ መከልከል የሚችል ሆኖ ከላይ በተጠቀሱት ቁጥሮች ከተደነገጉት ጉዳዮች ውጪም ቢሆኑ ሌሎች ጉዳዮች በዚህ ሥርዓት መታየት ይችላሉ (ቁ. 300 (1))፡፡

መ/ ማመልከቻው የሚቀርበው በቁ. 301 የተደነገገውን ሁኔታ አሟልቶና በመኃላ ቃል ተደግፎ መሆን አለበት፡፡

ሠ/ ማመልከቻው በቁ. 302 ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ውድቅ ሊሆን ይችላል፡፡

ረ/ ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጠው በማመልከቻው ላይ በተገለፀው እና አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር ያቀረባቸውን ሰነዶችና የፅሑፍ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው(ቁ. 303(2) እና 301(3))፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ የሆነ ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (303 (3)) ፡፡

ሠ/ ሕጉ በሌላ አኳኃን እንዲፈፀም የሚያዝ ካልሆነ በቀር በዚህ ሥርዓት በሚሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ አይቻልም (ከቁ. 309-311 ከተመለከተው በቀር) (ቁ. 306 (1))፡፡

ሸ/ ይግባኝ የሚፈቀድ ከሆነ ይግባኙ ፈርድ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት (ቁ. 306 (2))፡፡

በአጭር እና በተፋጠነ ስነ- ስርዓት የሚወሰኑ ክርክሮች ሂደትን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ

- ✓ ዝቅተኛ የሚያስፈልገው ጊዜ፡- አንድ ወር
- ✓ ከፍተኛ የሚያስፈልገው ጊዜ፡- ሁለት ወር ከ15 ቀናት

## 2.6. የንግድ ህጉን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ሂደት መቋጫ የጊዜ ስታንድርዶች ወሰንና ተጠባቂ ውጤት በመቶኛ

### 2.6.1. የንግድ ማህበራትን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች

በንግድ ችሎቶች የሚታዩ የንግድ ጉዳዮች ከተከፈቱበት ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ወይም በስድስት ወራት ውስጥ እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆኖ አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- ከቀረቡት ጉዳዮች 90% የሚሆኑት ጉዳዮች በ150 ቀናት ወይም በአምስት ወራት ውስጥ እልባት ያገኛሉ፤
- በመጨረሻ 100% በ180 ቀናት ወይም በስድስት ወራት ውስጥ ተጠቃለው እልባት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

### 2.6.2. ቼክ፣ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች

በንግድ ችሎቶች የሚታዩ ቼክ እና የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ከተከፈቱበት ቀን ጀምሮ በ120 ቀናት ወይም በአራት ወራት ውስጥ እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆኖ አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ተመላክቷል፡፡

- ከቀረቡት ጉዳዮች 90% የሚሆኑት ጉዳዮች በ90 ቀናት ወይም በሶስት ወራት ውስጥ እልባት ያገኛሉ፣
- በመጨረሻ 100% በ120 ቀናት ወይም በአራት ወራት ውስጥ ተጠቃለው እልባት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

#### 2.6.3. የውል ግንኙነትን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች

በንግድ ችሎቶች የሚታዩ የውል ጉዳዮች ከተከፈቱበት ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ወይም በስድስት ወራት ውስጥ እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆኖ አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- ከቀረቡት ጉዳዮች 90% የሚሆኑት ጉዳዮች በ150 ቀናት ወይም በአምስት ወራት ውስጥ እልባት ያገኛሉ፤
- በመጨረሻ 100% በ180 ቀናት ወይም በስድስት ወራት ውስጥ ተጠቃለው እልባት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

#### 2.6.4. በአጭር ሥነ-ሥርዓት መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮች

ቼክ እና የሚተላለፉ ገንዘብ ሰነዶችን ከሚመለከቱ ጉዳዮች ውጪ በንግድ ችሎት የሚታዩ ሌሎች በአጭር ስነ ስርዓት የሚታዩ ጉዳዮች ከተከፈቱበት ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ወይም በሦስት ወራት ውስጥ እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆኖ አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ተመላክቷል፡፡

- ከቀረቡት ጉዳዮች 95% የሚሆኑ ጉዳዮች በ60 ቀናት ወይም በሁለት ወራት ውስጥ እልባት ያገኛሉ፣
- በመጨረሻ 100% በ90 ቀናት ወይም በሦስት ወራት ውስጥ ተጠቃለው እልባት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

### 2.7. ለጊዜው ስለሚሰጡ ማገጃዎችና ሌሎች ትዕዛዞች (Provisional Remedies)

#### 2.7.1. ከፍርድ በፊት ንብረትን ማስከበር (ቁ 151-153)

ሀ/ በአንቀፅ 151(1) (ሀ) ና (ለ) ሥር የተዘረዘሩት ሁኔታዎች መኖራቸውን ከሳሹ ወይም የተከሳሽ ከሳሹ በመኃላ ቃል በተደገፈ አቤቱታ ወይም በሌላ ሁኔታ ማስረዳት ይችላል፡፡

ለ/ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን መርምሮ እውነት መሆኑን ካረጋገጠ ተከሳሹ ዋስትና እንዲሰጥ ወይም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንብረት ወይም ግምቱ እንዲቀርብ በወሰነው ጊዜ እንዲያመጣ ወይም ደግሞ ከሚያዘው ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ለሚሰጠው ፍርድ ተመዛዛኝ የሚሆን መጠን ያለው ገንዘብ ወይም ንብረት በፍ/ቤቱ እንዲቀመጥ ወይም ይህን መያዣ የማይሰጥበትን ምክንያት ቀርቦ እንዲያስረዳ ያዛል (ቁ 151(1) (ለ))፡፡

ሐ/ የሚያዘው ንብረት የግድ ከሳሹ ያመለከተው ሁሉ ሳይሆን ከክሱ ገንዘብ

ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት (ቁ 151(3) እና (1)) ። እንዲሁም በቁ. 404 እና በሌላ ሕግ እንዳይከበር የተወሰነ ንብረት መያዝ የለበትም።

መ/ ተከሳሹ ዋስ ያልጠራበትን ምክንያት በሚገባ ካስረዳ ወይም የሚፈለግበትን መያዣ ከሰጠ ንብረቱ ይለቀቅለታል። (ቁ. 152 (2) እና 153(4))።

ሠ/ ንብረቱ በሚከበርበት ጊዜ የሦስተኛ ወገኖች መብት መጠበቅ አለበት (ቁ 153(2)(3)፣ 428-421እና 443)።

## 2.7.2. ለጊዜው የሚሰጥ የማገድ ትዕዛዝ (ቁ 154-159)

ሀ/ በቁ.154 (ሀ) ና (ለ) ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች በመኃላ በተደገፈ ቃል ወይም በሌላ መንገድ ሲረጋገጡ ነገሩ በፍርድ እስኪወሰን ድረስ ወይም ሌላ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ክርክር የተነሳበት ንብረት እንዳለ እንዲቆይ፣ ከመጥፋት እንዲድን እንዳይበላሽ ለሌላ ሰው ተላልፎ እንዳይሰጥ ወይም ሌላ ስፍራ እንዳይዘዋወር ወይም እንዳይባክን ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ትዕዛዝ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

ለ/ ውል ወይም ሌላ ግዴታ ተደጋግሞ እንዳይፈርስ ወይም ለማፍረስ የተወሰደው እርምጃ እንዳይቀጥል የሚሰጠው ያማገጃ ትዕዛዝ በቁጥር 155 መሠረት ይፈፀማል።

ሐ/ የማገጃ ትዕዛዝ ያለማክበር የፍትሐብሔረና የወንጀል ኃላፊነትን ሊያስከትለ ይችላል (ቁጥር 156)።

መ/ የማገጃ ትዕዛዝ መሰጠት ያለበት በተቻለ መጠን ማመልከቻው ለሌላቸው ወገን ከደረሰው በኂላ ነው። ሆኖም ግን እግዱ መዘግየቱ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መስሎ ሲታይ ብቻ ነው (ለምሳሌ ንብረቱ የሚጠፋ ወይም የሚበላሽ ሲሆን) የማገጃ ትዕዛዝ በቁጥር 158 በተደነገገው መሠረት ሊነሳ ሊሠረዝ ወይም ሊሻሻል ይችላል።

## 2.8. ስለ ፍርድ አፈፃፀም

### 2.8.1. ፍርድ እንዲፈፅም ስለሚቀርብ ማመልከቻ

ሀ/ ፍርድን ለማስፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻ በቁ.378 የተደነገጉትን ፍሬ ነገሮች መያዝ አለበት።

ለ/ ማመልከቻው እንደ ፍርዱ ብቻ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ እንጂ በዋናው ፍርድ ላይ ያልተገለፀ አዲስ ጥያቄ መጨመር የለበትም፡፡ ፍ/ቤቱም አዲስ ጥያቄ ከቀረበ ማስተናገድ የለበትም /በአፈፃፀም ክርክር ጊዜ የደረሰውን ወጪና ኪሳራ በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር /

ሐ/ ማመልከቻው በድፍኑ እንደ ፍርዱ ይፈፀምልኝ የሚል ሳይሆን እንዲፈፀምለት የሚፈልገውን ጉዳይ በዝርዝርና በግልፅ መያዝ አለበት፡፡

መ/ ማመልከቻው ፍርዱ እንደተፈረደ ወዲያውኑ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ነገር ግን የፍርድ ባለ ዕዳው እንደ ፍርዱ ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆኖ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ ቢፈቀድለት ማመልከቻው የሚቀርበው በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካልፈፀመ ነው (ቁ.378(2) )፡፡

ሠ/ አንድ የተለየ ነገር እንዲፈፀም ፍ/ቤቱ ከሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ በቀር ፍርዱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ አስር አመት ካለፈ የቀረበ የአፈፃፀም ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተከታታይ የሚፈፀም ግዴታ ከሆነ የአስር ዓመት ጊዜው የሚውቀጠረው ግዴታው መፈፀም ከቆመበት ቀን ጀምሮ ነው /ቁ.384/፡፡

ረ/ የአፍፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ ማመልከቻው አስፈላጊውን ሥርዓት አሟልቶ የቀረበ መሆኑ መረጋገጥ አለበት /ቁ.385/፡፡

ሰ/ ጉድለት ያለበት ከሆነ ማመልከቻው ለባለ ጉዳዩ ይመለሳል ወይም ተሟልቶ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ያዛል፡፡

ሸ/ ማመልከቻው ተሻሽሎና ተሟልቶ ከቀረበ መጀመሪያ ቀርቦ በነበረበት ቀን ሕጋዊ ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡ /ማመልከቻው መጀመሪያ በቀረበበት እና ተሻሽሎ በቀረበበት ቀን መሀል ያለው ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር ከግምት ውስጥ አይገባም/

ቀ/ ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኛ ከመጥሪትያ ጋር ተያይዞ ለፍርድ ባለዕዳው ይላል፡፡ የፍርድ ባለዕዳው በመጥሪያው ላይ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ቀረቦ ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ይታዘዛል /ቁ.386/11/፡፡

## 2.8.2. ፍርድ እንዲፈፀም የሚገደድበት ሁኔታ

በመሠረቱ በአንድ ፍርድ ላይ ይግባኝ መቅረቡ ብቻ ፍርዱ እንዳይፈፀም አያግድም፡፡ ሆኖም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፍርዱ አፈፃፀም ለጊዜው እንዲታገድ ማዘዝ ይችላል፡፡ /ቁ.332/

ሀ/ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤትም ክርክሩ በይግባኝ ቀርቦ ከመታየቱ በፊት ፍርዱ ቢፈፀም ክርክር በተነሳበት ንብረት ላይ ከፍ ያል ጉዳት የሚደርስ መሆኑን ከገመተ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ፍርድ እንዳይፈፀም ሊያግድ ይችላል (ቁ.333)።

ለ/ በቁ.371 እስከ 376 በተደነገገው መሰረት ፍርዱን እንዲያስፈፅም ለሌላ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከሆነ ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት በቁ.333 መሠረት የሰጠው የሕግ ትዕዛዝ ፍርዱን እንዲያስፈፅም በታዘዘው ፍ/ቤት ላይም ተፈፃሚ ይሆናል /ቁ.376/4/።

ሐ/ ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘው ፍ/ቤቱ ራሱ የፍርድ ባለዕዳው በቂ ምክንያት ካቀረበ አቤቱታውን ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት እስኪያቅርብ በቂ ለሆነ ጊዜ ብቻ የሚቆይ የአፈፃፀም ዕገዳ ሊሰጥ ይችላል (ቁ.376(1))።

መ/ የይግባኝ ባዩ ፍ/ቤት ውይም ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት በቁ.334 በተደነገገው መሠረት ፍርዱ ለጊዜው እንዳይፈፀም ሊያግዱ ይችላሉ። ፍ/ቤቱ ቀኑን የሚያረዝም ተጨማሪ ትዕዛዝ ካልሰጠ በቀር ዕገዳው የሚቆየው ለ15 ቀን ብቻ ነው።

ሠ/ በቁ.332 እስከ 334 በተደነገገው መሠረት ዕገዳ ሊሰጥ የሚችለው በቁ.335 የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

ረ/ ፍርድ የማገድ ትዕዛዝ የሚሰጠው ማመልከቻው ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ከተሰማ በኋላ ነው። ሆኖም በመሀላ የተደገፈ ማመልከቻ ከቀረበ ተከራካሪዎቹ ባሉበት ነገሩ እስኪሰማ ድረስ ያማገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል /ቁ.335/4/።

ሸ/ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በፍርድ ባለገንዘቡ ላይ የፍርድ ባለ ዕዳው ሌላ ክስ ያቀረበበት እንደሆነ ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍ/ቤት ራሱ የፍርድ ባለዕዳው በቂ ዋስትና ወይም መያዣ እንዲሰጥ ካደረገ በኋላ ለክርክሩ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ፍርዱ ከመፈፀሙ አግዶ እንዲቆይ ለማዘዝ ይችላል /ቁ.377/።

ቀ/ ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች በማናቸውም መንገድ የፍርድ አፈትፃፀሙ ካልታገደ /እኒዲፈፀም ከታዘዘ/ ይግባኝ ባዩ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በቂ ምክንያት ሲያቀርብለት በፍርዱ አፈፃፀም ምክንያት የተወሰደው ነገር እንዲመለስ ዋስትና እንዲሰጥ ወይም የተወሰደውን ንብረት ለመሸፈን የሚችል ግምት ያለው መያዣ እንዳያስቀምጥ ፍ/ቤቱ ለማዘዝ ይችላል

(ቁ.336)፡፡

**2.8.3 የፍርድ ባለዕዳውን ስለመመርመር**

ሀ/ የፍርድ ባለዕዳው በቀረበበት ቀን ፍ/ቤቱና የፍርድ ባለ ገንዘቡ ጥያቄ ያቀርቡለታል፡፡

ጥያቄው የሚቀርበውም እንደፍርዱ የማይፈፀምበትን ምክንያት ለማጣራት ነው /ቁ.386/2/፡፡

ለ/ የፍርድ ባለዕዳው ለሚጠየቀው ጥያቄ መልስ የሚሰጠው በፅሑፍ ሳይሆን በቃል ነው፡፡ የሚስጠው መልስ ወይም መግለጫ እውነት መሆኑን በመሀላ ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሐ/ የፍርድ ባለዕዳው የሚያቀርበው ክርክር ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወምበትን ምክንያት የሚያስረዳ /ለምሳሌ በፍርድ የተወሰነው ዕዳ በሚገባ ተከፍሏል ወይም ከፍርድ ባለዕዳነት ነፃ ሆኛለሁ ወይም የፍርድ ባለዕዳነቱን ፈፅሜአለሁ ወይም ፍርዱ በይርጋ ታግዷል እና የመሳሰሉት / ብቻ መሆን አለበት፡፡ በፍርድ ስላለቀው ዋናው ጉዳይ እንደገና መከራከር አይቻልም፡፡ በፍርድ የተወሰነው ዕዳ በሚገባ ተከፍሏል የሚለው መቃወሚያ ከፍርዱ በኂላ የተከፈለን እንጂ በፊትም ተከፍሎ እያለ በስህተት ተፈርዶብኛል የሚለውን ክርክር አይጭምርም፡፡

መ/ የፍርድ ባለዕዳው ካልቀረበ ወይም ቀርቦ በቂ ምክንያት ካልሰጠ ፍርዱ እንዲፈፀም ወዲያውኑ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ ፍ/ቤቱም ፍርዱ የሚፈፀምበትን ተስማሚ መንገድ ወስኖ የፍርድ ማስፈፀም ትዕዛዝ ለአስፈፃሚው ያስተላልፋል /ቁ. 386/3/፣392/1/፣392/3/፡፡

ሠ/ የፍርድ ባለዕዳው ፍርዱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመፈፀም የማይቻል ከሆነ ፍርዱ እንዲፈፀም ትዕዛዝ አይሰጥም፡፡ በዚህ ጊዜ በቁ.387 እና 389 የተደነገጉት የማሰርና በማረፊያ ቤት የማቆየት ትዕዛዞችም ተፈጥፃሚ አይሆኑም፡፡ ሆኖም ለመፈፀም ችሎታ በሚያገኝበት በማናቸውም ጊዜ እንዲፈፀም ማዘዝ ይቻላል፡፡ በዚህ ጊዜ በቁ.384 የተደነገገው የይርጋ ጊዜም አይቆጠርም፡፡

ረ/ የፍርድ ባለዕዳው እንዲቀርብ በታዘዘበት ቀን ካልቀረበ የፍርዱን አፈፃፀም በተመለከተ አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት እንጂ ባለዕዳው ታስሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ግዴታ አይደለም፡፡ የማሰር ትዕዛዝ የሚሰጠው በቁ.386/4/ እና በቁ.387 በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡፡

ሰ/ በቁ.386/4 መሠረት ማመልከቻው የቀረበው ገንዘብ እንዲከፈል የተፈረደ ፍርድ እንዲፈፀም ከሆነና የፍርድ ባላደራው በመጥሪያው መሠረት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ታስሮ እንዲቀርብና ለሚደረግለት ጥያቄ ወይም ምርመራ መልስ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ ማዘዝ ይችላል፡፡ የፍርድ ባለዕዳው በቁ.387 የተመለከተውን ድርጊት ቢፈፀምም ባይፈፀምም ፍርዱ ገንዘብ እንዲከፈል የሚያዝ ከሆነ በቁ.386/4/ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሸ/ ቁ.387 ተፈፃሚ የሚሆነው ፍርዱ ማናቸውም ዓይነት ቢሆን የፍርድ ባለዕዳው ፍርዱ እንዳይፈፀም መሰናክል በመፍጠር ወይም የፍርዱን አፈፃፀም ለማዘግየት ንብረቱን ከፍ/ቤቱ ሥልጣን ክልል ውስጥ ለመሸሽ ወይም ራሱ ከፍ/ቤቱ ሥልጣን ክልል ውስጥ ለመውጣት ለመሸሽና ለመሠወር ያቀደ መሆኑን የሚያረጋግጥ በመሃላ ቃል የተደገፈ ማመልከቻ ሲቀርብ ነው፡፡

ቀ/ በቁ.386/4/ ወይም 387 መሠረት የማሰር ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ የፍርድ ባለዕዳው የሚፈልግበትን ነገር በፍርዱ መሠረት በፈቃዱ ከፈፀመ የማሰር ትዕዛዙ ተፈፅሚ ምሆን የለበትም /ቁ.388/፡፡ ፍ/ቤቱም የማሰር ትዕዛዙ ላይ እንዲሁም የማሰር ትዕዛዙን እንዲያስፈፅም ለታዘዘው ባለሥልጣን ይህን ነጥብ ግልፅ ማድረግ አለበት፡፡

በ/ የፍርድ ባለዕዳው በደረሰው መጥሪያ መሠረት በራሱ ፈቃድ ከቀረበ ወይም በቁ.386/4/ ወይም 387 በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ታስሮ ከቀረበና ፍ/ቤቱ ብቁ.386/2/ መሠረት ተገቢውን ምርመራ ከፈፀመ በኋላ የፍርድ ባለእዳው እንደ ፍርዱ መፈፀም የሚቻል ሆኖ ሳለ ያለበቂ ምክንያት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ብቻ የማይፈፅም መሆኑን ከተረዳ የፍርድ ባለ ዕዳው እስከ ስድስት ወር ድረስ በማረፊያ ቤት ታስሮ እንዲቆይ ሊወሰንበት ይችላል፡፡ ባለእዳው በሌላ ምክንያት ታስሮ ካለ ግን የማሰር ትዕዛዙ መሰጠት የለበትም /ቁ.389/11/፡፡

ተ/ በቁ.389/1/ መሠረት የሚሰጠው የስራ ትዕዛዝ ዓላማው ባለዕዳው እንደፍርዱ እንዲፈፀም ለማስገደድ ብቻ ነው፡፡ ባለዕዳው የወንጀል ጥፋት ፈፅሞ እንደተቀጣ አይቆጠርም፡፡ በሪከርድም አይያዝበትም፡፡

ቸ/ በቁ.389/1/ መሠረት የስራ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ባለዕዳው እንደ ፍርዱ ቢፈፀም ወይም ባለ ገንዘቡ ከጠየቀ ትዕዛዙ ተፈፀሚ አይሆንም፡፡ ይህ ሁኔታ የተፈፀመው ባለዕዳው እስር ቤት ከገባ በኋላ ከሆነም ከእስራት መለቀቅ አለበት /ቁ.389/2/፣388/2/፣390/1፡፡

ኀ/ ቁ.390/1/ መሠረት ከእስራት የተለቀቀ ባለዕዳ በዚያው ጉዳይ እንደገና

መታሰር የለበትም /ቁ.390/2/::

ነ/ ባለዕዳው መያዙ ወይም ተይዞ መለቀቁ በፍርዱ መሠረት በሙሉ ወይም በከፊል ከሚጠየቀው ዕዳ ነፃ አያደርገውም /ቁ.391/::

## 2.9. የፍርድ አፈፃፀም ሥርዓት

### 2.9.1 ንብረትን ስለ ማስከበር

ሀ/ ንብረት እንዲከበር የሚቀርብ ማመልከቻ በቁ.379 ሥር የተመለከቱትን ነገሮች አሟልቶ መቅረብ አለበት::

ለ/ መከበር የሚችሉና የማይችሉ እንዲሁም የሚከበሩበት ሥርዓት ከቁ.404 እስከ 417 በተደነገገው መሠረት ይመራል::

ሐ/ በቁ.404 ወይም በሌላ ሕግ እንዳይከበሩ እና በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት እንዳይወሰዱ የተከለከሉ ንብረቶች መከበር የለባቸውም::

መ/ የሚከበረው ወይም የሚሸጠው ንብረት ግምት በተቻለ መጠን በፍርዱ ላይ ከተገለፀው የገንዘብ ልክ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት /ቁ.394/2/:: ተመጣጣኝ ያልሆነ ንብረት ካልተገኘ ግን ማነኛውም ንብረት ተከብሮ ይሸጣል እንጂ በዚህ ምክንያት የባለመብቱ መብት መነካት የለበትም::

ሠ/ ንብረት ከተከበረ በኃላ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት የሆነው ፍርድ ከተፈፀመ ወይም ፍርዱ የተሻረ ከሆነ ንብረቱ እንዲያዝ የተሰጠው ትዕዛዝ ወዲያው እንደተሻረ ይቆጠራልም /ቁ.415/

### 2.9.2 በተከበረ ወይም በተያዘ ንብረት ላይ ሦስተኛ ወገኖች የሚያቀርቡት መቃወሚያ

ሀ/ በንብረቱ ላይ ቀዳሚ መብት አለኝ የሚሉ ሦስተኛ ወገኖች የንብረቱን መከበር ወይም መያዝ በመቃወም ፍርዱን ለሚያስፈፅመው ፍ/ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላሉ /ቁ.418

ለ/ በቁ.418 መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ በአፈፃፀም የተያዘው ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ነው እንጂ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት የሆነው ውሳኔ ያለአግባብ የተሰጠ ስለሆነ ይሠረዝልኝ የሚል መሆን የለበትም ጥያቄው ዋናውን ውሳኔ የሚመለከት ከሆነ ተቃውሞ የሚቀርብውና የሚታየው በቁ.358 እና በተከታዮቹ መሠረት ነው እንጂ በቁ.418 አይደለም

ሐ/ በቁ.418 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ በቂ ባልሆነ ምክንያት ከዘገየ ተቀባይነት አይኖረውም::መዘግየቱ የሚወሰነው እንደ ነገሩ አካባቢ ሁኔታ ነው:: ሆኖም ንብረቱ ከተሸጠ በኃላ መቅረብ አይችልም /በቁ.445 የተደነገገው እንደተጠበቀ ነው/::

መ/ ፍ/ቤቱ ማመልከቻውንና ማስረጃውን ከመረመረ በኃላ አቤቱታውን መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል /ቁ.419/::

ሠ/ ፍ/ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገው አመልካቹ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ ይችላል /ቁ401/::ሁነታው የሚፈቅድ ከሆነም በቁ.358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል::

ረ/ የተያዘው ወይም የተከበረው ንብረት የሦስተኛ ወገን የመያዣ መብት ያለበት ከሆነ የሦተኛ ወገኖች መብት ተጠብቆ አፈፃፀሙ ይቀጥላል እንጂ በዚህ ምክንያት ንብረቱን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በሕብረት የያዙትና ያልተከፋፈሉት ከሆነ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ ይችላል /ቁ.420 እና 443/

## 2.9.3 ለፍርድ አፈፃፀም ንብረትን የመሸጥ ሥ/ሥርዓት

ሀ/ የመሸጥ ሥ/ሥርዓት ከቁ.442 እስከ ቁ.449 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል::

ለ/ ከቁ.422 እስከ 431 የተነገሩት በሁሉም የሽያጭ ዓይነቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው::

ሐ/ ከቁ.432 እሰከ 438 ያሉት በተለይ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ብቻ የሚመለከቱ ናችው::

መ/ ከቁ.439 እስከ 449 ያሉት በተለይ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ናችው::

ሠ/ ማንኛውም ንብት በአፈፃፀም የሚሸጠው በሐራጅ ሽያጭ ነው:: ሆኖም በፍርድ ባለዕዳውና ባለገንዘቡ በስምምነት እንዲሸጥ ፍ/ቤቱ ለማዘዝ ይችላል::

ረ/ ንብረቱ ሐራጅ እንዲሸጥ ከተወሰነ የሽያጩ ማስታወቂያ ለህዝብ መግልፅ አለበት::ማስታወቂያውም ንብረቱ በሚገኝበት አቅራቢያ ወይም ግልፅ ሆኖ ሊታወቅና ሊሰማ በሚችልበት ዘዴና በማናቸውም ልማዳዊ ዓይነት ባደባባይ በመንገር ወይም በመለጠፍ ሊፈፀም ይችላል(ቁ425(1)እና(414(2)) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማስታወቂያው በጋዜጣ መውጣት አለበት/ቁ425/2/::

ሰ/ ማስታወቂያው በቁ423 ሥር የተዘረዘሩትን መግለጫዎች አሟልቶ መያዝ አለበት

ሸ/ የፍርድ ባለዕዳው ከዚህ አስቀድሞ እንዲሸጥ ካልተስማማ በቀር የሚንቀሳቀስ

ንብረት ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን አንስቶ 15 ቀን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ደንሞ 30 ቀን ሳይቆይ በሐራጅ ሊሸጥ አይችልም(ቁ426)፡፡

ቀ/ ነገር ግን ንብረቱ ቶሎ የሚበላሽ ከሆነ ወይም ለጥበቃው የሚያስፈልገው ወጪ ከዕቃው ዋጋ የሚበልጥ ንብረት ከሆነ ከላይ የተጠቀሰውን ጊዜ መጠበቅ ሳያስፈልግ ንብረቱ ወዲያሁኑ ሊሸጥ ይችላል/ቁ426፤406/2/፡፡

በ/ የሐራጅ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት የፍርድ ባለዕዳው የሚፈለግበትን ዕዳ በሙሉ ከከፈለ የሐራጅ ሽያጭ ይቆማል/ቁ427/

ተ/ በመጀመሪያው ጨረታ ማስታወቂያ ላይ በተገለፀው የዋጋ ግምት ንብረቱን የሚገዛ ገዥ ካለተኘ ሁለተኛ ጨረታ እንዲደረግ ይታዘዛል(ቁ428)፡፡

ቸ/ ሁለተኛው የሽያጭ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀመው ለመጀመሪያው ጨረታ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት ነው(ቁ.428(1))፡፡ሆኖም ግን የጨረታ መነሻ ዋጋ የሚሆነው የመጀመሪያው ጨረታ ግምት ሳይሆን ከዚያ በታችም ቢሆን በሁለተኛው ጨረታ ንብረቱ የሚሸጠው ከቀረቡት ተጫራቾች ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርበው ተጨራች ነው፡፡

ኀ/ የሚንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ሲሸጥ ሽያጩ ከሥርዓት ውጪ መፈፀሙ ሽያጩን አያፈርሰውም፡፡ሆኖም ጉዳት የደረሰበት ወገን ጉዳቱ አድራሹ ካሳ እንዲከፍለው መጠየቅ ይችላል/ቁ435/፡፡

ነ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ሲሸጥ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የተፈፀመ ከሆነ ግን የፍርድ ባለገንዘቡ ወይም መብቱ የሚገባው ሌላ ሰው ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ መጠየቅ ይችላል፡፡ሽያጩ የሚፈርሰው ከሥርዓት ውጪ ስለተፈፀመ ብቻ ሳይሆን ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም የማታለልና የማጭበርበር ሥራ ተፈፅሞ ሲገኝና ይህም በአመልካቹ ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሰበት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው/ቁ.445/፡፡

ኘ/ እዲሸጥ የተወሰነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ከመሸጡ በፊት በዚሁ ንብረት ላይ መብት ያገኘ ሰው ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ማመለልከት ይችላል/ቁ.444/፡፡

አ/ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲሰጥ ከታዘዘ በኃላ የፍርድ ባለዕዳው ያንኑ ንብረት በማከራየት ወይም በሌላ መንገድ ዕዳውን ለመክፈል እንደሚችል ማረጋገጫ ካቀረበ ፍ/ቤቱ በቂ ጊዜ ሰጥቶት ሽያጩ ለጊዜው እንዲታገድ ለማዘዝ ይችላል/ቁ.439/፡፡

ከ/ በፍርድ ምክንያት ንብረት እንዲተላለፍ የተሰጠውን ትዕዛዝ የመቃወም ወይም የእምቢተኝነት ድርጊት ሲፈፀም ፍ/ቤቱ ከቁ.450 እስከ 455 በተደነገገው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል:: እታ

**የፍርድ አፈፃፀም ሂደትን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው የጊዜ ስታንዳርድ**

የፍርድ አፈፃፀም ሂደትን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው ዝቀተኛ ጊዜ፦ አንድ ወር

የፍርድ አፈፃፀም ሂደትን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው ከፍተኛ ጊዜ፦ ሦስት ወር

## 2.10 ልዩ ልዩ ጉዳዮች(Miscellaneous Issues)

### 2.10.1 አቤቱታ ስለማሻሻል

ሀ/ ማሻሻያው የክሱን ወይም የመከላከያውን አቤቱታ በማብራራት ክርክሩን በተሻሻለ ሁኔታ የሚገልፅ እና ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ ከተገኘ በተከራካሪውቹ ጥያቄ ወይም በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ማንኛዉም አቤቱታ ሊሻሻል ይችላል(ቁ 91)::

ለ/ ማሻሻያው መከናወን ያለበት ከፍርድ በፊት ነው::

ሐ/ አቤቱታው ሲሻሻል ፍ/ቤቱ ስለ ሚኪሳራው አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት አለበት::

መ/ የክሱ መሻሻል ነገሩን በመጀመሪያ ከቀረበለት ፍ/ቤት ስልጣን በላይ ያደረገው ከሆነ የመጀመሪያ ፍ/ቤት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ያስተላልፋል:: ጉዳዩ የተላለፈለት ፍ/ቤትም የነገሩን መስማት ይቀጥላል::

### 2.10.2 ስለ ጊዜ አወሳሰንና ስለ ቀጠሮ

ሀ/ አንድ ነገር የሚፈፅምበት ጊዜ በሕግ ካልተወሰነ ፍ/ቤት የነገሩን ሁኔታ በማየት በቂ መስሎ የታየውን ጊዜ መወሰን ይችላል(ቁ.192(1)

ለ/ በሕግ የተወሰነውን ጊዜ ግን በሌላ አኳኋን ተገልፆ ካልተወሰነ በቀር ማሳጠር ወይም መሰረዝ አይቻልም(ቁ.192(2)::

ሐ/ በሕግ የተወሰነውን ሳይሆን በፍ/ቤት የተሰጠውን ጊዜ በከባድ ምክንያት ብቻ ማስረዘም ይቻላል(ቁ.194 እና196)::

መ/ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ አንድ ነገር እዲፈፀም ከተወሰነው ጊዜ በኃላ ቢፈፀምም እንዳልተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል (ቁ.195)፡፡

ሠ/ ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ አንድን ጉዳይ ለመፈፀም ቀጠሮ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለመፈፀም በቂ ሆኖ የሚገመት ጊዜ በመወሰን ቀጠሮ ይሰጣል(ቁ197(1))፡፡

ረ/ ምስክር መስማት የተጀመረበት ክርክር ሲሆን ለምስክርነት የተጠሩትን ሁሉ ሰምቶ እስኪ ጨርስ ፍ/ቤቱ በየለቱ አደሪ የሚሆን ቀጠሮ እየሰጠ ሥራውን ማከናወን አለበት(ቁ297(3))፡፡

ሰ/ የተከራካሪዎቹ ወገኖች ጠባቃ ወይም ነገር ፈጅ ባለመቅረቡ ምክኒያት ቀጠሮ አይሰጥም(ቁ197(4))፡፡

ሸ/ ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ ጉዳዩ ባይፈፀም ፍ/ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በዚያው ቀን ቀጠሮ የመሰለውን ውሳኔ ለመስጠት ይችላል(ቁ199(1)፡፡

ቀ/ ጉዳዩ ስይፈፀም የቀረው በተከራካሪዎቹ ጉድለት ካልሆነ ግን ፍ/ቤቱ ሌላ ቀጠሮ መስጠት አለበት(ቁ199(2)፡፡

### 2.10.3 በኪሣራ ስለሚከፈል ገንዘብ የሚሰጥ ዋስትና

ሀ/ ተከሳሹ ለደረሰበት ወይም ሊደርስበት ይችላል ተብሎ ለሚገመተው ኪሳራ ከሳሹ በቂ መያዣ የመስጠት ወይም ዋስ የመጥራት ግዴታ አለበት(ቁ.201(1))፡፡

ለ/ ይህን ግዴታ አለመፈፀም መዝገቡን ያዘጋል (ቁ 201(1))፡፡

ሐ/ ረቺው ያቀረበውን የወጪ ዝርዝርና ማስረጃ እንዲሁም ግራናቀኙየሚያደርጉትን ክርክር ከመረመረ በኃላ በፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል(ቁ463እና 464)፡፡

መ/ በቁ 463 እና 464 መሠረት ከሚወሰነው ወጪና ኪሳራ በተጨማሪ በቁ 465 በተዘረዘሩ ሁኔታዎች ፍ/ቤቱ ለተጎጂው ካሳ መወሰን ይችላል፡፡ወጪና ኪሳራውን ሳይጨምር የሚፈርድው ካሳ ከ500 ብር መብለጥ የለበትም፡፡

ሠ/ በወጪና ኪሳራው ውሳንኔ ላይ ብቻ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል(ቁ466)፡፡

## 2.11. ፍርዱን ወይም ትዕዛዙን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ የሚፈፅማቸው ማረሚያዎች ወይም ማስተካከያዎች (Review by Court of Rendition)

## 2.11.1.ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የተፈፀሙ ጉዳዮች

አንዳንድ ከሥርዓት ውጪ የተፈፀሙ ጉዳዮችን ወይም ስህተቶችን ለማረብ ይግባኝ መውሰድ ሳያስፈልግ ከቁ.207-212 በተደነገገው መሠረት ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ ወይም በባለጉዳዮቹ ጥያቄ ስህተቱን ለማረም፤ለመሰረዝ ወይ ለመዝጋት ይችላል፡፡

## 2.11.2 ጉዳዩን እንደገና ማየት

ሀ/ በአንቀፅ 6 መሠረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና ለማየት ይችላል፡፡

ለ/ ሆኖም ይህን ጥያቄ ማቅረም የሚቻለው በአንቀፅ 6 ሥር በተደነገጉት ውስን ሁኔታዎች ብቻ ነው፡፡

ሐ/ የመጨረሻ ውሳኔ የገኙ ጉዳዮች እንደገና እንዳይታይ የሚከልክለው አንቀፅ 5(Resjudicata)በአንቀፅ 6 የተመለከተውን መብት አያግድም፡፡

## 2.11.3 ስለ መቃወም (Opposition)

ሀ/ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም ለመግባት ይሚችልና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱንን የሚነካበት ሰው ፍርዱን መቃወም ይችላል(ቁ358)መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ነው(ቁ 358)፡፡

ለ/ መቃወሚያው የሚቀርበው በቁ359 የተደነገገውን ፎርም ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

ሐ/ መቃወሚያው ሲቀርብ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያው ክርክር ተካፋይ የነበሩትን ወገኖች አስቀርቦ ከመረመረ በኃላ መቃወሚያ የቀረበበትን ፍርድ ለማፅደቅ፤ለማሻሻል፤ለመለወጥ ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡(ቁ 36)፡፡

## 2.11.4 ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት

ሀ/ በሌለበት የተፈረደበት ተከሳሽ ውሳኔው መስጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ውስጥ ቀርቦ ውሳኔው እንዲነሳለት ሊያመለክት ይችላል(ቁ 78)

ለ/ ተከሳሽ የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከላከያውን ያላሰማው ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ፍ/ቤቱ ውሳኔውን ሊያነሳለት ይችላል፡፡



# ክፍል ሶስት

## የንግድ ችሎቶች የቀጠሮ ፖሊሲ

### 3.1. <u>የጉዳዮች ሂደት እልባት የሚያገኝበትን ጊዜ ስለመወሰን</u>

ሁሉም ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ሂደታቸው ሳይጓተት እልባት እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን በንግድ ችሎቶች የሚታዩ በተለይም የንግድ ማህበራትን የተመለከቱ ጉዳዮች ከሌሎች የፍ/ብሔር ጉዳዮች በተለየ መልኩ ከተከራካሪ ወገኖች ባለፈ በሶስተኛ ወገኖች እንዲሁም በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከሚያስከትሉት ተፅእኖ አኳያ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በአፋጣኝ እልባት እንዲያገኙ ይሰራል፡፡ የችሎቱ ዳኞች ጉዳዮችን በአፈጣኝ እልባት መስጠት ያስችላቸው ዘንድ ጉዳዮች እንደየአይነትና ባህሪያቸው እልባት ሊያገኙ የሚገባበትን ጊዜና የቀጠሮ ፖሊሲ ማስቀመጥ እና መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ የችሎቶቹ የቀጠሮ ፖሊሲ እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

### 3.1.1 <u>በንግድ ችሎቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እልባት ሊያገኙ ስለሚገባቸው ጉዳዮች</u>

ሀ. ከሰበር ችሎት ወይም ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ፣ ብይን ወይም ውሳኔ መሠረት ወደ ፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ እንዲታይ ወይም ሂደቱ እንዲቀጥል የተደረገ ጉዳይ

ለ. የችሎቱ ዳኞች ከጉዳዩ ባህሪይ አኳያ በአስቸኳይ እልባት ማግኘት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ሲገነዘቡ

ሐ. ለጉዳዮች እልባት ከተሰጠ በኋላ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች (ለምሳሌ ዳኝነት ዳግም እንዲታይ እና የተቃውሞ አቤቱታ ሲቀርብ)

መ. ጉዳዮች በሂደት ላይ እያሉ የሥነ-ሥርዓት ሕጎችን መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የተለያዩ የመብት ጥያቄዎች ሲቀርቡ (ለምሳሌ የእግድ እና የዋስትና አቤቱታዎች)

ሠ. በንግድ ማህበራት ላይ የመክሠር ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የመክሠር ሂደቱን ከማከናወን ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች

ረ. የንግድ ማህበራት መፍረስ እና ሂሳብ መጣራትን ተከትሎ በመፍረስ እና በሂሳብ ማጣራት ሂደት ወቅት የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች

### 3.1.2 በንግድ ችሎቶች ቀጠሮ የሚሰጥበት ሁኔታ

ፋይል ከተከፈተ በኋላ ለችሎት ቀርበው ቀጠሮ ሳያስፈልጋቸው እልባት የሚያገኙ ጉዳዮች እና በፍ/ብሔር ስነ ስርዓት ህጉ ቀጠሮ አሰጣጥ ሥርዓትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በንግድ ችሎቶች ቀጠሮ ሲሰጥ

ሀ. ጉዳዮች ለሬጅስትራር ቀርበው ፋይል በተከፈተበት ቀን ቅደም ተከተል ይስተናገዳሉ፡፡

ለ. የቀጠሮ ቀንና ከሰዓት በፊት ወይም በኋላ መሆኑን እንዲሁም የቀጠሮው ሰዓት ለባለጉዳዮች ይገለፃል፡፡ (ለምሳሌ ከሰዓት በኋላ ወይም ጠዋት ብሎ በጥቅሉ መቅጠር አይቻልም)

ሐ. ክስ ቀርቦ መዝገብ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ 10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለተከሣሹ የተላከው መጥሪያና ተያያዥ ሰነዶች እንዲደርሰው ቀጠሮ ይሰጣል፡፡

መ. ተከሣሽ ከፍርድ ቤት የተላከለት መጥሪያና ተያያዥ ሰነዶች ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ10ኛው ቀን መልሱን ለፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡

ሠ. ከላይ የተመለከቱት የቀጠሮ ቀናት እንደተጠበቁ ሆነው የችሎቱ ዳኞች እንደየጉዳዩ ባሕሪይ የቀጠሮ ቀናቶችን ማሳጠርና ማስረዘም ይችላሉ፡፡

ረ. በንግድ ችሎቶች ቀጠሮ ሲሰጥ የባለጉዳዮችን ፍላጎት እና የጉዳዮችን ባህሪይ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

ሰ. ክርክሩ ተጠናቆ ለምርመራ የተቀጠረ መዝገብ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመ በስተቀር እልባት ማግኘት ይኖርበታል፡፡

### 3.1.3. በንግድ ችሎቶች ተለዋጭ ቀጠሮ ሲሰጥ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ሁኔታዎች

በፍ/ብሔር ስነ ስርዓት ህጉ ቀጠሮ አሰጣጥ ሥርዓትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በንግድ ችሎቶች ተለዋጭ ቀጠሮ ለመስጠት የሚከተሉት ሁኔታዎችን ታሳቢ ሊረጉ ይገባቸዋል፡፡

ሀ/ ለተለዋጭ ቀጠሮ ምክንያት የሆነው ነገር በሌላ ሁኔታ ሊፈታ የማይቻል መሆኑ

ለ/ ተለዋጭ ቀጠሮ የተጠየቀበት ጉዳይ በሂደት ላይ የቆየበት ጊዜ መጠን

ሐ/ በጉዳዩ ቀድሞ ተለዋጭ ቀጠሮ ያልተጠየቀበት መሆኑን

መ/ የጉዳዩ መጓተት በሌላው ባለጉዳይ ላይ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ፍትህ የማግኘት መብት ላይ የሚፈጥረው ተፅእኖ

ሠ/ ተለዋጭ ቀጠሮው ጉዳዩ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ እልባት እንዲያገኝ ለማድረግ ያለው አስተዋጽኦ

ረ/ ከላይ የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው ሌላ አሳማኝ ምክንያት መኖሩን የችሎቱ ዳኞች ከተረዱ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት ይችላሉ፡፡

### 3.1.4. የንግድ ችሎት ዳኞች የጉዳዮችን ሂደት ስለሚቆጣጠሩበት ስርዓት

በሌሎች ህጎች ለዳኞች የተሰጠ ኃላፊነትና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ችሎት ዳኞች የሚከተሉትን ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፡-

ሀ/ የጉዳዮች ሂደት በተቀመጠላቸው ጊዜ ውስጥ እልባት ማግኘት የሚያስችል ቀጠሮ አሰጣጥ ተግባራዊ ማድረግ

ለ/ በእያንዳንዱ ጉዳይ ሂደት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን ቅደም ተከተል የመቆጣጠር፣ የመከታተልና የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ ሂደቱ ከመቋጫ እንዲደርስ ማድረግ

ሐ/ በጉደዳዮች ሂደት ውስጥ በቅደም ተከተል ለሚከናወኑ ተግባራት ሁሉ በቂ ዝግጅት ማድረግ፡፡

መ/ የፍ/ቤቱ የጉዳዮች ሂደት አስተዳደር ትግበራ መመሪያ ካለ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ

ሠ/ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ከሌሎች ጉዳዮች የመለየትና እልባት እንዲያገኙ ማድረግ

ረ/ ባለጉዳዮች በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት ስምምነት እንዲፈቱ የማድረግ

ሰ/ በጉዳዮች ሂደት ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት ተመጣጣኝ የሆነ የቀጠሮ ቀን፤ መጠንና ዙር መስጠት ይሆናል፡፡

## 3.2. ከባለ ድርሻ አካላት የሚጠበቅ ኃላፊነት እና ተግባር

በሌሎች ህጎች ለፍ/ቤቶች አስተዳደር፤ ለዳኞች፤ እና ለችሎት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የተሰጠ ኃላፊነትና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ችሎት ዳኞች የሚከተሉትን ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት አለበቸው፡፡

### 3.2.1 የፍ/ቤቱ አስተዳደር ተግባር እና ኃላፊነት

- ጉዳዮችን በተያዘላቸው ጊዜ ቀጠሮ ለማስቻል ምቹ ሁኔታዎች የተፈጠሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- በስርዓተ ችሎቱ ላይ የተመለከቱን ሁኔታዎችን ተግባራዊነት መከታተል፤ (እና) መቆጣጠር እና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ
- በዚህ ሠነድ ላይ የተመለከተውን የቀጠሮ ፖሊሲ በመተግበር ውጤታማ የሆኑ ዳኞችን እውቅና መስጠት እና ማበረታታት

### 3.2.2 የችሎቱ ዳኞች ተግባር እና ኃላፊነት

- ጉዳዮችን በተያዘላቸው ቀነ ቀጠሮ እና ሰዓት ማስተናገድና እልባት መስጠት
- ባለጉዳዮችን በጥሞና ማዳመጥ እና ተገቢውን ክብር መስጠት
- ለጉዳዮች ሂደት መጓተትና ተለዋጭ ቀጠሮ ምክንያት የሚሆኑ ተግባራትን አለመፍጠር

- በጉዳዮች ሂደት ውስጥ የሚከናወኑ ድርጊቶች በተለይም ተከራካሪ ወገኖችን ያላስማማ የህግ ወይም የፍሬ ነገር ጭብጥ የመለየት ሂደት፣ ማስረጃ የመስማት ሂደት፣ ውሳኔ የማሳወቅ ሂደት እና ቅጣት የማስተላለፍ ሂደትን በግልፅ ችሎት ማከናወን

- የስራ ሰዓትን ማክበር

- በማንኛውም ጉዳይ ክርክር ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪ ወገኖችን ለማስማማት መሞከርና ማግባባት

### 3.2.3. የችሎቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተግባር እና ኃላፊነት

- መዝገቦችን በተያዘላቸው ቀነ ቀጠሮ ቅደም ተከተል ከመዝብ ቤት ለዳኛ ማቅረብ

- መዝገቦችን በአግባቡ መሠየም እና ሁሉም መዝገቦች ተሟልተው ለዳኛ የቀረቡ መሆኑን ቀድሞ ማረጋገጥ፤

- እልባት ያገኙና የተቀጠሩበት ምክንያት የተከናወኑ መዝገቦች በዳታ ቤዝ እንዲመዘገቡና ወደ መዝገብ ቤት እንዲገቡ ማድረግ

- ባለጉዳዮችን በትህትና ማስተናገድ

- የስራ ሰዓት ማክበር

### 3.2.4 በተከራካሪ ወገኖች ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት

- ከአቅም በላይ ችግር ካልገጠመ በስተቀር የፍ/ቤትን መጥሪያ በተገቢው ጊዜ ማድረስ

- በወረቀት አሳትመው የሚያቀርቡትን ክርክር በሶፍት ኮፒም ጭምር ማቅረብ

- በተያዘላቸው የቀጠሮ ሰዓት ቅደም ተከተል መስተናገድ





# ክፍል አራት

## በፌደራል መጀመሪያ ፍ/ቤት የንግድ ችሎቶች ተፈፃሚ የሚሆኑ ዋና ዋና የህግ ምንጮች

### 4.1 የተለያዩ የአገር ውስጥ ህጎች

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት /አዋጅ ቁጥር 1/1988/**

ለለአገሪቱ ህጎች በሙሉ በምንጭነት የሚያገለግል የህጎች ሁሉ የበላይ ሲሆን በህገ መንግስቱ ከተደነገጉ ኢኮሚያዊ መብቶች አንዱ መንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት እና የመረጠውን ስራ የመስራት የመሠረታዊ መብት ስለመሆኑ ከህገ መንግስቱ  አንቀጽ 40 /1/ እና /2/ ስር መገንዘብ ይቻላል። ዜጎች በግ መንግስቱ የተጠበቀላቸውን መብት በመጠቀም በመረጡት የንግድ ዘርፍ ከተሰማሩ ፍ/ቤቶችም ይህን የዜጎች መሠረታዊ መብት የማክበር እና የማስከበር ህገ መንግስታዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 9/2/ ስር መረዳት ይቻላል።

**የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ /አዋጅ ቁጥር 25/1988/**

ይህ አዋጅ ፍ/ቤቶች በህገ መንግስቱ የተሰጣቸውን ህግ የመተርጎም ስልጣን መነሻ በማድረግ የፌደራል ፍ/ቤቶች ያላቸውን የዳኝነት ስልጣን የሚደነግግ ሲሆን የፌደራል

መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 14 መሠረት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠው የፍትሐብሔር ዳኝነት ስልጣን ውስጥ የሚካተቱ ንግድ ጉዳዮችን የተመለከተ የመብት ጥያቄዎችን ያስተናግዳሉ፡፡

**የንግድ ህግ /አዋጅ ቁጥር 166/1952/**

በፌደራል መጀመሪያ ፍ/ቤት ለሚታዩ የንግድ ጉዳዮች በዋና ምንጭነት የሚያገለግለው የንግድ ህግ ሲሆን ከነጋዴዎች እና ከንግድ መደብሮች፣ ከንግድ ማህበራት፣ ከሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች እንዲሁም ስለ ኪሣራ እና የመጠባበቂያ ስምምነቶች በንግድ ህጉ ላይ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች ይህንኑ ህግ መሠረት በማድረግ በፍ/ቤት እልባት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**የፍትሐብሔር ህግ /አዋጅ ቁጥር 165/1952/**

በንግድ ህጉ እና ሌሎች ተያያዥ ህጎች ላይ የተመለከቱ የንግድ ህግ ድንጋጌዎችን መነሻ በማድረግ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎች እንደተጠበቁ ሆነው የንግድ ችሎቶች ከፍትሐብሔር ችሎቶች መካከል የሚመደቡ በመሆባቸውን እና በችሎቶቹ የሚታዩ ክርክሮችም ፍትሐብሔራዊ በመሆናቸው በፍትሐብሔር ህጉ ላይ ስለ ውል እንዲሁም ሌሎች ከንግድ እንቅስቃሴና ነጋዴዎች ጋር ተያዥነት ያላቸው ህግጋትም እንደየ አግባብነታቸው አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡

**የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ /አዋጅ ቁጥር 52/1958/**

የንግድ ጉዳዮች እንደማንኛውም የፍትሐብሔር ጉዳዮች ሂደታቸው ሙሉ በሙሉ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህጉ ላይ በተመለከቱ ድንጋጌዎች አግባብ የሚመራ ሲሆን ከሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች ጋር ተያይዘው ለሚቀርቡ የገንዘብ ጥያቄዎች እና ሌሎች ከኢኮኖሚ አንድምታቸው አኳያ ፈጣን የፍ/ቤትን ምላሽ የሚሹ ጉዳዮች በስነ ስርዓት ህጉ ላይ በተፋጠነ እና በአጭር ስነ ስርዓት ይስተናገዳሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ስርዓተ ችሎት ክፍል አንድ ላይ የተዘረዘሩ የመብት ጥያቄዎች በንግድ ችሎቶች ሲቀርቡ ከላይ ከጠቀስናቸው ህጎች በተጨማሪ የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ አዋጅ /አዋጅ ቁጥር 980/2008/፣ የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ /ደንብ ቁጥር 392/2009/፣ የንግድ ምልክት ምዝገባ እና ጥበቃ አዋጅ /አዋጅ ቁጥር 501/1998፣ የንግድ ምልክት እዝገባ እና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ /ደንብ ቁጥር 273/2005፣ የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ /አዋጅ ቁጥር 813/2006/ እና ሌሎች ተያያዝ ህጎች ከጉዳዮች ዓይነት እና ባህሪ አኳያ እንደየ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 4.2. በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የተሰጠባቸው የንግድ ጉዳዮች

**ቅፅ**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 14605 | የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት (ስድስት ሰዎች) | ሐምሌ 29/1997 | በመጓጓዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች መጎዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 590, 591 የፍ /ብ /ህ/ ቁ. 1792 |

**ቅፅ 4**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 22162 | አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጉላ | ሚያዝያ 9/1999 | መድን ሰጭ የካሣን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ |

**ቅፅ 5**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማ እና እነ ባህሩ አብርሃም (አስራ ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 10/1999 | የአክስዮን ማህበር አባላት የአክስዮን አስተዳዳሪዎች መብታቸውን በሚጎዳ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ በቀጥታ መክሰስ የሚችሉ ስለመሆናቸው የንግድ ህግ ቁ. 367 |

**ቅፅ 6**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 23628 | ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ እና እነ.ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ (ሁለት ሰዎች | ጥቅምት 21/2000 | በውጭ ሀገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያገኘ ኩባንያ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ በውጭ አገር ያገኘውን የህግ ሰውነት ቀሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 100 |

## ቅፅ 7

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 19258 | አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ጉቡ | ሐምሌ 12/1999 | የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር መዋጮ መክፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራው ከተጀመረ በኋላ ስላለመሆኑ |
| 2. | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኀበር እና እነ ባህሩ አብርሃም (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 10/1999 | የአክሲዮን ማህበር አባላት መብታቸውን የሚነካ ድርጊት በማህበሩ አስተዳዳሪዎች በተከናወነ ጊዜ በቀጥታ አስተዳዳሪዎቹን ሊከሱ ስለመቻላቸው የንግድ ህ/ቁ. 364,365,367 |
| 3. | 33760 | ሐጂ ታጁ ለገሠ እና የጎንደር ከተማ የመሃል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር | መጋቢት 18/2000 | የንግድ ድርጅት /መደብር/ ላይ ያለ መብት የድርጅቱ ንግድ የሚካሄድበትን ቤት የኪራይ መብት የሚያካትት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 127 |
| 4. | 20232 | አቶ ትዕግስቱ ብዛ እና አቶ ይሃ ይብሬ | ሐምሌ 24/1999 | የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው በመሆናቸው የውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሟላታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 715, የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706, 1679 |

## ቅፅ 8

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| | 32854 | ወ/ሪት ማርታ አድማሱ እና እነ አቶ በረከት ሰብስቤ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2001 | ከአንሻሪነት ውል ጋር በተያያዘ ለሚኖር የጉዳት ሃላፊነት ካሣ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 595, 596, 597 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 2090, 2091, 2092, 2141, 2102 |
| | 32571 | አቶ ሚፍታህ ከድር እና የባህር ትራንዚት አገልግሎት | ታህሣሥ 9/2001 | የዕቃ አስተላላፊነት ሃላፊነትና ተግባር ዕቃን የማጓጓዝና የማስረከብ ሥራን የሚያካትት ስለመሆኑ |
| | 39256 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ሞሣ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት እንደተሰጠ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2863 — 2874 |

**ቅፅ 9**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 33954 | ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና አቶ ዘውዱ ቢረዳ | ጥቅምት 20/2001 | የንግድ ድርጅት በህግ አግባብ ለባለመብቶች ሊከፋፈል የሚችልበት ሁኔታ ፤ የንግድ ህግ ቁጥር 127 |
| 2 | 33470 | ወ/ሮ እጅጋየሁ ታደሰ እና መገርሳ ጉደታ | ህዳር 2/2001 | የአሽሙር ማህበር መፍረስ በንብረት ክፍፍል ረገድ የሚያስከትለው ውጤት |
| 3 | 34945 | ወ/ሮ መስታወት በላቸው እና አቶ ለገሠ ሣህሉ | ህዳር 2/2001 | የጋራ ሀብት የሆነ ኃሊፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንደሌላ ማናቸውም ንብረት ባለበት ሁኔታ በዓይነት ሊከፋፈል ወይም ደግሞ በሃራጅ ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 542 |
| 4 | 31264 | ወ/ሮ እመቤት መኮንን እና ወረዳ 20 ቀበሌ 29 አስ/ጽ/ቤት | ጥር 5/2001 | የንግድ መደብርን የተከራየ ወገን ይህንኑ የንግድ መደብር ለሌላ ሶስተኛ ወገን ያያለአከራዩ ፈቃድ ማከራየት ስለመቻሉ ፤ የንግድ ህግ ቁጥር 145 |
| 5 | 34586 | አቶ ያለው ድልነሳው እና<br>እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ<br>(አራት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግዴ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ የፌ/ብ/ህ/ቁ. 1161 የንግድ ህግ ቁ. 124 |
| 6 | 43315 | ብራንድ ኒው የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ማዕከል እና አቶ መስፍን ታደሰ | ግንቦት 18/2001 | ቼክን አስመልክቶ ክስ በቀረበ ጊዜ የተከሰሰው ወገን የቀረበበትን ክስ ለመከላከል እንዲፈቀድለት የሚያቀርበው ምክንያት ፈቃድ ሊያሰጥ የሚችል መሆን ያለመሆኑን አግባብነት ካላቸው ህግጋት አኳያ መታየት ያለበት ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 717 የፌ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 284 285 |

## ቅፅ 10

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 46358 | ወ/ሮ ብርሃን ፀጋዬ እና እነ አቶ ሚካኤል ፊስሃ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 25/2002 | የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብ በግለሰቦች መካከል በውል የሚፈጠር የሽርክና ማህበር የንግድ ህግ በሚያዘው መሰረት አይነቱ ተለይቶ ተመዝግቦ የማይገኝ በሆነ ጊዜ እንደ የእሽሙር የሽርክና ማህበር ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ<br><br>የንግድ ድግ ቁጥር 211,212,219 |
| 2 | 39608 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ እና እነ ወ/ሮ አምሳለ በላይ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 11/2002 | ኃሊፉነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑ ሰዎች ማህበሩን ሲያስተዳድሩ በሰሩት ያልተገባ<br><br>ስራ ምክንያት በኃሊፊነት ሊጠየቁ የሚችለበት አግባብ<br><br>የንግድ ህግ ቁጥር 580 |

## ቅፅ 12

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 40173 | አምባሰል የንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ አብደልቃድር ጁሃር | ጥቅምት 05/2003 | በቼክ ሊይ የተፃፈለትን ገንዘብ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ያልጠየቀበት ሰው ወይም በይዞታው እያለ የታገደበት እንደሆነ ይህንኑ ቼክ እንደ ተራ ሰነድ በማስረጃነት በማቅረብ ያለአግባብ የመበልፀግ ክስ ሊመሰርት የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 799 |
| 2 | 48242 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ቦጋለ መስቀላ / ሁለት ሰዎች/ | ጥቅምት 04/2003 | የሐዋላ ወረቀት በይርጋ ስለሚታገድበት አግባብ የንግድ ህግ ቁ. 817/1/ /2/, 825 |



| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | 52269 | እነ አቶ ከድር ሀድ ሁሴን /ሁለት ሰዎች/ እና አቶ ጁሀር አልይ | ጥቅምት 17/2003 | የአክስዮን ማህበር መሥራቾችና የአክሲዮን ድርሻ መብት ጋር በተያያዘ በሚቀርብ አቤቱታ ላይ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ ተፈፃሚነት የላለው ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 416/2/ |
| 4 | 55077 | ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገኑ እና አቶ ግደይ አብርሃ | ህዳር 28/2003 | ቼክ ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የፍትሃብሄር ክስ ለቼኩ መፃፍ / መውጣት/ ምክንያት ከሆነው ውል ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባ ስለመሆኑ ውልን መሠረት በማድረግ የተፃፈ ቼክ ሌላው ወገን የውድ ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም በሚል ምክንያት ብቻ ቼኩን የፃፈው ወገን በቼኩ ከመጠየቅ ነፃ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁጥር 717 |
| 5 | 52667 | ኒያሊ ኢንሹራንስ አክስዮን ማህበር እና የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ | ታህሳስ 12/2003 | በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለደረሰ ጉዳት የሚከፈል የጉዳት ካሣ አወሳሰን የባህር ህግ ቁ. 198/1/ /3/ |
| 6 | 57288 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አሸብር ታደሰ /አምስት ሠዎች/ | መጋቢት 19/2003 | የአክስዮን ማህበር አባል በመሆን የሚገኝ መብትና ጥቅም ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችልበት አግባብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ባለአክሲዮን የሆነ ሰው ላለበት የግል ዕዳ አክሲዮኖቹ /በወቅቱ የገበያ ዋጋ/ ተሸጠው እንዲከፈል ለማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 522-524 |
| 7. | 56480 | የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ሰኔ 14/2003 | በባህር ላይ በሚደረግ የዕቃ ማጓጓዝ ለሚደርስ ጉዳት የአጓጓዡ የኃላፊነት አድማስ የባህር ህግ ቁ. 196, 138, 205, 197, 180/3 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 8. | 57932 | ተክለ ካሣ ገብረየስ እና ማርኮ ባርዚ | ሰኔ 30/2003 | የአክስዮን ማህበር ወይም የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ድርጅቱ የሚያዝበት ገንዘብ እንደላው እያወቀ በድርጅቱ ስም በሚያወጣው/ በሚሰጠው/ ቼክ በኃላፊነት ሊያስጠይቀው የሚችል ስለመሆኑ የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ በንግድ ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ወይም የኩባንያውን መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ መስራቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ከድርጅቱ ጋር በአንድነት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በተናጠላ ለጠየቅ ስለመቻለ የንግድ ህግ ቁ. 530 |
| 9 | 58931 | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ታይገር ሎጀስቲክ እና የንብረት ጥበቃ ኃ/የተ/የግሌ ማህበር | ሐምሌ 15/2003 | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ሲል ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች አለመሆኑን እንዲሁም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ. 67/89 አንቀጽ 16/2/ 14 20 አዋጅ ቁ. 376/96 የንግድ ህግ ቁ. 137,138 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10 | 24435 | ሀጂ መሃመድ አደም<br>እና<br>አቶ ፍፁም ግርማ | የካቲት 04/2000 | ከቼክ ጋር በተያያዘ "የግል ግንኙነት" በሚል የተቀመጠው ሀረግ ለተርጎም የሚችልበት አግባብ በቼክ የሚገደድ ሰዎች ላይ አውጭው ክስ ለማቅረብ የሚችለው ቼኩ ከተፃፈበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br><br>በቼክ በተከሰሰና ሰነድን ይዞ በመጣው ሰው መካከል ያለን "የግል ግንኙነት" በመቃወሚያነት ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ ቼክ የሚሰጥበት ምክንያት በሰጪውና በተቀባዩ የሚወሰን እንጂ በህጉ የተዘረዘረ ባለመሆኑ ቼኩን የፃፈው ሰው ቼኩን የሰጠሁት ለዋስትናነት ነው በሚል ቼኩን ይዞ በመጣው ሰው ላይ "የግል ግንኙነትን" መሠረት በማድረግ የሚያቀርበው መቃወሚያ ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የማይችል ነው በሚል ውድቅ ሊደረግበት የማይገባ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 717/1/-/3/, 855, 881/1/, /ሀ/, 854, 640, 868, 752, 850, 827 — 840 |
| 11 | 50537 | ሲ/ር መአዛ ዮሴፍ እና<br>ዶ/ር ዮሴፍ ደነቀው | ግንቦት 02/2003 | ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል የሆነ ሰው ከአባልነቱ ለመውጣት የሚችልበት ብሎም ማህበሩ ሊመሰረትና ሊፈርስ የሚችልበት አግባብ የፌ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በሽምግልና ስምምነት ከመፍታት ጋር ተፈፃሚ የሚደረግበት አግባብ የንግድ ህግ ቁጥር 510/2/ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2/ /ረ/ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 12 | 49295 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና እነ የቻይና ዋንቦ ኢንጂነሪንግ ኮርፕሬሽን /ሁለት ሰዎች/ | መጋቢት 22/2003 | በንግድ ህጉ ቁጥር 683 "ወኪሎች" በሚል የተመለከተው የእቃ አስተላላፍነት ሥራን ለጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን የማያካትት ስለመሆኑ መድን ሰጪው ክስ ሊያቀርብባቸው የማይችላቸው ወገኖች ከመድን ገቢው ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸውና ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለመድን ገቢው ጥቅም የሚሰሩ ወገኖችን ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ. 683/3/ |

**ቅፅ 13**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳዩ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 54117 | ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አ.ማ | ጥቅምት 13/2004 | በባህር ላይ እቃ አመላላሽ በእቃዎች ላይ ለደረሰ ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቅ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>በባህር ሊይ እቃን ለማመላለስ የውል ግዴታ የገባ ወገን ከእቃዎቹ መጎዳት ጋር በተያያዘ ስላለበት የኃላፊነት አድማስና ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ<br>የባህር ህግ ቁ.196,138,205,197,180(3) |
| 2 | 60385 | ጎልደን ሮዝ አግሮ ፋርምስ ኃ/የተ/የግ ማህበር<br>እና አቶ ሐለፎም ተስፋ ማሪያም | ጥቅምት 24/2004 | እቃን ከማጓጓዝ ጋር በተገናኘ ከእቃው አደገኛ (ጉዳት አድራሽ) ባህሪ የተነሣ ዕቃውን በሚያጓጉዘው ተሸከርካሪ ሊይ ለደረሰ ጉዳት የእቃው ባለቤት (ባለንብረት) የዕቃውን በአግባቡና በጥንቃቄ አለመታሸግ አለመያዝ) ጋር በተገናኘ በኃላፉነት ሊጠየቅ ስለመቻሉ<br>የንግድ ህግ ቁ.578(2) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | 69603 | አቶ ሀብተወልድ ዘርጋው የጄትሮ የስራ አመራር የማማከር አገልግሎት ድርጅት እና እነ አቶ ሳሙኤል አሰፊ የጄትሮ ሊደርሺፕ ኤንድ ማኔጅመንት(ሁለት ሰዎች) | ህዳር 08/2004 | ከንግድ ስም አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የንግድ ሚኒስቴር በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታ በይግባኝ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.686/2002 አንቀፅ 6, 7, 30, 2(9), 16, 61 |
| 4 | 63454 | ዳት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ/ ባለቤት ዶ/ር ጤና አብተው እና<br>እነ የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 26/2004 | ከንግድ ስም ወይም ምልክት ምዝገባ ጉዳይ ጋር በተገናኘ በሚመለከተው ተቋም በተሠጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ያለው መብት በይግባኝ ሥርዓት የማሳረም ስለመሆኑ፤<br>አዋጅ ቁጥር 501/98/ አንቀጽ 6,17,36,49 |
| 5 | 36935 | አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | የካቲት 27/2004 | ለገንዘብ እዳ የሚሰጥ ዋስትና አንድ የመድን ተቋም ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል አንዱ ስለመሆኑ፤<br>በመድን ሰጪ ድርጅቶች ተዘጋጅቶ የሚሰጥ የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) ስለሚኖረው ውጤት የገንዘብ የዋስትና የግዴታ ሰነድ ሊያሟሊቸው የሚገቡ ፎርማሊቲዎች እና አቤቱታ ከማቅረብ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ስለሚኖረው የይርጋ ደንብ አዋጅ ቁ.86/86 አንቀፅ 2 የፌ/ብ/ህ/ቁ 1845, 1922(2)(3), 1725(ሀ), 1727, 1926, 1929, 1930, 1931 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር 23/2002 አንቀፅ 1(1), 2(1) መመሪያ ቁጥር 24/2004 አንቀፅ 1(3), 2(1), 3 የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ) አዋጅ ቁ.110/90 አንቀፅ 2(2) አዋጅ ቁ.57/89 አንቀፅ 2(18) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | 47004 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>ባላ ገጠር ልማት ድርጅት | መጋቢት 11/2004 | ስለ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantee Bond) የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ውል በባህሪው ከመድን ውል የሚለይና በፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1921, 1719, 1720, 1727, 71719(2), 1920, 1845, 1924(1), 1922(3), 1926<br><br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁ23/2002 አንቀጽ 1(1),<br><br>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ 24/2002 አንቀጽ 1(3)<br><br>የንግድ ህግ ቁ. 654(1), 657(1), 712 አዋጅ ቁ. 57/1989<br><br>አዋጅ ቁ 648/2001 አንቀጽ 2/20 አንቀጸ 2(18) አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2) |
| 8 | 71134 | አቶ ያሬዱ ሲሳይ<br>እና<br>አልግሪን አግሮ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሰኔ 04/2004 | አንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንዲፈርስ ለመጠየቅ በቂና ህጋዊ መስፈርቶች መሟላታቸው መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ የማህበር ሥራው በአግባቡ አልተመራም ከሚል ጥያቄ ጋር በተያያዘ አግባብነት ያለው አካል የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች መሠረት በማድረግ እንዲስተካከል ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 217, 218, 511, 543 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9 | 40186 | አፍሪካ ኢንሹራንስ (አ.ማ) እና ዳሸን ባንክ (አ.ማ) | የካቲት 27/2004 | ስለ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ (Financial Guarangee Bond) እና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በማናቸውም ስያሜ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ የማውጣት ተግባር እንዳይፈጽሙ የተከለከሉ ስለመሆኑ የአክሲዮን ማህበራት ፕሬዚዳንት ወይም ዋና ሥራ አስኪያጅ ስላለው ስልጣን እና በህግ አግባብ ስልጣኑ ተገድቧል ለማለት ስለሚቻልበት ሁኔታ የገንዘብ ዋስትና የግዴታ ሰነድ እንደ የኢንሹራንስ ፖሊሲ የማይቆጠር ስለመሆኑና በፍ/ብሔር ህጉ ስለ ዋስትና ግዴታ በተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ፡ ቁ. 24/2004 አንቀጽ 3,1(3) ቁ. 23/2004 አንቀጽ 1(1) አዋጅ ቁ. 86/86 አንቀጽ 2(4) ,6,4 32-34 አዋጅ ቁ. 87/89 አንቀጽ 2(18)<br><br>አዋጅ ቁ. 110/90 አንቀጽ 2(2) የፍ/ብ/ህ/ቁ.1725 (ሀ),1727,1922(2),(3) አዋጅ ቁ. 648/2001 አንቀጽ 2(20) የንግድ ህግ ቁ.36(1)(2), 121(ሰ), 348(3), 313(1)-(7), 313(10-12), 34(1),1 09(ረ), 323(2-3), 35(1), 26, 120 |
| 10 | 63200 | እነ ጣና ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር (አራት ሰዎች) እና ሚስተር አልቸዲ ዴልጋውዲዮ | ታህሳስ 30/2004 | የአክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ያለአግባብ ከስልጣኔ (ከስራ አስኪያጅነቴ) ተሸሬያለሁ በሚል በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤት ግለሰቡን ወደ ስራ አስኪያጅነቱ እንዲመለስ ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ፣<br><br>የንግድ ህግ ቁ. 525-537 |

**ቅፅ 14**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳዩ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 76394 | አቶ ወርቁ ወ/ፃዱቅ እና እነ የአቶ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ወራሾች (ሰባት ሰዎች) | ህዳር 18/2005 | የአሽሙር ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሌለው እንዲሁም በጽሁፍ መረጋገጥና ሌሎች የንግድ ማህበሮችን በተመለከተየተደነገጉት የማስታወቅና የማስመዝገብ ሥርዓቶች የማይፈፀምበት ነው በሚል ምክንያት ብቻ የአሽሙር ማህበርን አስመልክቶ ማህበሩ እንዲፈረስ በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ስመልክቶ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ የአሽሙር ማህበር የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርገው በሽሪኮቹ ስም ስለመሆኑና ሽሪኮቹም እንደተራ ተዋዋይ ወገኖች የሚታዩ ስለመሆናቸው የንግድ ህግ ቁ. 212(1),272 |
| 2 | 80599 | ጀሽዋ ኢነድ ካሌብ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ወ/ሮ እንቁጣጣሽ አሰፋ | ጥር 15/2005 | አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) የሚጨበጥና የማይጨበጥ እንዲሁም የሚንቀሣቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መብቶች ምን ምን እንደሆኑ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ስለመሆኑ አንድ የንግድ ማህበር (ድርጅት) ሥራውን የሚያከናውንበት የንግድ ቦታ ኪራይ መብት የማህበሩ ህልውና ጋር የሚያያዝ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የንግድ ድርጅቱ የፈረሰ ቢሆንም የንግድ ሥራውን ሲያከናውንበት የነበረውን ቦታ በሌላ ጉዳይ በፍርድ እንዲልቅ በተወሰነ ጊዜ የማህበሩ ሒሳብ ተጣርቶ አለመጠናቀቅ ቦታውን ላለማስለቀቅ ምክንያት ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ፣ |

**ቅፅ 15**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳየይ |
|---|---|---|---|---|
| | 79561 | አቶ ፀጋዬ አማን ለጃ እና በየካ ክፍለከተማየወረዳ 08አስተዳደር ጽ/ቤት | የካቲት 11/2005 | የንግድ መደብር ኪራይ ከንግድ ቤት ኪራይ የተለየ ስለመሆኑ፣ የንግድ መደብር የተከራየ ሰው ያለአከራዩ እውቅና እና ፈቃድ መደብሩን ለ3ኛ ወገን በኪራይ አሳልፎ ለመስጠት ስለመቻሉ፣ የንግድ ህግ ቁ. 127 (ሐ),145(ለ), |
| | 82503 | እነ ወ/ሪት ቤዛ ዱጉማሁለት ሰዎች) እና ዘሚሊ ቀለም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 21/2005 | የንግድ ማህበር ሒሣብ ከተጣራና ትርፍና ኪሣራው ተለይቶ ከቀረበ በኋላ የማህበር አባል (ባለአክሲዮን) የሆነ ሰው ከትርፍ ሊደርሰው የሚገባውን የድርሻ ክፍያ በመለየት ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት የሚያቀርብው ጥያቄ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 211, 517, 518, 532(1) |
| | 85009 | ሃጅ ፈዬ ገመቹ ሄዳኦ እና እነ አቶ ዓለሙ በቀለ (አስራ አምስት ሰዎች) | መስከረም 21/2006 | የህብረት ሥራ ማህበራት ንብረት እንደ የአባለቱ የጋራ ሀብት (ንብረት) ተቆጥሮ ንብረቱን ለመሸጥ የሁሉም አባላት ስምምነት ያስፈልጋል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ የህብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ጋር በተያያዘ ውሣኔ ለማሳለፍ የሚችለው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስለመሆኑ፣አዋጅ ቁ. 147/91 አንቀጽ 21, 18, 32, 19 ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 20(2) 123 |
| | 83489 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ግንቦት 19/2005 | አበዳሪ የሆነ ባንክ ለተበዳሪው ላበደረው ገንዘብ በመያዣነት ለያዘው ንብረት የመድን ሽፋን የገባለት እና የአርቦን ክፍያን ለመክፈል የተስማማ እንደሆነ ለመድን አስገቢው ተቋም የአረቦን ክፍያውን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣ የንግድ ህግ ቁጥር 657, 675 |

## ቅፅ 16

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 90434 | ሉሃና አንጂነሪግ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ. የግል ማህበር እና ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ኃ.የተ.የግል ማህበር | ሰኔ 06/2006 | ለቼኩ መሰጠት መሰረት የሆነውን ውል እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለውን ህግ ሳይመለከቱና በተገቢው የክርክር አመራር ስርዓት ፍሬ ነገሩን ሳያጣሩ የሚሰጥ ዳኝነት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ |

## ቅፅ 17

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 94278 | አቶ ሐሠን መሀመድ እና ማጅ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ሕዳር 11/2007 | ክሱ የቀረበው በአንድ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ወይም ቀን የተፈጠረ ክስተትን መሠረት በማድረግ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ተከስተዋል የተባሉ የተለያዩ ችግሮችን መሠረት አድርጐ ሲሆን የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ ወይም ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚባልበት ምክንያትሥላለመኖሩ፣ የን/ሕ/ቁ 218(1)፣541(1) የፍ/ሕ/ቁ 1835፣1845 |
| 2 | 95069 | እነ ስፍሜት አግሮ ቢዝነስ ኃ/የተ/ ማህበር /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ኤልሳቤት ብረቱ | ሕዳር 23/2007 | ከውጪ አገር በዶላር የተላከ የውጭ ምንዛሬ ለተላከለት አላማ አልዋለም በሚል ገንዘቡ እንዲመለስ ክርክር ሲነሳ ገንዘቡ ሊመለስ የሚገባውዶላር በተላከበት ጊዜ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ በተሠጠው ተመን መሠረት ስለመሆኑ፣ የፍ/ሕ/ቁ 1705፣1749፣1750፣1771 |



**ቅፅ 18**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 94481 | ወ/ሪት ፀሐይነሽ በቀለ እና ወ/ሪት ንግስት ተክላይ | ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም 3 | የሽርክና ማህበር በህግ አግባብ ተቋቁሞ እየሠራነው ለማለት በጽሁፍ ውል መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ተዋዋይ ወገኖች በጋራና በተናጠል በመተባበር በመስራት ከጥቅሙም ይሁን ከእዳው በጋራ ሲጋሩ እንደነበር መረጋገጥ ያለበት ሥለመሆኑ፣ አንዴ የሽርክና ማህበር በህጉ አግባብ ተቋቋመ ለማለት የሚቻለው ተዋዋይ ወገኖች ተነጻጻሪ ሣይሆን ተደጋጋፉ የሆነ ግብ ይዘው መዋጮ በማውጣት<br><br>አብረው በመስራትና በመተባበር ትርፍና ኪሣራም በህጉ አግባብ እየተጋሩ ኢኮኖሚያዊ ተግባር ማከናወናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ፣<br><br>የንግድ ህግ ቁጥር 211፣229፣269/1/ |
| 2 | 96990 | አቶ አያላው ወልዴ ዮሃንስ እና አቶ ጀማል ሰማን ኑር | ሐምሌ 01 ቀን 2007ዓ.ም | የሽርክና ውል ስምምነት አለ ለማለት መሟላት ሥለሚገባቸው መስፈርቶች የንግድ ህግ 5፣10(1)፣ 210(1)፣ 211፣ 215 እና 229(2) |
| 3 | 100621 | አቶ ልዑልሰገድ ሞጆ እና እነ አንዴነት ቅቤና ቅመማ ቅመም ነጋዴዎች | ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም | በሞተ ሰው ሥም የተመዘገበን የአክስዮን ድርሻ ላይ ሟቹ እንደተገኘ ተቆጥሮ የሚተሲለፍ ውሳኔ አግባብነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተፈፃሚነት ያለው በንግድ ህጉ የተቀመጠው የሦስት ወር ጊዜ ሳይሆን በፍ/ሕ/ቁ 1845 የተመለከተው የአስር ዓመት ይርጋ ስለመሆኑ የንግድ ህግ ቁ.416 የፍ/ሕ/ቁ.1845 |
| 4 | 102725 | እነ አቶ ዲንሳፋ ያዕቆብ /ሦስት ሰዎች/ እና<br><br>ወ/ሮ አየለች በቀለ | ሐምሌ 14 ቀን 2007 ዓ.ም | በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት በልዩ ሁኔታ በንግድ ቤት ተጠቃሚ ለመሆን ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 5 | 103717 | የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሰራተኞች ሸማቾች ህብረት ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር እና የአዳማ ወረዳ ንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት | ሐምሌ 03 ቀን 2007 ዓ.ም | የህብረት ሥራ ማህበራት በመሰረታዊነት ለትርፌ ተብሎ የሚቋቋሙ ሳይሆን የአባላቱን ፍላጐት በአነስተኛ ወጪ ለሚሟሊት የሚቋቋሙ በመሆኑ ለትርፍ ስራ የሚሰሩ የንግዴ ስራዎች የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ የሚገደድበት አግባብ የላለ ሥለመሆኑ የኃብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ማሻሻያው አዋጅ ቁ. 402/96 አንቀጽ 6 |

**ቅፅ 19**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ግራ ቀኙ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 99900 | አቶ ኃይሉ መንግስቱ እና አቶ ሬገን መሐመድ (ሁለት ሰዎች) | መስከረም 25 ቀን 2008 ዓ.ም | በውል መሰረት ከተቋቋመ የሽርክና ማህበር ውስጥ አንድ የማህበር አባል ከማህበሩ ሊወጣበት ስለሚችልበት አግባብ<br><br>የንግድ ህግ 227 እና ተከታዮቹ |
| 2 | 97760 | ወ/ሮንግስቲ አትክልቲ እና አቶ አበባው ሽፈራው | ታህሳሥ 19 ቀን 2008 ዓ.ም | በአንዥ ጥፋት በደረሰ አደጋ ምክንያት በተጎዡ(መንገደኛው) ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ለመወሰን ልንከተላቸው ስለሚገቡ የካሳ አከፋፈል መርሆች የን/ሕ/ቁ. 599፣ የፍ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 |
| 3 | 105628 | ዩኒቨርሳል ሜታልስና ሚኒራልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በስፋት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም | የህንጻ ኪራይ ውል ካለቀ በኂላ የታጣ ገቢ የኪራይ ዋጋ በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣኖች በወሰኑት ታሪፍ መሠረት ወይም ታሪፍ<br><br>የሌለ እንደሆነ የቦታዎች ልማድ በመከተል መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ሕ/ሕ/ቁ. 2950/2/ |

**ቅፅ 21**

| ተ.ቁ | መዝገብ ቁጥር | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔ የተሰጠበት ቀን | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳዩ |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 110149 | ምድር ሎዛ የጋራ ሕንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ እና አቶ ይህደጎ ኪዱኔ | ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ.ም | በአንድ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ አባል የሆነ ሰው በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምፅ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ እና ይህ ሁኔታ /አጠቃላይ መርህ/ ሊታለፍ የሚችለው መረጃ ሊቀርብበት የሚችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ስለመሆኑ<br><br>አዋጅ ቁጥር 147/91 /በአዋጅ ቁጥር 402/96 እንደተሻሻለ አንቀጽ 18/2/ |
| 2 | 123984 | አቶ ጌታቸዉ መሸሻ እና አቶ ተሾመ ወልዴ | ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | ቼክ የብድር ዉልን ተክቶ ብድር መኖሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለው ሰነድ ነዉ ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br><br>በብድር የተሰጠዉ ገንዘብ 500 / አምስት መቶ/ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድር ዉል በጽሑፍ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት የማይቻል ስለመሆኑ<br><br>ንግድ ሕጉ ቁጥር 827 /ሀ/ እና 854<br><br>የፍ/ብ/ሔ/ቁ.2472(1) |
| 3 | 118246 | የሲዲሞ ተራ ህንጻ ስራ አክሲዮን ማህበር እና ወ/ሮ አብረኸት ሀብተእዝጊ ተማኑ ወራሾች (ዘጠኝ ሰዎች) | ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም | አንድ የውጪ ዜግነት ያለው ሰው በኢትዩጵያ ውስጥ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት ውስጥ አክሲዩንን በመግዛት ለንግድ ስራ ምቹ የሆነ ህንፃ በማሰራት የሥራ መስክ ሊሳተፍ የሚችል ስለመሆኑ<br><br>አንድ የባለአክሲዮኖቹ ጉባኤ ሕግን፣ መመስረቻ ፅሑፍንና መተዳደሪያ ደንብን በመከተል የተደረገ እስከሆነ ድረስ በሕጉ ጥበቃ የሚያገኝ ስለመሆኑ<br><br>አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12(1ሀ))፣ 2(6) እና 38 ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 3<br><br>የን/ሕ/ቁጥር 416(1) |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4 | 139932 | አስማማው በየነ<br>እና<br>አሰፋ ነጋሽ | ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም | ቼክ አምጪው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ባንክ ሣያቀርብ ይህንኑ ጊዚ አሳልፎ አንድ ዓመት ሣያልፍ ባንክ አቅርቦ በቼክ አውጪው ስም በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ቼክ አምጪ ቼኩን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክስ አንድ ዓመት አላለፈም በሚል የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br><br>በንግድ ህግ ቁጥር 881/1/ ስር በተመለከተው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ክስ የማቅረብ መብታቸው በህግ ፊት ተቀባይነት<br><br>ሊኖር የሚችለው በን/ሕ/ቁ. 855 ስር ቼኩን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለባንክ የማቅረብ ቅድመ ሁኔታ ሲያሟላ ስለመሆኑ፣<br><br>የን/ሕ/ቁ. 855፣881/1 |

